# ከ
# አምባገነን አገዛዝ
# ወደ
# ዲሞክራሲ

## ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ለነፃነት


**ጂን ሻርፕ**

አልበርት አንስታይን ኢንስቲትዩት


<u>ተርጓሚዎች፤</u>

1. *አሰፋ ኃይሉ ገዝሙ*
2. *ማሞ ተሰማ አርአያ*
3. *አያሌው ማሩ ራያ*

የተርጓሚዎቹ መብት በህግ የተጠበቀ ነው።

የመጀመሪያ ዕትም /እንግሊዝኛ 2002/
ሁለተኛው ዕትም /እንግሊዝኛ 2003/
የመጀመሪያው ዕትም /አማርኛ ኅዳር 1998/
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ



# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

የአልበርት አንስታይን ተቋም ተልዕኮ መግለጫ ..... I
የተርጓሚዎቹ ማስታወሻ ..... II
መግቢያ ..... V

ምዕራፍ አንድ
አምባገነኖችን መጋፈጥ ..... 1
1.1. ተደጋጋሚ ችግሮች ..... 2
1.2. በኃይል አመጻ ነጻነትን መቀዳጀት ይቻላል? ..... 5
1.3. መንግሥት ግልበጣ፣ ምርጫና ባዕዳን ደራሾች ..... 6
1.4. ሀቁን መቀበል ..... 9

ምዕራፍ ሁለት
የድርድር አደጋዎች ..... 11
2.1. የድርድር ጠንካራና ደካማ ጐኖች ..... 12
2.2 እጅ የሚያሰጥ ድርድር ..... 13
2.3. በድርድር ጊዜ የሚኖር ኃይልና ፍትህ ..... 14
2.4. ብልጣብልጥ አምባገነኖች ..... 16
2.5. ምን ዓይነት ሰላም? ..... 17
2.6. ተስፋ የማድረግ ምክንያቶች ..... 18

ምዕራፍ ሦስት
አቅም የሚገኘው መቼ ነው? ..... 20
3.1. የአምባገነኖች የፖለቲካ ሥልጣን ምንጮች ..... 21
3.2. የዲሞክራሲያዊ ሥልጣን ማዕከል ..... 25

ርዕስ ገጽ


ምዕራፍ አራት

አምባገነኖች ደካማ ጐኖች አሏቸው ..................... 28

4.1. የአቺሌን ተረከዝ መለየት ..................... 28

4.2. የአምባገነኖችን ደካማ ጐን ማጥቃት ..................... 31

ምዕራፍ አምስት

አቅምን በሥራ ላይ ማዋል ..................... 33

5.1. የሰላማዊ ትግል አካሄድ ..................... 34

5.2. ሰላማዊ የትግል መሣሪያዎችና ዲሲፕሊን ..................... 35

5.3. ግልፅነት፣ ምስጢራዊነትና ፅናት ..................... 39

5.4. የኃይል አሠላለፍን መቀያየር ..................... 40

5.5. አራቱ የለውጥ መንገዶች ..................... 41

5.6. የፖለቲካ ተቃውሞ ውጤቶችን ዲሞክራሲያዊ ማድረግ ..................... 44

5.7. የሰላማዊ ትግል ውስብስብነት ..................... 45

ምዕራፍ ስድስት

የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አስፈላጊነት ..................... 46

6.1. ትክክለኛ ዕቅድ መንደፍ ..................... 47

6.2. ዕቅድ የመንደፍ ዕንቅፋቶች ..................... 48

6.3. በስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅት አራት ቁልፍ ቃላት ..................... 52

ምዕራፍ ሰባት

ስትራቴጂያዊ ዕቅድ መንደፍ ..................... 56

7.1. የትግል ዘዴ አመራረጥ ..................... 58

7.2. ዲሞክራሲን ስለማቀድ ..................... 59

7.3. የውጪ ድጋፍ ..................... 60

7.4. ዓብይ ስትራቴጂ መቅረፅ ..................... 61




ርዕስ ገጽ


7.5. የዘመቻ ስትራቴጂዎች መንደፍ ..................... 63

7.6. ትብብር የመንፈግን ፅንሰ ሀሳብ ማሰራጨት ..................... 67

7.7. ጭቆናና የአፀፋ እርምጃዎች ..................... 68

7.8. በስትራቴጂያዊ ዕቅዱ መተማመን ..................... 70

ምዕራፍ ስምንት

ፖለቲካዊ ተቃውሞ ..................... 71

8.1. መርጦ መቃወም ..................... 72

8.2. ተምሳሌታዊ ግፍጫ ..................... 73

8.3. ኃላፊነትን ማከፋፈል ..................... 75

8.4. በአምባገነኑ ሥልጣን ላይ ማለም ..................... 76

8.5. ስትራቴጂ መለወጥ ..................... 79

ምዕራፍ ዘጠኝ

አምባገነናዊነትን ማናጋትና ማፈራረስ ..................... 81

9.1. ነጻነትን ማጉልበት ..................... 84

9.2. አምባገነናዊነትን ማፈራረስ ..................... 86

9.3. ስኬትንና ድልን በወጉ መያዝ ..................... 87

ምዕራፍ አሥር

ለዘላቂ ዲሞክራሲ የመሠረት ድንጋይ መጣል ..................... 90

10.1. የአዲስ አምባገነናዊነት ሥጋት ..................... 91

10.2. መፈንቅለ መንግሥትን መዝጋት ..................... 91

10.3. ሀገ-መንግሥት ማርቀቅ ..................... 93

10.4. ዲሞክራሲያዊ የመከላከያ ፖሊሲ ..................... 94

10.5. ከበሬታን የሚያጐናጽፍ ኃላፊነት ..................... 95

አባሪ ..................... 97-106

## <u>የአልበርት አንስታይን ተቋም</u>
## <u>ተልዕኮ መግለጫ</u>

የአልበርት አንስታይን ተቋም /ኢንስቲትዩት/ ተልዕኮ ሰላማዊ ትግል በግጭት ውስጥ ያለውን ሚና በሚመለከት ጥናትና ምርምር በማድረግ ስትራቴጂያዊ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ የሚውልበትን ዘዴ ማጐልበት ነው። በመሆኑም ተቋሙ፣

- ዲሞክራሲያዊ ነጻነቶችንና ተቋሞችን ይንከባከባል፤
- ጭቆናን፣ አምባገነንነትንና የዘር ማጥፋት ወንጀልን ይኮንናል፤
- ዓላማን ለማስፈፀም ኃይል መጠቀምን በብርቱ ይቃወማል፤

### <u>ተልዕኮውን ለመተግበርም ሦስት ዓይነት መንገዶች ይጠቀማል</u>

- ሰላማዊ የእምቢተኝነት ዘዴዎች በተለያዩ ግጭቶች ያስገኟቸው ውጤቶች ጥናትና ምርምር እንዲደርግባቸው ያበረታታል፤
- የተገኙትንም ውጤቶች በህትመቶች፣ በስብሰባዎችና በመገናኛ ብዙሀን አማካይነት ልምዱን ያከፍላል፤
- ሰላማዊ ትግል ስላለው ስትራቴጂያዊ ዕምቅ ኃይል በግጭት ተሳታፊ ከሆኑ ወገኖች ጋር ምክክር ያደርጋል።

## የተርጓሚዎቹ ማስታወሻ

የእዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ረቂቅ የተሰናዳውና በባንኮክ/ታይላንድ/ የታተመው በ1993 እ.ኤ.አ መሆኑን ከመግቢያው ላይ መረዳት ይቻላል:: በአሜሪካ የመጀመሪያው ዕትም የወጣው ግን እ.ኤ.አ በ2002 ነው:: ይህን ቅጂ ቀደም ሲል ያውቁት የነበሩ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወዳጆቻችን ከኢንተርኔት ፈልገን እንድናነበው ጠቆሙን:: እንደተባለውም አገኘንና አነበብነው:: በኢንተርኔት በተሠራጨው የኤሌክትሮኒክስ ቅጅው ላይ በ2003 እንደገና መታተሙን ተረዳን:: ምናልባት ከቀዳሚው ዕትም ሁለተኛው ዕትም የተሻሻለ ሀሳብና የተጨመረ አዲስ ነገር ይኖረው እንደሆነ በማለት እነዚያኑ ወዳጆቻችንን ቅጂውን እንዲልኩልን ጠየቅናቸው:: እነሱም የ2003ን ሁለተኛ ዕትም ሌላ ማሳሰቢያ ጨምረው ላኩልን::

ማሳሰቢያቸውም፣ ይህ በእንግሊዝኛ የተሰናዳ መጽሐፍ በይዘቱ እጅጉን ጠቃሚ ከመሆኑ የተነሳ አብዛኞቹ አማርኛ ማንበብ የሚችሉ ኢትዮጵያውያን እንዲያነቡት ብትተረጉሙትና ታትሞ ቢሰራጭ የሚል ነው:: ከትርጉማ ሀሳባቸውም ጋር ትርጉሙን በኮምፒውተር ለመጻፍ፣ ረቂቁን ለማተምና ለማረም እንዲሁም እስከ ህትመት ገጽ ዝግጅት ድረስ ያለውን ማናቸውንም የጸሐፊና የጽህፈት መሣሪያ ወጪ መሸፈን እንደሚችሉ ቃል በመግባት ከባድ አደራ ጣሉብን:: ብዙ ሳይቆዩም ቃላቸውን አሟልተዋል::

እኛም አደራውን ተቀበልን፤ መጽሐፉንም እንደገና ዳር እስከዳር መመርመር አስፈለገን፤ ባደረግነው ምርመራም የመጽሐፉ ይዘት ምንም እንኳ በሌሎች ሀገሮች ታሪክና ተሞክሮ ላይ ተመሥርቶ ቢጻፍም፣ አጠቃላይ ገጽታው የሀገራችንን ታሪክና ወቅታዊ ሁኔታ ፍንትው አድርጉ የሚያሳይ ሆኖ አገኘነው:: ይህ እንዴት እንደሆነ ጥቂት ነጥቦች እንዘርዝር::

የመጽሐፉ ዋና ርዕስ «ከአምባገነናዊነት ወደ ዲሞክራሲ» የሚል ነው:: በመጽሐፉ 10 ያህል ምዕራፎችና 198 ዝርዝር ተግባሮች ያሉት አባሪ አለው:: የመጀመሪያዎቹ የመጽሐፉ ምዕራፎች ስለአምባገነናዊ አገዛዝ ባህርያት ጥንካሬና ድክመት፣ ስለሰላማዊ ትግል (ህዝባዊ እምቢተኛነት) ምንነት፣ ለዲሞክራሲ



መስፈን አስፈላጊ ስለሆኑ የትግል ሥልቶች በአጫጭሩና በግልጽ ምሳሌዎች ያስረዳል:: አምባገነናዊነትን ለመዋጋት ከኃይል አመጻና ከጦርነት አማራጭ ይበልጥ ሰላማዊ ትግልና ሰላማዊ እምቢተኛነት የተሻለ እንደሆነ ያብራራል:: በሰላማዊ ትግሉ ውስጥ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎችም ይመከራል::

መጽሐፉ፣ በሰላማዊ እምቢተኛነት አማራጭ ላይ ማተኮር ዋነኛ ጥቅሙ አምባገነኑ አገዛዝ የማያውቀውና የማይዘጋጅበት የትግል ሥልት መሆኑን ከልዩ ልዩ አገሮች ምሳሌዎችን በመጥቀስ ያብራራል:: ሰላማዊ ህዝባዊ እምቢተኛነት የሁሉንም ጭቁን ህዝቦች ተሳትፎ ለማስተባበር የሚያስችል ሥልት በመሆኑ አምባገነኖች እጅጉን የሚፈሩት፣ የሚጠሉትና ሊያሸንፉት የማይችሉት መሆኑን በማስረጃ አስደግፎ ያስገነዝባል:: ይህ ከልዩ ልዩ ሀገሮች ታሪክና ተሞክሮ በመነሳት የቀረበው ከአምባገነን አገዛዝ ነጻ የመውጫ ሥልት ባለፉት ዘመናት በሀገራችን ይደረጉ ከነበሩት የአመጻ የሥልጣን ንጥቂያዎችና የአምባገነኖች መትከያዎች እጅጉን የተለየ መሆኑን፣ ተገዢና ተጨቋኝ ህዝቦች ጠመንጃ አንስቶ ከማመጽ ይልቅ ሰላማዊ እምቢተኛነት የማይበገር የህዝብ ኃይል የሚፈጥር መሆኑን ያሳያል፤ ከአምባገነኖች ጋር በሚደረገው ትንቅንቅ በሰው ኃይል፣ በንብረትና ህይወት ላይ የሚደርሰው ጥፋት ከጦርነት በእጅጉ የሚያንስ መሆኑን በተከታታይ ምዕራፎቹ ያስገነዝባል::

በዚህ ትይዩ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሀገራችን ሥልጣንን በጦርነት ሳይሆን በሰላማዊ ትግል መያዝና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን መገንባት ይቻላል በሚል መነሻ የሚንቀሳቀሱ ወገኖች መኖራቸው ሀቅ ነው:: የእነዚህ ወገኖች ያላሰለሰ ጥረት፣ ቅስቀሳና ምሳሌነት ያለው እንቅስቃሴ ከግንቦት 7/1997 ዓ.ም. በፊት ባደረጉት ተግባራዊ ክርክርና ውይይት ታይቷል:: በጥቂት ወራት ውስጥም ህዝቡን ከፍርሃትና ከግዴለሽነት አላቀው ለመብቱ የሚቆምና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በሰላማዊ እምቢተኛነት ሊታገል የቆረጠ እንዲሆን አብቅተውታል::

በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የአምባገነን ገዢዎች ዝርዝር ባህርያት በውል ላጤናቸው ከትናንት ወዲያ፣ ትናንት፣ ወይም ዛሬ በየአካባቢያችን፣ በየክልላችንና በሀገራችን የተደረጉ፣ ወይም በመደረግ ላይ ያሉ መሆናቸውን

በአእምሮአችን ውስጥ እናሰላስላቸዋለን:: በዲሞክራሲያዊ ተቃዋሚ ወገኖች በኩል የሚደረጉት እርምጃዎችም ቢሆኑ አብዛኞቹ በዓለም ውስጥ ለሰላማዊ ትግል ከሚደረጉት እንቅስቃሴዎች ጋር የሚጣጣሙ ለመሆናቸው ይህ መጽሐፍ ምስክርነት ይሰጣል:: ኢትዮጵያውያንም የየትኛውም ሰላማዊ ተቃዋሚ ድርጅት ደጋፊ ይሁኑ፣ አይሁኑ፣ ለረጅም ዘመናት በሀገራቸው ተንሰራፍቶ የኖረውን ትርምስና ምስቅልቅል የበዛበትን የሥልጣን ሽግግር በሰላማዊ ትግል መለወጥ እንደሚቻል አምነው ያደረጉትና እያደረጉት ያለው ተግባራዊ ሰላማዊ እምቢ ባይነት ከመጽሀፉ ሀቆች ውስጥ ትይዩ ማመሳከሪያዎች አሉት:: እናም ለሰላማዊ ትግልና አልገዛም ባይነት ቆርጠው የተነሱ ዜጎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚመክረውን መጽሐፍ ሀሳብ በጥቂቱም ቢሆን በተግባርም እየተረጉምነው ያለን ይመስለናል::

ከዚህ በላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም ዝርዝር ጠቀሜታዎች የተነሳ ወዳጆቻችን በጠቆሙን መሠረት መጽሐፉን ተርጉመነዋል:: ስንተረጉምም የዋናውን ሥራ መሠረታዊ ፈለግና አወቃቀር ሳንለቅ፣ በእኛም እምነት፣ ለእኛም ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ እንዲስማማ አድርገን ነው:: በዋናው ሥራ ውስጥ የቀረቡትን የግርጌ ማስታወሻዎች ትተናቸዋል:: ይህንንም ያደረግነው የህትመትንና የገጽ ቅንብርን ጣጣ ላለማብዛትና የማተሚያ ወጪንም ለመቀነስ በማሰብ ነው:: በተርጓሚዎቹ እምነት የግርጌ ማስታወሻዎቹ መቅረታቸው ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት አይጐዳውም::

በዚሁ የተርጓሚዎች ማስታወሻነት ያቀረብናቸውን ሀሳቦች ይበልጥ ለመረዳት ትችሉ ዘንድ ለመልካም ንባብ በመጋበዝ እናብቃ::

*ተርጓሚዎች:- አሰፋ ኃይሌ ገዝሙ*
*ማም ተሰማ አርአያ*
*አያሌው ማሩ ራያ*
*ጥቅምት 1998 ዓ.ም.*



## መግቢያ

ሕዝቦች አምባገነኖችን እንዴት መከላከልና ማጥፋት እንደሚችሉ ለብዙ ዓመታት ሲያስጨንቀኝ ቆይቷል:: ይህም ሊቀረፅብኝ የቻለው የሰው ልጅ በእንደዚህ ዓይነቶቹ አምባገነኖች ሊጨቆንና ሊጠፋ እንደማይገባ ካለኝ ፅኑ እምነት አኳያ ነው:: ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ስለሰው ልጅ ነጻነት፣ ስለአምባገነኖች ተፈጥሮ /ከአርስጣጣሊስ እስከ ጊዜው ፍፁም አገዛዝ ድረስ/ እንደዚሁም የአምባገነኖችን ታሪክ /በተለይም የናዚዎችና የስታሊናዊያንን ሥርዓቶች/ በመመርመር እየተጠናከረ የመጣ እምነት ነው:: በአለፉት ዓመታት ከናዚዎች የማጐሪያ ካምፖች ያመለጡትን ጨምሮ በናዚዎች አገዛዝ የተሰቃዩ ሰዎችን ለማግኘትና ለማወያየት ችያለሁ:: በኖርዌይ የፋሽስቶችን አገዛዝ ተቋቁመው የተረፉና ሌሎች የተጨፈጨፉ ሰዎችን ታሪክ ሰምቻለሁ:: ከናዚ ማጐሪያ ካምፖች ያመለጡና እንዲያመልጡ ያገዟቸውን ሰዎች ታሪክ ጭምር ከአይሁዶች ጋር ለመወያየት ችያለሁ::

በተለያዩ አገሮች ስለነበረው የኮሚኒስቶች አገዛዝ ለመረዳት ግን ከግለሰቦች ይልቅ መረጃው የተገኘው ከመጻህፍት ነው:: በተለይም የእነዚህ ሥርዓቶች የሰቆቃ አገዛዝ ከጭቆናና ከብዝበዛ በሚያወጣ ነጻነት ስም በሕዝብ ላይ የተጫነ በመሆኑ እነዚህ ሥርዓቶች በተለየ ሁኔታ ያሳዝኑኛል::

በቅርብ አሥርት ዓመታት ደግሞ እንደፓናማ፣ ፖላንድ፣ ቺሊ፣ ቲቤትና በርማ በመሳሰሉ በአምባገነኖች በሚገዙ ሀገሮች በተካሄዱ ግለሰባዊ ግንኙነቶች አማካይነት ስለአምባገነኖች እውነታውን ይበልጥ ተረድቻለሁ:: የቻይናን ኮሚኒስቶች ወረራ ከተዋጉ ቲቤታውያን፣ የኦገስት 1991 ዓ. ም. የአክራሪዎችን መፈንቅለ ሥልጣን ካከሸፉ ሩሲያውያንና ሀገሪቱን ወደ ወታደራዊ አገዛዝ ለመመለስ የተደረገውን ሙከራ በሠላማዊ መንገድ ከቀለበሱት ታይላንዳውያንም ስለአምባገነኖች የተለያዩ፣ አስገራሚና ክፉ ተፈጥሮ ብዙ ለመማር ችያለሁ::

እነዚህን የጭካኔ አገዛዞች ለመቋቋም የተደረገው ትግልና የተከፈለው መስዋዕትነት መሪር ሀዘን የሚፈጥረውን ያህል አሁንም ድረስ የከፋ አደጋ

ባለበትና ጠንካራ የህዝብ ተቃውሞ በሚታይበት ህብረተሰብ የሚካሄደው ለማመን የሚያስቸግር ተጋድሎ፣ ቆራጥነትና ጀግንነት ሲታሰብ መንፈስን ያበረታታል:: ከእነዚህም በኖሬጋ አገዛዝ የፓናማ ህዝብ፣ በቪልኒየስ/ሉቲኒያ/ በሶቪየት አገዛዝ ዘመን የተፈጸመው፣ በቤጂንግ የታይናንሜን አደባባይ ጭፍጨፋ እንደዚሁም ነጻ በወጣው የበርማ ክፍል የሚገኘው የማኔርፕላው የዲሞክራሲያዊ ኃይሉ ጠቅላይ መምሪያ ይገኙበታል::

አልፎ አልፎም በቪልየስ /ሪጋ/ የቴሌቪዥን ማማና ህዝባዊ መናፈሻ የተረሸኑ ሰዎችን የቀብር ሥፍራ፣ በሰሜን ኢጣልያ ፌራራ ፋሽስቶች ተቃዋሚዎችን አሰልፈው የረሸኑበትን፣ እንደዚሁም በማኔርኘላው በለጋ ዕድሜያቸው የተፈጁ ህፃናት አስከሬን የተከማቸበትን የጅምላ መቃብር ለማየት ችያለሁ:: እያንዳንዱ አምባገነን ይህን የመሰለ ፍጅትና ጥፋት ትቶ ማለፉ ሲታሰብ በእጅጉ የሚዘገንንና የሚፀጽት ነው::

ከዚህም በመነሳት አምባገነንነትን ያለብዙሀን ጭፍጨፋ መታገል እንደሚቻልና አምባገነኖች ሲጠፉና በነባሮቹ አምባገነኖች ፍርስራሽ ላይ አዳዲሶችም እንዳይፈጠሩ ለማድረግ እንደሚቻል ጠንካራ ተስፋ አሳድሯል::

የተቻለውን ያህል የህዝብን ሰቆቃና የህይወት መጥፋት በመቀነስ አምባገነኖችን ለማስወገድ የሚቻልበትን ውጤታማ መንገድ በጥንቃቄ ለማሰላሰል ሞክሬያለሁ:: በዚህም መሠረት በአምባገነኖች አገዛዝ፣ በተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ፣ በአብዮቶች፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በመንግሥት ሥርዓቶችና በተለይም ሊተገበር በሚችል ሰላማዊ ትግል ላይ ለብዙ ዓመታት ጥናት በማድረግ ድምዳሜ ላይ ደርሻለሁ:: የዚህ ጥናት ውጤትም ይህ መፅሀፍ ነው:: መፅሀፉ ፍፁም ባይሆንም ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ከሚገመተው በላይ ኃይል እንዳላቸው እንዲገነዘቡና ውጤታማ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን ለማቀድ መነሻ ሊሆናቸው እንደሚችል እገምታለሁ::

የዚህ መፅሀፍ ትኩረት ተመሳሳይ ባህርይ ያላቸውን አምባገነኖች ማጥፋትና አዳዲሶችም እንዳይፈጠሩ መከላከል ነው:: በእያንዳንዱ ሀገር ለሚካሄድ ትግል ዝርዝር መመሪያ ለመንደፍ ግን ችሎታው የለኝም:: ይሁንና የአምባገነኖችን ተመሳሳይ ባህርይ የሚያሳየው ይህ ትንተና ባሁኑ ጊዜ



በአምባገነኖች ሥር ለሚሰቃዩ ህዝቦች ትግል ሊጠቅም እንደሚችል ተስፋ አደርጋለሁ:: በመፅሀፉ ውስጥ የተሰነዘሩት ዋና ዋና ሀሳቦች የትግሉ መሪዎች የራሳቸውን ትግል ለማራመድ የሚኖራቸውን አግባብነትና ጠቀሜታ ከሚገኙበት ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ ለመመርመር ያግዟቸዋል::

ይህን መፅሀፍ ሳዘጋጅ የበርካታ ሰዎች አስተዋፅኦ ያለበት ቢሆንም ትንተናውና ድምዳሜው ግን የእኔ ሀላፊነት ነው:: በዚህ መፅሀፍ በየትኛውም ክፍል አምባገነኖችን መቋቋም ዋጋ የማይከፈልበትና ቀላል ተግባር እንደሆነ አልገለፅኩም:: ሁሉም የትግል ዓይነቶች እጅግ ውስብስብነት ያላቸውና መስዋዕትነትን የሚጠይቁ ናቸው:: አምባገነኖችን መፋለም ያለጥርጥር አደጋ ያስከትላል:: ይሁንና በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የተሰጠው ትንተና የትግል ስትራቴጂ ቀያሾች አቅማቸውን ለማጉልበትና መስዋዕትነታቸውን ለመቀነስ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች እንዲነድፉ እንደሚያነሳሳቸው ተስፋ አደርጋለሁ::

ከዚህም በላይ መፅሀፉ አንድ አምባገነን ሲወገድ ሌሎች ችግሮች ሁሉ በቅፅበት ይጠፋሉ የሚል መልዕክት የለውም:: የአንድ አምባገነን ውድቀት ችግሮችን ሁሉ በቅጽበት በማጥፋት ተምኔታዊ ሥርዓት አይፈጥርም:: ይልቁንም ጠንክሮ በመሥራት የተመጣጠነ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሥርዓት ለመፍጠርና በማህበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ኢ-ፍትሀዊ ግንኙነቶችንና ጭቆናዎችን ለማጥፋት በሩን ወለል አድርጉ ይከፍታል:: በዚህ መፅሀፍ ውስጥ አንድ አምባገነን እንዴት እንደሚበታተን የተገለጸው ሀሳብ በየትኛውም ሀገር በአምባገነኖች ሥር በጭቆና ለሚኖሩና ነጻነታቸውን ለሚናፍቁ ህዝቦች ጠቃሚ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ::

ጂን ሻርፕ

ጁን፣ 2003 /እ.ኤ.አ/

ዩ. ኤስ. ኤ

# ምዕራፍ አንድ

## አምባገነኖችን መጋፈጥ

በአሁኑ ጊዜ የተለያየ መልክ ያላቸው አምባገነን መንግሥታት በህዝብ አልታዘዝም ባይነት እየተፍረከረኩ በአፍጢማቸው ተደፍተዋል። ሕዝቦች በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውና በማህበራዊው መስክ የሚያሳዩትን አልታዘዝም ባይነት ለመቋቋም አምባገነኖች ክንዳቸው ሲዝልና ጉልበታቸው ሲብረከረክ ይስተዋላሉ። ለምሳሌ እ.ኤ.አ. ከ1980 ጀምሮ በኢስቶኒያ፣ በላቲቪያ እና ሊቷንያ፣ በፖላንድ፣ በምስራቅ ጀርመን፣ በቼኮዝሎቫኪያ እና ስሎቬኒያ፣ ማዳጋስካር፣ ማሊ፣ ቦሊቪያና በፊሊፒንስ አምባገነን መንግሥታት በሰላማዊ የህዝብ አልገዛም ባይነት ተንኮታኩተዋል።

በኔፓል፣ በዛምቢያ፣ በደቡብ ኮሪያ፣ በቺሊ፣ በአርጀንቲና፣ በሀይቲ፣ በብራዚል፣ በኡራጓይ፣ በማላዊ፣ በታይላንድ፣ በቡልጋሪያ፣ በሀንጋሪ፣ በዛየር፣ በናይጀሪያና በቀድሞዋ የሶቭየት ህብረት በ1991 የተደረገውን የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ በየግዛቶቿ በሚገኙ ሕዝቦች የተካሄዱ ሰላማዊ ግፍጫዎች ትግሉን ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አሸጋግረውታል። በቅርቡም በቻይና፣ በበርማና በቲቤት የተካሄዱት መሰል ሰላማዊ ትግሎች አምባገነን መሪዎችን ከሥልጣን ዙፋናቸው ማስወገድ ባይችሉም፣ ባንድ በኩል የመሪዎቹን ጨቋኝነትና ገዳይነት ለዓለም ህብረተሰብ ያጋለጡ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ሕዝቦች መሰል ትግሎችን በተጠናከረ መልካቸው እንዲቀጥሉ ትምህርት ሰጥተው አልፈዋል።

ሰላማዊ ትግል ለመብት ማስከበር መቆምን፣ ለጨቋኞች አለመታዘዝን እና አልምበረከክም ባይነትን ያካትታል። ከላይ

እንደተጠቀሰው የአምባገነን መንግሥታትን ውድቀትን ተከትሎ እነደ ድህንነት፣ ወንጀል፣ ቢሮክራሲያዊ አቅመቢስነት፣ የተፈጥሮ አካባቢ ቀውስና የመሳሰሉት ባንድ ጊዜ ተወግደዋል ማለት አይቻልም። ይሁን እንጂ በህዝቦቹ ላይ ተንሰራፍቶ የነበረው የግፍ አገዛዝ ተወግዶ በምትኩ ፖለቲካዊ ዴሞክራሲ፣ የግል ነጻነትና ማህበራዊ ፍትህ የሚያጐናፅፉ አስተዳደሮች ሰፍነዋል።

## 1.1. ተደጋጋሚ ችግሮች

ካለፉት አሥርት ዓመታት ጀምሮ በዓለም ላይ ያሉ ሕዝቦች ወደ ነጻነትና ዴሞክራሲ እየተጓዙ ይገኛሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰዎችን ፖለቲካዊ መብቶችና የነፃነቶች ደረጃዎችን የሚያመለክቱ መረጃዎችን በየዓመቱ በመመዝገብ የሚታወቀው ፍሪደም ሀውስ /Freedom House/ የተባለውና በኒውዮርክ የሚገኘው ድርጅት የሚከተሉትን መረጃዎች አቅርቧል።

| | ሙሉ ነጻ ሀገሮች | በከፊል ነጻ ሀገሮች | ነጻ ያልሆኑ |
|---|---|---|---|
| እ.ኤ.አ. 1983 | 55 | 76 | 64 |
| እ.ኤ.አ. 1993 | 75 | 73 | 38 |

በዚህ መረጃ መሠረት መብታቸውን የሚያስከብሩ ሕዝቦች ቁጥር እያደገ ቢሄድም በጭቆናና በአፈና ሥር ያሉት አገሮች ሰቆቃ በቀላሉ የሚታለፍ አይደለም። ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በጥር 1993 ዓ.ም. 5.45 ቢሊዮን ከሚሆነው የዓለም ሕዝብ መካከል 31% የሚሆኑት ነጻነታቸውንና ሰብዓዊ መብታቸውን የተገፈፉ ናቸው።

በ38 ሀገሮችና በ12 ቀጠናዎች የሚኖሩ ነጻነት የሌላቸው ህዝቦች ማለትም በርማንና ሱዳንን የመሳሰሉት በወታደራዊ አምባገነን አገዛዝ ሥር፣ ሳውዲ አረቢያንና ቡታንን የመሳሰሉት ደግሞ በባህላዊ አፋኝ ንጉሳዊ አገዛዝ ሥር፣ ቻይናን፣ ኢራቅንና ሰሜን ኮሪያን የመሳሰሉት



ደግሞ በጨቋኝ የፖለቲካ ፖርቲ ሥር፣ ቲቤትንና ምሥራቃዊ ቲሞርን የመሳሰሉት ደግሞ በውጭ ወራሪ ኃይሎች መዳፍ ሥር ተይዘው የሚማቀቁ ናቸው።

የሕዝባቸውን መብትና ነጻነት የሚያስከብሩና ኢኮኖሚያቸውን የሚያሳድጉ ሀገሮች ቁጥር እየጨመረ የመምጣቱን ያህል በተቃራኒው ወደኋላ የሚጓዙ ሀገሮችም ሁኔታ አሳሳቢ ሆኗል። እነዚህ ሀገሮች በዴሞክራሲና በሀገር ዕድገት ስም በሚምሉና በሚገዙ አዲስ ዓይነት አምባገነን መሪዎች መዳፍ ሥር ወድቀዋል። በእነዚህ መሰል መንግሥታት ውስጥ ወታደራዊ የአመራር ቡድኖች፣ ስግብግብና ፍላጐታቸው የማይረካ ግለሰቦች፣ በሕዝብ ምርጫ ስም የተደራጁ ስብስቦችና ለጥቅም ማስከበሪያ በተቋቋሙ የፖለቲካ ፖርቲዎች ሥር የተጠለሉ ግለሰቦች ፍላጐታቸውን በሕዝቡ ላይ ይጭናሉ። ተግባራዊ የሚደረገውም የሕዝቡ ፍላጐት ሳይሆን የእነዚህ ቡድኖች ፍላጐት ይሆናል።

አለመታደል ሆኖ ያለፈው የመከራ አገዛዝ ሁሉ እስካሁንም በሕዝብ ጫንቃ ላይ ተንሰራፍቶ ይገኛል። የአምባገነን መሪዎች የጭካኔና የአፈና ሥልታቸው በግልጽም በሥውርም ሥር እንደሰደደ ነው። ብዙውን ጊዜ ሰዎች መብታቸው ሲገፈፍና ሲጨቆኑ ለምን ብሎ አለመጠየቅና አሜን ብሎ የመቀበል ሁኔታ የቆየና እግር ተወርች የአሰረ ችግር ነው። አምባገነን መሪዎች ነጻ የሆኑ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የሃይማኖት ተቋማት እንዳይኖሩ የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ። ቢኖሩም እንኳን ያዳክሟቸዋል። ምንጊዜም ቢሆን ፍላጐታቸው ማንኛቸውም ህዝባዊ ማህበራት ወይም ተቋማት የእነሱ የሥልጣን ማጠናከሪያና የእድሜ ማራዘሚያ እንዲሆኑ ነው። ለእነሱ መሣሪያ ካልሆኑ እንዲዳከሙ ያደርጓቸዋል፤ አልፎም ያፈርሷቸዋል። በምትካቸውም ታማኝና አገልጋይ የሆኑ ተቋማት ይፈለፍሉና የሕዝቡ

መቆጣጠሪያ መሣሪያ ያደርጓቸዋል። ሕዝቡ አምባገነን መሪዎቹ ያመጡለትንና የባረኩለትን እንዲያምንና እንዲሠራ ይደረጋል እንጂ በራሱ ተነሳሽነት የሚያደርገው አንዳች ነገር አይኖረውም። ሰዎች እርስ በርሳቸው እንዲተማመኑና አብረው በመሥራት መግባባትን እንዲፈጥሩ ዕድሉ አይሰጣቸውም።

ከዚህም የተነሳ ህብረተሰቡ መንፈሱ የደከመና በራሱ የማይተማመን ከመሆኑ የተነሳ በአንድ ልብ ተነሳስቶ መብቱን እንዳይጠይቅ ይሆናል። ሰዎች እርስ በርሳቸው በመነጋገር በአምባገነን መሪዎቻቸው ላይ ያላቸውን ጥላቻ መግለጽ የሚያስቡት ጉዳይ አይሆንም። የቱንም ያህል የነጻነትና የመብት ጥማት ቢኖራቸውም እንኳ አንዱ ከሌላው ጋር ለመነጋገር ይፈራል። ሌላው ቀርቶ በቤተሰብም መካከል ፍርሀት ይነግሳል። እነዚህ ሕዝቦች የሚገኙበት ሁኔታ ዓላማ የሌለው፣ ሥቃይና የተስፋ ጭላንጭል የማይታይበት የጭለማ ኑሮ ይሆናል።

በአሁኑ ወቅት ያለው የአምባገነንነት ይዞታ ቀደም ሲል ከነበረው ገጽታው በእጅጉ የባሰ ነው። ቀደም ሲል አንዳንድ የህብረተሰቡ ክፍሎች የተቃውሞ ሙከራ ያደርጉ ነበር፤ የህዝብ መንፈስም ለጊዜውም ቢሆን ከፍ ይል ነበር። በሌላ ጊዜ ደግሞ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች አንዳንድ መርሆዎችን በመንደፍ ያልተሳኩ የተቃውሞ ተግባራትን ያከናውኑ ነበር፤ ይሁንና መነሻ ምክንያታቸው ምንም ያህል ታላቅ ቢሆን፣ እንዲህ ያሉቱ ያለፉት ጊዜያት የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች አምባገነናዊ አገዛዙን ለማስወገድ እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚያዙትን ህዝቡን ከፍርሃትና ከታዛዥነት መንፈስ ነጻ አላወጡትም። እንደነዚያ ዓይነት ተግባራት ህዝቡን ወደነጻነት ወይም ወደተስፋ ሳይሆን በሚያሳዝን ሁኔታ ለባሰ ሥቃይና ሞት ዳርገውትም ይሆናል።



## 1.2.. <u>በኃይል አመፃ ነጻነትን መቀዳጀት ይቻላል?</u>

የኃይል አመፃ እርምጃ ጠቀሜታ የለውም። በመሠረቱ አምባገነን መሪዎች ለህገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎች፣ ለህጋዊ ሥርዓት፣ ለፍርድ ቤት ውሳኔዎችና ለህዝብ አስተያየት ቅንጣት ታክል ደንታ የላቸውም። አንዳንድ ሰዎች የጨቋኝ መሪዎችን እሥራት፣ ማሰቃየት፣ አፈናና ግድያ ማስወገድ የሚቻለው በአመጽ ብቻ ይመስላቸዋል። ጥቃቱ የደረሰባቸው ክፍሎች ያገኙትን ሁሉ መሣሪያ በመጠቀም ውጤቱ ምንም ይሁን ምን በአጥቂዎቻቸው ላይ ዓይናቸውን ጨፍነው ይነሳሉ። በቆራጥነትም ይታገላሉ። የአካልና የሕይወት መስዋዕትነትንም እስከመክፈል ይደርሳሉ። ነፃነታቸውን የተጎናጸፉበት ጊዜ ግን ጉልቶ አልታየም። እንዲያውም የህዝቦች ብጥብጥና አመጽ ማካሄድ አምባገነኖች የበለጠ የጭቆና ሠይፋቸውን እንዲመዙ በር ይከፍትላቸዋል።

ምን ጊዜም ቢሆን አንድ ህዝብ የአመጽ እርምጃን አማራጭ አደረገ ማለት አምባገነን መሪዎች የበላይነት የያዙበትን የትግል ሥልት መረጠ ማለት ነው። አምባገነኖች ከቀላል እስከ ከባድ የጦር መሣሪያ የታጠቁ በመሆናቸው የተለመደ አረመኔያዊ እርምጃቸውን እንዲወስዱ መልካም አጋጣሚ ያገኛሉ። ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች የሚወስዱት እርምጃ ረጅም ጊዜም ይፍጅ ወይም የአምባገነኖቹ አረመኔያዊ እርምጃ የማይቀር መሆኑ ለአፍታም መዘንጋት የለበትም። እንዲሁም ተጨቋኞች ባዶ እጃቸውን መሆናቸው መታወቅ አለበት።

አንዳንዶች መደበኛ ወታደራዊ እርምጃ የሚያዋጣ መስሎ ሲታያቸው፣ ሽምቅ ውጊያን ከጭቆና መላቀቂያ አማራጭ አድርገው ይወስዱታል። ይህም ቢሆን ግን ዲሞክራሲን በማስፈን ሰዎችን ከጭቆና ነጻ ያወጣበት ሁኔታ እምብዛም አልታየም። ይልቁንም በወገን ላይ መፈናቀልን፣ የአካል ጉዳትን፣ ዕልቂትን፣ ስደትንና የተለያዩ

ሥቃዮችን ከማስከተሉ ባሻገር ረጅም ጊዜም ይወስዳል:: በንድፈ ሀሳብ ደረጃና በአንዳንድ ስትራቴጂያዊ ትንታኔ ድጋፍ ቢኖረውም እንኳ በድል ለመወጣት እንደማያስተማምን እየታወቀ መጥቷል:: እንዲያውም በሽምቅ ውጊያ አማካኝነት ለሥልጣን የበቃ መንግሥት የቀድሞዎቹን የህዝብ ተቋማት ያፈራርስና የራሱን በመተካት ከቀድሞው የበለጠ ጨቋኝና አፋኝ ይሆናል:: ሥራው ሁሉ ያስፈራውን በመበቀል ላይ ያተኮረ ይሆናል:: በራሱም ስለማይተማመን ሁሉንም ነገር በአዲስ መልክ ለማደራጀት ደፋ ቀና ሲል ይኖራል:: ሁሉን ነገር ዲሞክራሲያዊ አካሄድ ነው እያለ በራሱ አምሳል ቀርጾ በማዕከላዊነት ራሱ ማካሄድ ይፈልጋል:: ኃይልን በመጠቀምም ተግባራዊ ያደርጋል:: ስለሆነም ተጨቋኝ ሕዝቦች አመፅን ትተው ሌላ ሰላማዊ አማራጭ መፈለግ ይኖርባቸዋል::

## 1.3. <u>መንግሥት ግልበጣ፣ ምርጫና ባዕዳን ደራሾች፤</u>

አምባገነን መሪዎችን በመገልበጥ ከሥልጣን ማስወገድ ቀላልና ፈጣን ዘዴ ሊመስል ይችላል:: ግን አይደለም:: አደገኛ ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል:: የመንግሥት ሥልጣኑንና ወታደራዊ ኃይሉን በመቆጣጠር ረገድ ቅጥ ያጣ የሥልጣን ምሥቅልቅል ሊያስከትል ይችላል:: ሥልጣን ላይ ያለ ጨቋኝ ቡድንን አስወግዶ በቦታው ሌላ ጨቋኝ ቡድን የመተካት አደጋም ይኖረዋል:: ምናልባት አዲሱ ቡድን ከበፊቱ ለስለስ ያለና ደህና ሊመስል ይችል ይሆናል:: ግን በተቃራኒውም የበለጠ አደገኛ ሊሆን ይችላል:: ቀስ በቀስም ሥልጣኑን እያጠናከረ ይመጣና የጭቃ ጅራፉን ያነሳል:: የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ፈፅሞ እንዳይነሳ ያደረጋል:: ስለሆነም መንግሥት ግልበጣ የሚጠቅም የትግል መሣሪያ አይደለም::



በአምባገነኖች የአገዛዝ ሥርዓት ውስጥ ሕዝባዊ ምርጫ የዴሞክራሲ አዋላጅ መሣሪያ አይደለም:: ጨቋኞች ለማስመሰያነት እንጂ በእውነት የፖለቲካ ለውጥ ለማምጣት አይጠቀሙበትም:: ዴሞክራሲያዊ ለመምሰል ሕዝቡ እንዲመርጥ ሲያደርጉም እነሱ አሸናፊ የሚሆኑበትን መንገድ በቅድሚያ አበጅተው ነው:: ለምሳሌ ከአምባገነን መሪዎቹ ነጻ የሆኑ በማስመሰል ዕጩዎችን አቅርበው ያስመርጣሉ:: የተቃዎሚ ፖርቲዎች ዕጩዎችን ከውድድሩም በፊት ሆነ ምርጫው ተካሂዶ ከተመረጡ በኋላ ያስፈራሯቸዋል፤ ያስደበድቧቸዋል፤ ያስሩዋቸዋል፤ ይባስ ብሎም ይገድሏቸዋል:: በበርማ በ1990፣ በናይጀሪያ በ1993 እንደተደረገው ተቃዋሚ ኃይሎች በምርጫ ተወዳድረው ሊያሸንፉ ይችሉ ይሆናል:: ይሁን እንጂ በተቃዋሚዎች የተገኘው ድል ተቀባይነት አያገኝም:: ይባስ ብሎ ተመራጮቹ ለወከባ፣ ለእሥርና ለስደት ሊዳረጉ ይችላሉ:: ለዚህም ነው፣ አምባገነን መሪዎች በምንም ዓይነት መንገድ ከሥልጣን መንበራቸው ሊያወርዳቸው የሚችል የምርጫ ውጤት አይቀበሉም የሚባለው::

ብዙ ሰዎች በአምባገነን መሪዎች መዳፍ ሥር የወደቁ ተጭቋኞች ራሳቸውን ነጻ ማውጣት ይችላሉ ብለው አያምኑም:: ስለሆነም ነጻ መውጣት የሚችሉት በሌሎች ትግል ይመስላቸዋል:: እምነታቸውን በውጪ ኃይሎች ላይ ይጥላሉ:: ጨቋኝ መሪዎችን ከሥልጣናቸው ማባረር የሚችለው ምናልባትም ዓለም አቀፋዊ ኃይል ይመስላቸዋል::

በእርግጥ በጨቋኞች ክንድ የደቀቁ ሕዝቦች ለተወሰነ ጊዜ ራሳቸውን ነጻ ማውጣት ሳይችሉ ሊቆዩ ይችላሉ:: ይህም የሚሆነው ለጊዜው ጨካኝና ነፍሰ ገዳይ መሪዎቻቸውን ሊቋቋሙ የሚችሉበት አቅም እንደሌላቸው ስለሚገምቱ ነው:: ለዚህም ምክንያቱ ራሳቸውን ከአደጋ መከላከል እንደሚችሉ ስለማይረዱና በራሳቸው ስለማይተማመኑ

ነው:: በመሆኑም በዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ውግዘት ላይ ወይም በተባበሩት መንግሥታት ላይ ወይም ባንድ ባሌላ ሀገር ላይ ወይም በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ማዕቀብ ላይ ይተማመናሉ::

እነዚህ ባዕዳን ደራሾች ለጊዜውም ቢሆን ተስፋ ሰጪና ውጤት የሚያስገኙ ይመስላሉ:: ግን መሠረታዊ አደጋ አለባቸው:: ማንኛውም ክፍል ጣልቃ ገብቶ ከጭቆና ነጻ ሊያወጣ አይመጣም:: ቢመጣም የሚታመን አይደለም:: ለማናቸውም፣ እነዚህን የውጪ ሀይሎች በሚመለከት የሚከተሉትን ፍሬ ሀሳቦች ማጤን ይጠቅማል::

- አብዛኛውን ጊዜ የውጪ መንግሥታት ለራሳቸው ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅም ሲሉ የጨቋኝ መሪዎችን አረመኔያዊ ሥራ ከመታገስም አልፈው ድጋፍ ያደርጉላቸዋል::
- የውጪ መንግሥታት ከጨቋኝ መንግሥታት ሊያገኙ ከሚፈልጉት ጥቅም በመነሳት የጭቁን ሕዝቦችን ትግል ከማገዝ ይልቅ አሳልፈው ሊሰጧቸው ይችላሉ::
- አንዳንድ የውጪ መንግሥታት አምባገነን መሪዎችን ሲቃወሙ የሚታዩት ሁኔታውን ተጠቅመው የተጨቋኝ ሀገሮች ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ተቋማትን ለመቆጣጠር ነው::
- የውጪ መንግሥታት በሌላ ሀገር ጨቋኝ መሪዎች ላይ እውነተኛ ተቃውሞ የሚያሳዩት የሕዝቡ ትግል ተጠናክሮና ገፍቶ ጨቋኞቹን ሲያብረከርካቸውና ሲያፍረከርካቸው ሲያዩ ብቻ ነው::

በአብዛኛው ጨቋኝ መሪዎችን በሥልጣን እንዲቆዩ የሚያደርጋቸው የሕዝቡ ሰላማዊ ትግል ደካማ መሆን ነው:: የሀገር ውስጡ ሁኔታ ለመኖራቸውም ሆነ ለመወገዳቸው ወሳኝ ነው:: በአምባገነኑ አገዛዝ ላይ ጉዳት ለማድረስ ህዝቡ ደካማ ከሆነ የሀገሪቱ ሀብትም ሆነ ሥልጣን



በጥቂቶች እጅ ይገባል:: አምባገነናዊነት ከውጪ ኃይሎች ድጋፍም ሆነ ተቃውሞ ቢገጥመውም እንኳ ለዕድሜው መራዘም ዓይነተኛ ዕድል የሚሰጠው የውስጥ ሁኔታ ነው:: የውጪ ኃይሎች ተቃውሞ ጠቃሚ የሚሆነው የውስጡ ትግል ጠንካራ ሲሆን ብቻ ነው:: የውጪ ኃይሎች ውግዘት፣ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መቋረጥ፣ ድጋፍ ማቆም እና የኢኮኖሚ ማዕቀብ መጣል በእርግጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል:: ቢሆንም የተጠናከረ የሀገር ውስጥ ተቃውሞና ትግል ከሌለ የነዚህ ሀይሎች እውነተኛ ድጋፍ ይኖራል ማለት ዘበት ነው::

## 1.4. ሀቁን መቀበል

እውነቱን መጋፈጥ መራራም ቢሆን አምባገነን መሪዎችን በትሳካ ሁኔታና ብዙ ዋጋ ሳይከፈል ከሥልጣን ለማስወገድ መጀመሪያ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል::

- ጭቁን ሕዝቦች ለትግል ያላቸውን ቁርጠኝነት፣ በራስ የመተማመን ሁኔታንና ችግሮችን የመቋቋም ብቃታቸውን ማጠናከር፣
- በራሳቸው በጭቁኖች የተቋቋሙ ማህበራዊ ስብስቦችንና ተቋማትን ማጠናከር ፣
- ጠንካራ የሆኑ የሀገር ውስጥ የተቃውሞ ኃይሎች መፍጠር፣
- ጭቁኖችን ነጻ ለማውጣት የሚያስችል ብልህነት የተሞላበት ስትራቴጃዊ ዕቅድ በመንደፍ በዘዴ ተግባራዊ ማድረግ፣

የነጻነት ትግል በራስ የመተማመንና የውስጥ ታጋይ ቡድኖችን ለማጠናከር የሚደረግ ትግል ነው:: በ1879 ና በ1880 ቻርለስ ስትዋርት ፓርኔል በአየርላንድ እንደጠሩት ያለው የኪራይ አድማ ዘመቻ ዓይነቱን እዚህ ላይ መጥቀስ ይቻላል::

*በመንግስት ላይ መተማመን ምንም ፋይዳ የለውም::*
*...በራሳችሁ ውሳኔና ቆራጥነት ላይ ብቻ ነው መተማመን*

*ያሰባችሁ::... አብሮ በመቆም ራሳችሁን እርዱ፣ በመካከላችሁ ደካሞች ካሉ አበረታቷቸው:: ራሳችሁን አስተሳስሩ ራሳችሁን አደራጁ፣ ታሸንፋላችሁም:: ይህ እንዲሆን እስካልተነሳችሁ ድረስ፣ እስከዚያች ጊዜ ድረስ የነጻነት ጥያቄው አይመለስም፤ አይሳካም::...*

በራሱ የሚተማመን ኃይል ካለ፣ ብልህነት የተሞላበት ስትራቴጂ ከተነደፈ፣ ሥነ-ሥርዓታዊና ደፋር እርምጃ ከተወሰደና ትክክለኛ/ሀቀኛ ጥንካሬ ከተገኘ አምባገነናዊ ሥርዓቱ ይፈረካከሳል:: ነገር ግን ቢያንስ እነዚህ አራቱ መስፈርቶች መሟላት ይገባቸዋል::

እነዚህ ሲሟሉ ሕዝቡ በራሱ የሚቆም ብቻ ሳይሆን ሥነ-ሥርዓት፣ ቆራጥነትና እውነተኛነት የተሞላበት ትግል ስለሚያካሂድ አምባገነን መሪዎች ይደነግጣሉ፤ ይርዳሉ፤ ባፍጢማቸውም ይደፋሉ:: ስለሆነም ከጨቋኝ መሪዎች ነጻ የመውጣቱ ነገር ጭቁን ሕዝቦች ራሳቸውን ነጻ ለማውጣት ባላቸው ብቃትና ችሎታ ላይ የተመሠረተ ነው:: ሰዎች በሰላማዊ ትግል ራሳቸውን ነጻ የሚያወጡባቸው በርካታ መንገዶች አሉ:: የተለያዩ አማራጮች አሏቸው:: ከእነዚሁ አምባገነን አገዛዝን ሊበታትኑት ከሚችሉት መካከል ድርድር አንዱ ስለሆነ በቅርበት እንየው::



# ምዕራፍ ሁለት

# የድርድር አደጋዎች

ቀደም ሲል እንዳየነው የአምባገነን መሪዎች ጥቃት ሲከፋ አንዳንድ ሰዎች ጸጥለጥ ወደ ማለቱ ይመለሱ ይሆናል:: ሌሎች ደግሞ የዲሞክራሲ ተስፋቸው ይጠፋና ይልቁንም ከአምባገነኖቹ ጋር በሽምግልና በመታረቅ፣ አንተም ተው አንተም ተው በመባባልና በመደራደር አረመኔያዊ ተግባሩ ቆሞ የተሻለ ነገር ሊመጣ ይችል ይሆናል ወደማለት ያዘነብላሉ:: ከላይ፣ ከላይ ሲታይ አስተማማኝ አማራጭ በሌለበት ሁኔታ በዚህ ዓይነት ማሰቡ የሚያዋጣ ይመስላል:: ነገር ግን ከጨካኝ አምባገነኖች ጋር መታገል አልጋ ባልጋ መንገድ የለውም::

አምባገነን መሪዎችን በመታገል ረገድ የተለያዩ አስተያየቶች አሉ:: ከአምባገነን መሪዎች ጋር ጠንከር ያለ ትግል ለምን ያስፈልጋል? ዝም ብሎ ከመጋፈጥ ይልቅ ምክንያት ባለው ነገር በመነጋገርና በመደራደር አምባገነናዊ ሥርዓትን ቀስ በቀስ ማስወገድ ይቻል ይሆን? አምባገነን መሪዎች ልብ ገዝተው የጭቆና አገዛዛቸውን እንዲያቆሙ በማነጋገር ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ለምን አያሳምኗቸውም? ይህን ቢያደርጉ ቀስ በቀስ ጨቋኝነታቸውን እየተዉ ዴሞክራሲን ሊያሰፍኑ ይችሉ ይሆን? የሚሉ ወገኖች አሉ::

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሀቅ ካንድ ወገን ብቻ አይኖርም የሚል ክርክር ይነሳል:: ምናልባትም አምባገነን መሪዎች አስቸጋሪ ሁኔታ ባጋጠማቸው ጊዜ ከችግሩ ለመውጣት በቀና መንፈስ ተነሳስተው የሚወስዱት እርምጃ በተዛባ ሁኔታ ይወሰድባቸው ይሆናል:: ወይም ምናልባት አንዳንዶች እንደሚሉት አምባገነን መሪዎች ከተወደሱና ከተበረታቱ ሀገራቸው ከምትገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በደስታ ራሳቸውን ያወጣሉ፤ ለአምባገነን መሪዎች ማንም ወገን አሸናፊ

ያልሆነበት ነገር ግን ሁሉም ወገን ተጠቃሚ የሚሆንበት የመፍትሔ ሀሳብ ሊቀርብላቸው ይገባል የሚል ክርክርም አለ:: ዲሞክራሲያዊ ተቃዋሚ ኃይሎች ከአምባገነን መሪዎች ጋር በሰላማዊ መንገድ በሚደረግ ድርድር ችግሮችን ለመፍታት ፈቃደኝነት ካላቸው በአመጽ ትግል ሊደርስ የሚችለው አደጋና ችግር ሊወገድ ይችላል የሚል ክርክርም ይቀርባል::

## 2.1. <u>የድርድር ጠንካራና ደካማ ጐኖች</u>

ድርድር አንዳንድ አለመግባባት የሚፈጥሩ ነገሮችን መፍታት የሚያስችል መሣሪያ ነው:: በመሆኑም አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ ሁሉ ወደጐን ሊገፋና ችላ ሊባል አይገባውም:: አንዳንድ ጊዜ መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ጉዳት የማይደርስ ከሆነ እንተም ተው አንተም ተው ተባብሎ መስማማት መልካም ነው:: የሠራተኛ ደሞዝ ጭማሪን ለማስገኘት የሚደረግ የሥራ ማቆም አድማ በድርድር አለመግባባትን ለመፍታት የሚያስችል ጥሩ ምሳሌ ነው:: ሠራተኞች ከሠራተኛ ማህበራቸው ጋር የሚፈጥሩት ግጭት ከጨካኝ አምባገነን መሪዎች ጋር ከሚፈጠር ግጭት ጋር በፍጹም የማይገናኝ ጉዳይ ነው:: ከጨካኝ መሪዎች ጋር ድርድር ውስጥ መግባት ፖለቲካዊ ነጻነትን አጣብቂኝ ውስጥ መክተት ነው:: አጣብቂኝ ውስጥ የገቡት ጉዳዮች መሠረታዊ የሆኑትን ሀይማኖታዊ መርሆዎችን፣ የሰውን ልጅ ነጻነትን፣ ወይም የህብረተሰቡን የወደፊት ዕድገት የሚነኩ ከሆኑ ተደራዳሪዎችን ሊያረካ የሚችል መፍትሔ ላይ አይደረስም:: በአንዳንድ መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የአንተም ተው አንተም ተው ድርድር ሊኖር አይገባም:: አጣብቂኝ ውስጥ የገቡ ነገሮችን ወደ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ለማምጣት የሚቻለው የኃይል ሚዛን ወደነሱ ዘንበል ካለ ብቻ ነው:: ይህ ደግሞ ዕውን የሚሆነው በጠነከረ ሰላማዊ ትግል እንጂ በድርድር አይደለም:: ይህ ሲባል ግን ድርድር ፈጽሞ አያስፈልግም ማለት አይደለም::



መታወቅ ያለበት ጉዳይ ጠንካራ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች በሌሉበት ሁኔታ ጨካኝ አምባገነን መሪዎችን ማስወገድ አይቻልም::

ድርድር አማራጭ ሆኖ የማይቀርብበት ሁኔታም አለ:: በማይነቃነቅ ሁኔታ ሥር የሰደዱና ባላቸው አቅም የሚተማመኑ አምባገነኖች ከሚቃወሟቸው ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር መደራደርን ፈጽሞ አይቀበሉም::

## 2.2. <u>እጅ የሚያሰጥ ድርድር</u>

አምባገነኖችን የሚቃወሙና ድርድር የሚፈልጉ ግለሰቦችና ቡድኖች ብዙውን ጊዜ ጥሩ ምክንያት ሊኖራቸው ይችላል:: በተለይ ድል የማይታይበት፣ ረጅም ጊዜ የሚወስድ የትጥቅ ትግል በአምባገነኖች ላይ ከተከፈተ ሰዎች የቱንም ያህል የፖለቲካ ዕምነት ቢኖራቸው ሰላምን ይፈልጋሉ:: በተለይ አምባገነኖች የኃይል /የጦር/ የበላይነት ካላቸው ዲሞክራቶች በሕዝባቸው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ዕልቂትና ጉዳት በማሰብ ወደ ድርድር ያዘነብላሉ:: ዲሞክራቶች ድርድር በማድረግ በመጠኑም ቢሆን ዓላማቸውን አሳክተው ሰላምን ለማስፈን ከፍተኛ ፍላጐት ሊኖራቸው ይችላል::

ይሁን እንጂ አምባገነኖች ለድርድር የሚያቀርቡት የሰላም ሀሳብ ሽፍጥ የተሞላበት ሀቅ የሌለው ማታለያ ነው የሚሆነው:: በመሠረቱ አመጽ የሚያነሱት አምባገነን መሪዎች ናቸው:: አመጹም በሕዝባቸው ላይ ነው:: ስለሆነም ሰላም የሚሰፍነው እነሱ በሕዝቡ ላይ የሚመዙትን ሠይፍ ወደአፎቱ ሲመልሱ ብቻ ነው:: በሕዝብ በኩልማ ማንም ማንንም እንደማይገድል ይታወቃል:: አምባገነኖች ሰላም ከፈለጉ እኮ ከማንም ጋር ድርድር ሳያስፈልጋቸው የሰውን ልጅ ክብርና መብት በመጠበቅ፣ ንጹህ ሰዎችን ባለማሠር፣ ካለህግ ያሠሩዋቸውን በመፍታት፣ ግድያንና አፈናን በማቆም፣ ሥልጣናቸውን በመልቀቅና ለፈጸሙት

ጥፋት ሕዝቡን ይቅርታ በመጠየቅ ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ ምንጊዜም በእጃቸው ያለ ነው::

አምባገነናዊ ሥርዓት አስጨናቂ ተቃውሞ የገጠመው እንደሆነ ሰላም በማስፈን ሽፋን ተቃዋሚዎችን ለድርድር በመጠየቅ ለጊዜው ሸብረክ ይል ይሆናል:: የድርድር ጥያቄውም የሰዎችን ዕይታ ሊስብ ይችላል:: ከድርድሩ ጀርባ ግን ትልቅ አደጋ ተደብቆ ሊሆን ይችላል:: ማሰብና ማሰላሰል ይህንን ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ ተቃውሞው በተለየ ሁኔታ ጠንካራ በሆነበትና ለአምባገነናዊው ሥርዓት በትክክል የሚያስፈራ በሆነበት ጊዜ አምባገነኖቹ የሥልጣን የበላይነታቸውን ወይም ያካበቱትን ሀብት ለማስጠበቅ ሲሉ ከምር ድርድር ሊፈልጉ ይችላሉ::

ስለዚህ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች በአምባገነኖች ሥውር ተንኮል ከተዘረጋላቸው ወጥመድ ሊጠነቀቁ ይገባል:: መሠረታዊ የሆኑት የፖለቲካ ነጻነት ጥያቄዎች ባሉበት ሁኔታ አምባገነኖች የሚያደርጉት የድርድር ጥሪት ዲሞክራቶችን ከትግላቸው ለማዘናጋትና እንዲብረከረኩ ለማድረግ ነው:: ይህን የሚያደርጉት ደሞክራሲያዊ ኃይሎቹ በሰላማዊ መንገድ ጥያቄዎቻቸውን እንዲያለዝቡና ጨቋኞቹ ግን በሕዝቡ ላይ የሚያካሂዱትን አመጽ እንዲቀጥሉ ሆነው ነው:: በነዚህ ዓይነት ግጭቶች ጊዜ የድርድር ዋናው ተግባር መከናወን ያለበት በወሳኙ ትግል መጨረሻ ላይ ማለትም አምባገነኖች በሚገባ ከተሸነፉ በኋላ ነው::

## 2.3. <u>በድርድር ጊዜ የሚኖር ኃይልና ፍትህ</u>

ድርድርን በሚመለከት የተሰጡት አስተያየቶች በጣም ከባድ ከሆኑ የተጋነኑ የሚመስሉት ሊለሳለሱ ይገባል:: ድርድር እንዴት እንደሚሠራ ለመረዳት ግልጽ የሆነ አስተሳሰብ መኖር አለበት::



«ድርድር» ሁለት ወገኖች አለመግባባት ስለፈጠሩባቸው ነገሮች በእኩልነት ደረጃ ቁጭ ብለው የሚወያዩበትና መፍትሔ የሚያገኙበት ማለት አይደለም:: እዚህ ላይ ሁለት እውነታዎች መታወቅ አለባቸው:: የመጀመሪያው በድርድር ስምምነት የሚደረስባቸውን ጉዳዮች የሚወስኑት አንፃራዊ ህጋዊነት ያላቸው የተደራዳሪዎች ወገኖች አመለካከቶችና ዓላማዎች አይደሉም፤ ሁለተኛው ደግሞ በድርድር ስምምነት የተደረሰባቸውን ጉዳዮች የሚወስነው በሁለቱም ተደራዳሪዎች ወገን ያለው የኃይል ሚዛን መሆኑ ነው::

በርካታ አስቸጋሪ ጥያቄዎችንም ከግንዛቤ ማስገባት ያስፈልጋል:: አንደኛው ወገን በድርድሩ ከስምምነት ላይ አልደርስም ብሎ ቢያፈርስ ሌላው ወገን ዓላማው ግቡን እንዲመታ ወደፊት ምን ማድረግ ይኖርበታል? ስምምነት ከተደረሰ በኋላ አንዱ ወገን ስምምነቱን አፍርሶ ያለውን ሀይል ተጠቅሞ ዓላማውን ለማሳካት ቢንቀሳቀስ ሌላው ወገን ምን ማድረግ ይኖርበታል?

በድርድር ጊዜ ስምምነት ላይ የሚደረሰው የአስቸጋሪ ጉዳዮችን ትክክለኛና ስህተተኛ ጐኖችን በመቃኘት አይደለም:: የድርድር እውነተኛው ውጤት ላይ ሊደረስ የሚቻለው የተደራዳሪዎችን የኃይል ሚዛን በመቃኘ ትና በመመዘን ነው:: ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ቢያንስ የአነስተኛ ጥያቄዎቻቸውን መልስ ለማረጋገጥ ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል? አምባገነኖችስ የበላይነታቸውን እንዳረጋገጡ ለመቆየት እንዲችሉና ዲሞክራቶችን ከጥያቄዎቻቸው ለማራቅና ገለልተኛ ለማድረግ ምን ማድረግ አለባቸው?

በድርድር ጊዜ ሁለቱም ወገኖች ምን ላይ ለቀቅ እንደሚሉ ወይም ምን ለመስጠት ፈቃደኛ እንደሆኑም ማየት ያስፈልጋል:: ውጤታማ ድርድር የሚኖረው ከሁለቱም ወገን ሰጥቶ መቀበል ሲኖር

ወይም አንተም ተው አንተም ተው ሲባል ነው። እያንዳንዱ ወገን ከሚጠይቀው የተወሰነውን ያገኛል፣ ከራሱም የተወሰነውን ይለቃል።

ድንበር በሌለው አምባገነናዊ ሥርዓት ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ለአምባገነኖች ሊሰጡት የሚችሉት ምንድነው? ከአምባገነኖች ዓላማዎች ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሊቀበሉ የሚችሉት የትኞቹን ነው? ዴሞክራቶች ለአምባገነኖች ወደፊት በሚመሠረተው መንግሥት ውስጥ በሕገመንግሥት የፀደቀ ቋሚ ተግባር እንዲኖራቸው የሚያደርግ ሥልጣን ሊሰጧቸው ነው? ይህ ከሆነ ደግሞ ዴሞክራሲው የት ጋ ነው የሚኖረው?

በድርድሩ ሁሉም ነገር በቀና ሁኔታ ሄዷል ተብሎ ቢታሰብም እንኳ ምን ዓይነት ሰላም ነው የሚመጣው? ዲሞክራቶቹ ትግል ቢጀምሩ ወይም የተጀመረውን ቢቀጥሉ የሕዝቡ ኑሮ በፊት ከነበረው የባሰ ወይስ የተሻለ ይሆናል? የሚሉትን ጥያቄዎች መጠየቅና መመለስ አስፈላጊ ነው።

## 2.4. ብልጣብልጥ አምባገነኖች

አምባገነኖች ሕዝብን ረግጠው ለመግዛት የሚያነሷቸው የተለያዩ ምክንያቶችና ዓላማዎች አሏቸው። ሲጠቀሱም ኃይል፣ ሥልጣን፣ ሀብት፣ ህብረተሰቡን ለነሱ በሚያመች መልክ መቀየርና የመሳሰሉት ናቸው። መታወቅ ያለበት ነገር በህዝቡ ላይ ያላቸውን ቁጥጥር ካጡ ከእነዚህ ከተጠቀሱት ፍላጐቶቻቸው መካከል አንዱንም ማሳካት እንደማይችሉ ነው። ስለሆነም በድርድር ጊዜ ለእነዚህ ግቦች መሳካት ጥረት ያደርጋሉ። አምባገነኖች በድርድር ጊዜ ምንም ዓይነት ቃል ቢገቡም ዓላማቸውን ለማሳካትና ዴሞክራቶችን በማዘናጋት ለማንበርከክ ሲሉ መሆኑ መታመን አለበት።



ዲሞክራቶች ከጭቆናና ከአፈና ጊዜያዊ እፎይታ እናገኛለን በማለት የተቃውሞ እንቅስቃሴዎቻቸውን ቢገቱ በኋላ በጣም ሊናደዱና ተስፋ ሊያጡ ይችላሉ። ተቃውሞ ማቆም አፈናን ሲቀንስ የሚታየው አልፎ አልፎ ነው። የተጀመረው ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቃውሞ ካቆመ አምባገነኖች አፈናና ጭቆናቸውን ከቀድሞው በበለጠ የጭካኔ ሁኔታ ሊቀጥሉ ይችላሉ። የሰላማዊ ሕዝባዊ ተቃውሞ መዳከም ማለት የአምባገነኖችን የጭካኔ አገዛዝ ማጠናከር ማለት ነው። በፈለጉት ላይ በፈለጉ ጊዜ የጥቃት ሰይፋቸውን እንዲመዙ ያደርጋቸዋል። ሕዝቦች የአምባገነኖችን ጭካኔ ለመመከት አቅም ባጡ ቁጥር የአምባገነኖቹ ክንድ ይፈረጥማል።

መሠረታዊ የሕዝብ መብቶች አደጋ ላይ በወደቁ ጊዜ ለውጥ ለማምጣት መፍትሔው ድርድር ሳይሆን ሰላማዊ ተቃውሞ ነው። በማንኛውም ሁኔታ አምባገነኖችን ከሥልጣን መንበራቸው ለማስወገድ ሰላማዊ ተቃውሞ ወሳኝ ነው። ፖለቲካዊ እምቢተኛነት ወይም ሰላማዊ ትግል ለመብታቸው ለሚታገሉ ሁሉ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው።

## 2.5. ምን ዓይነት ሰላም?

አምባገነኖችና ዲሞክራቶች ሁለቱም ስለሰላም የሚያወሩ ከሆነ በውስጡ አደጋ ስለሚኖረው ግልጽ የሆነ ሀሳብ ያስፈልጋል። ስለ«ሰላም» የሚያወራና የሚሰብክ ሁሉ ነፃነትንና ፍትህን ያሰፈነ ሰላም ይፈልጋል ማለት አይደለም። ለጭካኔ አገዛዝ መንበርከክና በህዝባቸው ላይ ጭፍጨፋን ለሚያካሂዱ አምባገነኖች የሕዝብ ዝም ብሎ ታዛዥ መሆን እውነተኛ ሰላም ሊሆን አይችልም። ለጨካኝ ገዥዎች ሰላም ማለት ካለምንም ተቃውሞ ጸጥ ለጥ ብሎ መገዛት ነው። የእነሱ የሰላም ትርጉም የሁሉም አሜን ብሎ መገዛት ነው። ሂትለርም አብዛኛውን ጊዜ ስለ ሰላም ይናገር ነበር። የንግግሩ ይዘት ግን ለሱ ፍላጐት አሜን ብሎ

መገዛት ነበር:: የአምባገነኖች ሰላም ከእሥር ቤት ሰላም ወይም ከመቃብር ሰላም የተለየ አለመሆኑን መገንዘብ ይገባል::

ሌላም አደጋ አለ:: ድብቅ ዓላማ ይዘው የሚደራደሩ አምባገነናዊ ወገኖች አንዳንድ ጊዜ የድርድሩን ዓላማዎችና የድርድሩን ሂደት ያመሰቃቅሉታል:: ግልጽ ፊር እንዳይዝ ያደርጉታል:: እዚህ ላይ የአምባገነኖች የሰላም ጥያቄ ከዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጥያቄ እጅጉን የተለየ እንደሆነ ማጤን ያስፈልጋል::

### 2.6. <u>ተስፋ የማድረግ ምክንያቶች</u>

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የተቃውሞ ኃይሎች መሪዎች በዴሞክራሲያዊው ትግል ተስፋ በማጣት ምክንያት እንዲደራደሩ የተገፋ ሊመስላቸው ይችላል:: ይሁን እንጂ የወቅቱ አቅም ማጣት ይለወጣል:: አምባገነኖች ዘላለማዊ አይደሉም:: በአምባገነን መሪዎች መዳፍ ውስጥ የወደቁ ሕዝቦች ደካማ በመሆን ጨቋኞቻቸው ለረጅም ጊዜ ኃይለኛ ሆነው የጭቆና ቀምበራቸውን እንደጫኑባቸው እንዲቀጥሉ መፍቀድ የለባቸውም:: አሪስጣጣሊስ አምባገነናዊ የጭካኔ ሥርዓት ዕድሜ ከማንኛውም ዓይነት የአገዛዝ ሥርዓት ያነሰ ነው ብሏል:: ዘመናዊው አምባገነናዊ አገዛዝም ለውድቀት የተጋለጠ ነው:: እንጉል ተግባራቸው እየባሰበት፣ የመጨቆኛ ኃይላቸውም እየደከመና እየተናደ ይሄዳል::

የቅርብ ጊዜ ታሪክ የአምባገነኖችን ለውድቀት ተጋላጭነትና በአንፃራዊ መልኩ በአጭር ጊዜ መውደቃቸውንም አሳይቶናል:: ለምሳሌ ኮሚኒስታዊ አምባገነንነትን ከፖላንድ፣ ከምሥራቅ ጀርመንና ከቼኮዝሎቫኪያ ለመጣል 10 ዓመታት /እ.ኤ.አ ከ1980-1990/ የጠየቀ ሲሆን በ1989 በሳምንታት ውስጥ ፍጻሜ አግኝቷል:: በኤልሳልቫዶርና በጓቲማላ ሕዝቦች ከጨፍጫፊ ወታደራዊ አምባገነን ገዥዎች ጋር ያካሄዱት ሰላማዊ ትግል እ.ኤ.አ በ1944 በሁለት ሳምንታት ውስጥ



በሕዝቡ አሸናፊነት ተጠናቋል:: በወታደራዊ ኃይሉ አይበገሬ የነበረው የኢራኑ ሻህ አገዛዝ በጥቂት ወራት ውስጥ አብቅቶለታል:: የፊሊፒንሱ አምባገነን ገዥ ፈርዲናንድ ማርቆስ እንዲሁ በህዝብ ሰላማዊ ትግል እ.ኤ.አ. በ1986 በሳምንታት ውስጥ አብቅቶለታል:: ትደግፈው የነበረችው አሜሪካም የማርቆስ ተቃዋሚዎች ጥንካሬያቸውን ሲያረጋግጡ ድጋፏን እርግፍ አድርጋ ትታዋለች:: በሌላ በኩልም እ.ኤ.አ. በኦገስት 1991 በሶቪየት ህብረት በአክራሪ ኮሚኒስቶች የተደረገው የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ በፖለቲካዊ ተቃውሞ ከሽፏል::

ቀደም ሲል የነበረው «የኃይል ዐመጽ የማካሄድ ትግል ቶሎ ውጤት ያስገኛል፣ ሰላማዊ ትግል ግን ውጤት ለማሳየት ረጅም ጊዜ ይፈልጋል» የሚለው አስተሳሰብ ከላይ ባየናቸው ሰላማዊ ትግሎች ውድቅ ሆኖአል:: በርግጥ ሰላማዊ ትግል ለውጥ ለማምጣት ብዙ ጊዜ የሚወስድበትም ሁኔታ ሊኖር ይችላል:: ሆኖም አምባገነኖችን ለመጣል የሚደረገው ሰላማዊ የሕዝብ ትግል በአንፃራዊ መልኩ በፍጥነት ውጤት እንደሚያስገኝ ታምኖበታል::

ለማሸነፍና ለመርታት በሚደረግ ትግል ውስጥ ድርድር ብቸኛው አማራጭ አይደለም:: በምዕራፍ አንድ ላይ እንደተገለፀው ሰላምንና ነፃነትን ለሚሹ ወገኖች ሌላም አማራጭ የትግል ስልት አለላቸው፣ እሱም ሰላማዊ ፖለቲካዊ ተቃውሞ ነው::

# ምዕራፍ ሦስት

## አቅም የሚገኘው መቼ ነው?

ለአንድ ሕዝብ ነጻነትንና ሰላምን ማግኘት ቀላል ሥራ አይደለም፡፡ ከፍተኛ ግብ መቀየስን፣ አደረጃጀትንና ዕቅድ መንደፍን ይጠይቀዋል፡፡ ከሁሉም በላይ ችሎታና አቅም ያስፈልገዋል፡፡ ዲሞክራቶች የራሳቸውን ችሎታ በብቃት መተግበር ሳይችሉ አምባገነን መሪዎችን ለማስወገድ መመኘት የለባቸውም፡፡

ታዲያ ይህ እንዴት ነው እውን መሆን የሚችለው? በምን ዓይነት አቅም ነው ዴሞክራሲያዊ ተቃዋሚ ኃይሎች አምባገነኖችን ከጦራቸው፣ ከፖሊስና ከስለላ ተቋሞቻቸው ጋር ከሥልጣን ለማውረድ የሚችሉት?

እነዚህን የፖለቲካዊ አቅም ማግኛ ጥያቄዎችን ለመመለስ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የ14ኛውን ክፍለ ዘመን የቻይና ተረት ማየት ይጠቅማል፡፡

ቹ በምትባል የቻይና ግዛት ውስጥ ዝንጀሮዎችን በማሠማራት የሚኖሩ አንድ አዛውንት ሰው ነበሩ፡፡ የሚተዳደሩትም ዝንጀሮዎቹ ከዚያም ከዚያም ለቃቅመው በሚያቀርቡላቸው ፍራፍሬ ነበር፡፡ ያገሬው ሰዎች የዝንጀሮዎች ጌታ ይሏቸዋል፡፡ ሁልጊዜ ጧት ጧት ዝንጀሮዎቹን በግቢያቸው ውስጥ ይሰበስቡና ከሁሉም ጠና ያለውን ዝንጀሮ መርጠው በማዘዝ ሌሎቹን በመምራት ወደጫካ ሄደው ከየዛፉ ላይ ፍራፍሬ ለቅመው እንዲያመጡ ያሠማሩዋቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ዝንጀሮ ካገኘው ፍራፍሬ ከአሥር አንዱን እጅ ለሰውዬው መስጠት ደንባቸው ነበር፡፡ ይህን ማድረግ የተሳነው ዝንጀሮ ግን በኃይል ይገረፋል፡፡ በመሆኑም ሁሉም ዝንጀሮዎች በከፋ ሁኔታ ይሰቃዩ ነበር፡፡ ግን አንዳቸውም የተቃውሞ ድምጻቸውን አሰምተው አያውቁም፡፡



አንድ ቀን አንዱ ትንሽ ዝንጀሮ «ለመሆኑ የፍራፍሬ ዛፎቹን የተከለና ያበቀለው ይህ አዛውንት ሰውዬ ነው?» በማለት ሌሎቹን ጠየቃቸው፡፡ «እሱ አልተከላቸውም፣ በተፈጥሮ የበቀሉና ያደጉ ናቸው፡፡» አሉት፡፡ «ካለ አዛውንቱ ፈቃድ እነዚህን ፍራፍሬዎች መውሰድ አንችልም?» አላቸው፡፡ «አዎ! እንችላለን» አሉት፡፡ አሁንም ቀጠለና ትንሹ ዝንጀሮ «ታዲያ ለምንድነው አዛውንቱ እጅ ላይ የወደቅነው?» «ለምንስ እሱን እናገለግላለን?» ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ ሁሉም ዝንጀሮዎች ነገሩ ተገልጾላቸው ባነኑ፡፡

በዚሁ ዕለት ማታ አዛውንቱን እንቅልፍ ሲወስዳቸው ዝንጀሮዎቹ ወደሚታጐሩበት ቦታ የሚወስዱትን መንገዶችና የሚታጐሩበትን ግቢ በሙሉ ያፈርሳሉ፡፡ ከዚያም እነሱም የሰበሰቡትንና አዛውንቱ ያከማቹትን ፍራፍሬ ጥርግርግ አድርገው በመውሰድ ወደ ገደላቸው ይሄዳሉ፡፡ ከዚያም እስከ መጨረሻው ወደ አዛውንቱ አልተመለሱም፡፡ አዛውንቱም በርሃብ ሞቱ ይባላል፡፡ /ይህ ተረት የተገኘው ዩ-ሊ-ዚ /እ.ኤ.አ. 1311-1375/ ካዘጋጀው መጽሐፍ ነው፡፡/

ታዲያ አንዳንድ መሪዎች ሕዝባቸውን በትክክለኛው መንገድ ሳይሆን እንደ ዝንጀሮዎቹ ጌታ በማታለል ያስተዳድራሉ፡፡ ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች የዝንጀሮ አሳዳሪው አዛውንት ዓይነት አይደሉም ወይ? አእምሮአቸው ልክ እንደማይሠራ የሚገነዘቡ አይደሉም፡፡ በመጨረሻም ሕዝቡ በማጭበርበር እንደሚገዙት ሲነቃባቸው ያ የሚያታልሉበት ዘዴ እንደሚከሽፍ አያውቁም፡፡

### 3.1. የአምባገነኖች የፖለቲካ ሥልጣን ምንጮች

ነገሩ ቀላል ነው፡፡ አምባገነኖች የሚገዙትን ሕዝብ ድጋፍ ይፈልጋሉ፡፡ ካለህዝቡ ድጋፍ የፖለቲካ ሥልጣናቸውን ባስተማማኝ

ሁኔታ ማረጋገጥ ይሳናቸዋል:: እነዚህ የፖለቲካ ሥልጣን ምንጮች የሚከተሉትን ያካትታሉ::

- ባለሥልጣን:- በሥልጣን ላይ ያለ መንግሥት ሕጋዊ ስለሆነ ለሱ መታዘዝ የሞራል ግዴታ ነው የሚለው በህዝቡ ዘንድ ያለ እምነት፣
- የሰው ኃይል:- ለገዥው መንግሥት የሚታዘዙት፣ የሚተባበሩት፣ ወይም ድጋፍ የሚሰጡት ሰዎች ቁጥር መበርከት ፣
- ሙያና ዕውቀት:- አንድን የተወሰነ ሥራ ለማከናወን በገዥው መንግሥት በኩል ያለው ፍላጐትና ይህን ለማከናወን የሚቀርቡት ሰዎች ወይም ቡድኖች መኖር፣
- የማይጨበጡ ረቂቅ ነገሮች:- ሰዎች ገዥዎቻቸውን እንዲታዘዙና እንዲደግፉ የሚገፋፏቸው ሥነ-ልቦናዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ነገሮች መኖር፣
- የቁሳዊ ነገሮች ምንጭ:- ገዥዎች ባገሪቱ ንብረት፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ የገንዘብ ምንጭ፣ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት፣ የመገናኛ ብዙሀንና የመገናኛ ዘዴዎች ላይ ያላቸው ቁጥጥር መጠን መስፋት፣
- ገዥው መንግሥት የሚፈልጋቸውን ፖሊሲዎቹን ተግባራዊ በማድረግ የግዛት ዘመኑን እንዲያራዝም አልታዘዝም፣ አልተባበርም በማለት የመምበርከክንና የእጅ መስጠትን ነገር አናደርገውም በሚሉት ሰዎች ላይ የሚጥለው ማዕቀብ፣ ቅጣት፣ ማስፈራራት፣ ጭቆናና የመሳሰሉት ናቸው::

እነዚህ ሁሉ የሥልጣን ምንጮች ገዥው መንግሥት በሚኖረው እንፃራዊ ተቀባይነት፣ በህዝቡ አሜን ባይነትና ታዛዥነት እንደዚሁም



ትብብር በሚያሳዩት ሰዎች ብዛትና በማህበራዊ ተቋማት ላይ የተመሠረቱ ናቸው::

ከህዝቡ የሚገኝ ሙሉ ትብብር፣ ታዛዥነትና ድጋፍ ገዥው የሚፈልጋቸው የሥልጣን ምንጮች እንዲበራከቱ ብሎም የሥልጣን አቅሙ እንዲጐለብት ያግዙታል::

በሌላ ወገንም ለአምባገነኖችና ለጨቋኞች የሚደረጉ ሕዝባዊና ተቋማዊ ትብብርን መከልከል ጨቋኝ መሪዎች የሚተማመኑባቸውን የሥልጣን ምንጮች ያደርቃል:: ካለነዚህ የሥልጣን ምንጮች አምባገነኖች ጠውልገው መርገፍ እንጂ ሊለመልሙ አይችሉም::

አምባገነኖች በተፈጥሯቸው እንደፈለጉ የሚያንቀሳቅሳቸውንና አቅማቸውን የሚጐዳ ድርጊትና ሀሳብ ሁሉ ከመጠን በላይ ያስጨንቃቸዋል፣ ያስበረግጋቸዋል፣ ያስደነግጣቸዋል:: በመሆኑም አልታዘዝ የሚላቸውን፣ አድማ የሚያደርግባቸውን፣ ወይም አልተባበር የሚላቸውን ወደማስፈራራትና ብሎም ወደ መቅጣት ያመራሉ:: ይሁን እንጂ አፈናና የጭካኔ እርምጃቸው ሁልጊዜ አሜን ባይነትንና ትብብርን አይወልድላቸውም::

ህዝቡ አፈና እየተካሄደበትም ቢሆን የሥልጣን ምንጫቸው ለረጅም ጊዜ እየተገደበ ወይም እየተቋረጠ ከቀጠለ በአምባገነኖች ዘንድ የመጀመሪያው ውጤት የነገሮች መመሰቃቀልና እርግጠኛ አለመሆን ስሜት ሊሆን ይችላል:: በመቀጠልም ግልጽ የሥልጣን መዳከም ይከተላል:: በጊዜ ሂደትም ሕዝቡ የገገርዎችን የሥልጣን ምንጮች ገድቦ የመያዙ ሁኔታ በአምባገነኖች ላይ የአቅም መሽመድመድን የሚያስከትል ሲሆን በመቀጠልም መፍረክረክን ያደርሳል:: ጨቋኙ መንግሥት የፖለቲካ ክስረትም ይገጥመውና ሥልጣኑ ቀስ በቀስ ወይም በፍጥነት እየሞተ ይሄዳል::

በማንኛውም መንግሥት የነጻነት ወይም የጭቆና መጠን ደረጃ ሕዝቦች ሲጨቁናቸው የመጣውን ኃይል ለመታገል ያላቸው አንፃራዊ ፈቃደኝነትና ችሎታ ነፀብራቅ ነው::

በተለምዶ ከሚታመንበት አመለካከት በተቃራኒም የፍጹማዊ አምባገነን መሪዎች ዕጣ ፋንታ በሚገዙት ህብረተሰብ ሁኔታ ላይ የሚወሰን ነው:: ካርል ዱቼ /በ1953/ የተባለው የፖለቲካ ሳይንቲስት እንደተናገረው፤

> *ፍጹማዊ የአገዛዝ ሥልጣን ጠንክሮ የሚዘልቀው በተደጋጋሚ በሥራ ላይ እስካልዋለ ድረስ ብቻ ነው:: ፍጹማዊ አገዛዝ በአጠቃላይ በህዝቡ ላይ በተደጋጋሚ በተግባር የሚውል ከሆነ በጠንካራነቱ ለመቀጠል ዕድል አይኖረውም:: ከሌሎቹ ያገዛዝ ሥርዓቶች ይልቅ ይህ ፍጹማዊ አገዛዝ ይበልጥ ሥልጣን ካስፈለገው የህዝቡን ታማኝነትና ታዛዥነት ይፈልጋል:: ቢያንስ ለሚፈልገው ድጋፍ ሁሉ የአብዛኛውን ፈጣን ምላሽ ማግኘት ያሻዋል::*

የ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የእንግሊዝ የህግ ንድፈ ሀሳብ ቀማሪ ጆን አውስቲን እንደገለፀው ደግሞ የአምባገነኖች ሁኔታ ከተጨቆኑ ህዝቦች ተቃውሞ ይገጥመዋል:: አውስቲን እንደገለፀው ህዝቡ አምባገነኑን አገዛዝ ለመደምሰስ ከተነሳሳና ይህንንም በማድረግ የሚደርስበትን ጭቆና ሁሉ ለመቋቋም ከወሰነ፣ አገዛዙና ደጋፊዎቹ፣ የውጭ ድጋፍ ቢኖርም ቅሉ፣ የተጠላ መንግሥት ዕድል መፈረካከስ ይሆናል:: ለተቃውሞ የወጡ ህዝቦች ቀድሞ ወደነበሩበት ታዛዥነትና እሺ ባይነት ፈጽሞ ሊመለሱ አይችሉም::

ከብዙ ጊዜ በፊት ኒኮላይ ማኪያቬሊ የሚባል አንድ መስፍን «አጠቃላይ ህዝቡን ጠላት ካደረገ ለደህንነቱ ዋስትና የለውም፤ የጭቆናና



የጭካኔ አገዛዙ በጠነከረ መጠን የአገዛዝ ሥርዓቱ እየተዳከመ ይሄዳል» ሲል አስገንዝቦ ነበር::

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ማነቃቂያ ምሳሌዎች በምዕራፍ አንድ ላይ በተዘረዘሩት በፖላንድ፣ በጀርመን፣ በቼክ፣ በስሎቫክና በሌሎችም ኮሚኒስት ሀገሮች ተግባራዊ ሆነው በአጠቃላይ ኮሙኒዝምን ከምሥራቅ አውሮጳ ለማንኮታኮት በቅተዋል::

የሕዝቦች ሰላማዊ ትግል የቅርብ ጊዜ ክስተት አይደለም:: እንዲያውም ከክርስቶስ ልደት በፊት ቢያንስ ፕሌቢያኖች ለሮማውያን ጌቶቻቸው ያደርጉት የነበረውን ትብብርና እሺ ባይነት ወደ አቋረጡበት 494 ዓመተ ዓለም /B.C/ ድረስ ይሄዳል:: የተጨቆኑ ሕዝቦች ሰላማዊ ትግል በተለያዩ ጊዜያት በእሲያ፣ በአፍሪካ፣ በአሜሪካ፣ በአውስትራሊያና በፖሲፊክ ደሴቶች እንዲሁም በአውሮጳ ተካሂዷል::

የመንግሥትን ሥልጣን እስከምን ደረጃ ድረስ መገደብ ወይም አለመገደብ ከሚወስኑት ዋና ነገሮች መካከል የሚከተሉት ሦስቱ ይጠቀሳሉ::

1. ሕዝቦች በመንግሥታት ሥልጣን ላይ ገደብ ለመጣል ያላቸው አንፃራዊ ፍላጐት፣
2. የሕዝቦች ነጻ ማህበራትና ተቋማት በጋራ የመንግሥትን የሥልጣን ምንጭ ለማቋረጥ ያላቸው አንፃራዊ ጥንካሬ፣
3. ሕዝቦች ለአምባገነኖች ፈቃደኝነታቸውንና ድጋፋቸውን ከመስጠት ለመታቀብ ያላቸው አንፃራዊ ብቃት ናቸው::

## 3.2. <u>የዲሞክራሲያዊ ሥልጣን ማዕከል</u>

ዲሞክራሲ የሰፈነበት ሕብረተሰብ አንዱ መለያው ነገር በውስጡ ከመንግሥት ጣልቃ ገብነት የፀዱ በጣም በርካታ መንግሥታዊ ያልሆኑ ቡድኖችና ተቋማት መኖር ነው:: እነሱም ለምሳሌ ቤተሰቦች፣

የሀይማኖት ተቋማት፣ የባህል ማህበሮች፣ የፖለቲካ ፖርቲዎች፣ የስፖርት ክበቦች፣ የኢኮኖሚ ተቋሞች፣ የሙያ ማህበራት፣ የተማሪዎች ማህበራት፣ የአካባቢ ማህበራት፣ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች፣ የሙዚቃ ቡድኖች፣ የሥነጽሑፍ ማህበራትና የመሳሰሉት ናቸው:: እነዚህ አካላት የተቋቋሙበትን ዓላማዎች ለማሳካትና የህብረተሰቡን ፍላጐቶች ለማሟላት ጠቃሚ ናቸው:: ይህ የሚሆነው ግን ከመንግሥት ቁጥጥር ነጻ ሆነው በህብረተሰቡ ፍላጐት ሲካሄዱ ነው::

እነዚህ አካላት በተጨማሪም ታላቅ የፖለቲካ ጠቃሜታ አላቸው:: ሰዎች የማህበር አባላቶቻቸውን አቅጣጫ ለማስያዝ የሚጥሩበትን ሁኔታ መፍጠርና ሌሎች ወገኖች ወይም መንግሥት ዓላማቸውን ለማስፈጸምና ተልዕኳቸውን ለማሳካት ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ እንዳያውካቸው የሚቋቋሙበት መድረክ ያገኙላቸዋል:: ከነዚህ ስብስቦች ውጪ የሆኑ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ከማንኛውም አቅጣጫ የሚደርስባቸውን ጥቃት ለመቋቋም ብቃት አይኖራቸውም::

እነዚህ ማህበራት ነጻነትና በራስ የመንቀሳቀስ መብታቸውን በአምባገነኖች ከተነጠቁ ሕዝቡ አለኝታ ቢስ ይሆናል:: በተጨማሪም ማህበራቱ አምባገነናዊ ቁጥጥር ከተጫናቸው፣ ወይም በቁጥጥር ሥር በዋሉ መሰል ማህበራት ከተተኩ የማህበራቱን አባላት መጨቆን ብቻ ሳይሆን በአካባቢ የሚገኙት የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ ይታፈናሉ::

በአንፃሩ እነዚህ አካላት ከመንግሥት ቁጥጥር ውጪ ሆነው ነፃነታቸው ተጠብቆ በራሳቸው የሚንቀሳቀሱ ከሆነ ጨቋኞችን ለመቋቋምና የፖለቲካ ተቃውሞ ለማድረግ ጠቃሚ መሣሪያዎች ናቸው:: ይህ እውን የሚሆነው ግን ሕብረተሰቡ ተቋማቱን በመጠቀም ሰፊ የፖለቲካ ተቃውሞ ማድረግ ሲችል ነው:: ከላይ እንደተገለፀው እነዚህ የኃይል ማዕከላት ሕዝቡ በጨቋኞች ላይ ከፍተኛ ግፊትና ተጽእኖ ማድረግ የሚችልበትን ተቋማዊ መሠረት ይጥሉለታል:: ለወደፊቱም ለነጻ ማህበረሰብ አስፈላጊ መዋቅሮች በመሆን ይጠቅማሉ:: ስለሆነም ቀጣይነታቸውና ዕድገታቸው ለነጻነት ትግሉ መኖር በቀዳሚነት የሚያስፈልጉ ናቸው::



አምባገነን መሪዎች እነዚህን የህብረተሰቡን ነጻ ተቋማት ማጥፋት ወይም መቆጣጠር ከቻሉ ተቃዋሚ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሌሎች አዲስ ነጻ ማህበራዊ ቡድኖችና ተቋማት መፍጠር መቻል አለባቸው:: ከተቻለም ከአምባገነኖች ቁጥጥር ያመለጡ ካሉ ወይም በከፊል ቁጥጥር ሥር የወደቁትን መልሶ ህዝቡን እንዲያገለግሉ ማድረግ መቻል ያስፈልጋል:: በ1956-57 በሃንጋሪ በተደረገው አብዮት ብዛት ያላቸው ደሞክራሲያዊ ካውንስሎች ተቋቁመውና ግንባር ፈጥረው ለሳምንት ያህል አስተዳደሩንና ተቋማትን በፌዴራላዊ ሥርዓት መርተውት ነበር:: ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ1980 መጨረሻ አካባቢ ፖላንድ ውስጥ ላብ አደሮች ሕጋዊ ዕውቅና የሌላቸው በርካታ የትብብር ቡድኖችን በማቋቋም ከመንቀሳቀሳቸውም ሌላ በህግ ተቋቁሞ ኮሚኒስቶች ይጠቀሙበት የነበረውን የሠራተኛ ማህበር መቆጣጠር ችለው ነበር::

በእርግጥ የትኞቹንም አምባገነኖች ከሥልጣን የማውረድ እንቅስቃሴ ሁኔታ ቀላል ተደርጐ የሚታይ አይደለም:: እያንዳንዱ ሙከራም የታለመለትን ግብ ላይመታ ይችላል:: እንቅስቃሴው ካለምንም ጉዳት የሚሄድ የአልጋ ባልጋ ጉዞም አይደለም:: አምባገነን መሪዎችና አጫፋሪዎቻቸው አሁንም ህዝቡ እንዲገብርና እንዲታዘዝ ለማድረግ መዋጋታቸውና የተቻላቸውን ያህል አደጋ ማድረሳቸው አይቀርም:: ምንም ይሁን ምን ህዝቡ ጠንክሮ በተቃውሞው ከገፋበት ማሸነፉ የማይቀር ነው:: አምባገነኖች የሕዝብን ትግል የማይቋቋሙበት የተወሰነ የጋራ ባህርይ አላቸው:: በጀመሩበት የአፈናና የጭቆና መንገድ ረጅም ርቀት መጓዝ አይቻላቸውምና::

# ምዕራፍ አራት

# አምባገነንኖች ደካማ ጐኖች አሏቸው

አምባገነኖች አብዛኛውን ጊዜ የማይበገሩ ይመስላሉ:: የሥለላ ተቋሞቻቸው፣ የፖሊስና ወታደራዊ ኃይሉ፣ እሥር ቤቱ፣ የሚያፍኑባቸው ቦታዎች እና ገዳይ ቡድኖቻቸው ሁሉ በጥቂት የአምባገነን ቁንጮዎች ቁጥጥር ሥር ያሉ ናቸው:: የሀገር ገንዘብ፣ የተፈጥሮ ሀብቶችና ምርቶች እንደተፈለገው እየተዘረፉ ፍላጐቶቻቸውን ለማስፈጸም ይበተናሉ::

በአንፃሩ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች አብዛኛውን ጊዜ ደካማ፣ ውጤተ ቢስ እና ምንም ኃይል የሌላቸው አቅመቢስ መስለው ይታያሉ:: የአምባገነኖችን አይደፈሬነትና የተቃዋሚ ኃይሎችን አቅመቢስነት አጋኖ የማየቱ ጉዳይ ውጤት ያለው ተቃውሞ ማካሄድን የማይሳካ አድርጐ መገመትን ያስከትላል:: እውነቱ ግን ይኸ አይደለም:: የማይበገሩ የሚመስሉት የሚበገሩበትን ሁኔታ ከሚከተለው ጥንታዊ የግሪክ አፈ ታሪክ መረዳት ይቻላል:: ታሪኩ እንዲህ ይነበባል::

## 4.1. የአቺሌን ተረከዝ መለየት

አቺሌ /Achilles/ የተባለው ጀግና ምንም ዓይነት ምት እንደማያቆስለውና ሰውነቱን ጦር እንደማይበሳው ይነገርለት ነበር:: እንደዚሁም ሊሆን የቻለው እናቱ በህፃንነቱ ስቲክስ በተባለው ምትሀታዊ /አስማታዊ/ ወንዝ ውስጥ ነክረውት ስለነበረ ከማንኛውም አደጋ እንደሚጠብቀው ይታመንበት ነበር:: ያም ሆኖ ግን ችግር ነበረበት:: ይኸውም፣ ውሃው ውስጥ ሲነከር ተረከዙን ተይዞ ስለነበረና ውሃው ተረከዙን ስላልነካው አስማቱ/ምትሀቱ ተረከዙን አይከላከለውም:: አቺሌ አድጐ ትልቅ ሰው በሆነ ጊዜ አይደፈሬ ሆኖ ታየ:: ከዕለታት አንድ ቀን



ከወታደሮቹ ጋር ሆኖ ጦርነት ይገጥማል:: በዚህን ጊዜ አንድ ምስጢር አወቅ ሰው አቺሌ የነበረበትን ድክመት ይናገርና የጠላት ወገን ወታደር ቀስቱን የምትህት መከላከያ ወደሌለው የአቺሌ ተረከዝ አነጣጥሮ በመተኰስ ይገድለዋል:: ይኸውና እስከዛሬም ድረስ ተጋላጭ የሆነውን ወይም መደፈር የሚችለውን የሰው አካል፣ ዕቅድ፣ ወይም ተቋም መከላከያ እንደሌለው ወይም ድክመቱ ከታወቀ «የአቺሌ ተረከዝ» በመባል ይጠራል::

ይህ መርህ ለአምባገነን መሪዎችም ያገለግላል:: ስለሆነም የአምባገነኖች ደካማ ጐን በውል ተለይቶ የሚታወቅ ከሆነና በዚሁ ድክመታቸው ላይ ትኩረት ከተደረገ በሰላማዊ ትግል በአጭር ጊዜና በአነስተኛ ጉዳት ማሸነፍ ይቻላል::

### በአብዛኛው ከአምባገነኖች ደካማ ጐኖች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ::

1. የአምባገነኖችን ሥርዓት ሞተር ሆነው የሚያንቀሳቅሱት በርካታ ሰዎች፣ ቡድኖችና ተቋማት ከተግባራቸው ይቆጠቡ ወይም እስከነጭራሹ እርግፍ አድርገው ይተው ይሆናል::
2. ቀደም ሲሉ የነበሩ ፖሊሲዎቻቸው ከወቅቱ ጋር የመጣጣምና ችግሮችን የመፍታት አስፈላጊነታቸውና ውጤታማነታቸው እየቀነሰ ሊመጣ ይችላል፣
3. ሥርዓቱ የተለመደ ተግባሩን በማከናወን ከአዳዲስ ክስተቶች ጋር በፍጥነት የመሄድ ችሎታው አነስተኛ ይሆናል::
4. በሀገሪቱ ላሉት ሥራዎች የተመደበው ሠራተኛና ሀብት ለአዳዲስ ፍላጐት በቀላል የሚገኝ አይሆንም፤

5. የበታች ሠራተኞች የበላይ አለቆቻቸውን እናስከፋለን ብለው ስለሚፈሩ ለአምባገነን መሪዎች ውሳኔና እርምጃ የሚጠቅሙ ትክክለኛና የተሟላ መረጃ አያቀርቡም::
6. የፖለቲካ ጽንሰ ሀሳባቸው ይሸረሸራል፤ እንዲሁም የሥርዓቱ ታሪክና ምልክት ሁሉ እየዋዠቀ ይሄዳል::
7. የሰዎችን አመለካከት ይስብ የነበረው ጠንካራ የፖለቲካ ጽንሰ ሀሳብ ህዝብ ድርቅ ብሎ ይከተለው ስለነበረው ትክክለኛ ሁኔታ ትኩረት እንዳይሰጥ ሊያደርገው ይችላል::
8. እያሽቆለቆለ ለሚሄደው የቢሮክራሲው ቀልጣፋነትና ብቃት ወይም የሚደረገው ከመጠን ያለፈ ቁጥጥርና ደንብ የሥርዓቱን ፖሊሲዎችና ተልዕኮ ውጤት አልባ ያደርጋቸዋል::
9. የተቋሞች ውስጣዊ ግጭቶችና የግለሰቦች ፉክክር እንደዚሁም ጥላቻ አምባገነኖችን መጉዳት ብቻ ሳይሆን እንቅስቃሴያቸውንም ያናጋባቸዋል::
10. ምሁራንና ተማሪዎች በሀገር ላይ በአምባገነኖች በሚጣለው ገደብ፣ እመቃና መመሪያ ሳቢያ አለመረጋጋት ይፈጠርባቸዋል::
11. በአጠቃላይ ሕዝቡ በሂደት ለአምባገነን መሪዎቹ ደንታ ቢስ፣ ዝም ብሎ ተመልካች ሊሆንና ብሎም በጠላትነት ሊቆም ይችላል::
12. ክልላዊ፣ መደባዊ፣ ባህላዊ ወይም ብሔራዊ ልዩነቶች አሳሳቢ ሊሆኑ ይችላሉ::
13. የአምባገነኖች የሥልጣን ተዋረድ ምንጊዜም ቢሆን መጠነኛና አንዳንድ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ አለመረጋጋት ይታይበታል:: ግለሰቦች የያዙትን የኃላፊነት ቦታ እንደያዙ አለመቆየት ብቻ ሳይሆን ከያዙት ቦታ ሊያድጉ ወይም ሊሻሩ ወይም ከነበሩበት ቦታ ተወግደው በሌላ ሊተኩ ይችላሉ::



14. የፖሊስ ወይም የጦር ኃይል ክፍሎች ከአምባገነን መሪዎቹ ፍላጐትና አመራር ውጪ የራሳቸውን ዓላማ ለማስፈጸም ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ:: የመንግሥት ግልበጣም ሊከተል ይችላል::
15. አምባገነናዊ ሥርዓቱ አዲስ ከሆነ ለመጠናከርና ሥር ለመስደድ ጊዜ ይፈልጋል::
16. ጥቂት ግለሰቦች በርካታ ውሳኔዎችን ስለሚሰጡ በሚዛናዊነት፣ በፖሊሲ አነዳደፍና በሚወሰዱ እርምጃዎች ስህተት መፈጸሙ አይቀርም::
17. አምባገነኖች ይህን አደጋ ለማስወገድና ቁጥጥራቸውንና ውሳኔ አሰጣጣቸውን ለሌሎች አሳልፈው ከሰጡ በማዕከላዊ ደረጃ ያለው የሥልጣን ቁጥጥራቸው እየተሸረሸረ ይሄዳል::

### 4.2. <u>የአምባገነኖችን ደካማ ጐን ማጥቃት</u>

እነዚህን የአምባገነኖችን ተፈጥሮአዊ ድክመቶች በማወቅና ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች «የአቺሌን ተረከዝ» መርህ ተከትለው በሰላማዊ ህዝባዊ ትግል ጭቆናን ሊያዳክሙና ብሎም ሊያስወግዱ ይችላሉ::

አምባገነኖች ኃይለኛ መስለው የሚታዩበት ሁኔታ ቢኖርም ደካማ ጐንም እንዳላቸው መታወቅ ይኖርበታል:: ለምሳሌም ያህል ውስጣዊና ተቋማዊ ቅልጥፍና ማጣት፣ ጤናማ ያልሆነ የእርስ በርስ ውድድር መኖር፣ በተቋሞች ውስጥ ባሉ ልዩ ልዩ ክፍሎችና በተቋሞች መካከል አለመግባባት መታየት የሚጠቀሱ ናቸው:: ቀስ በቀስም እነዚህ ድክመቶች የአምባገነን መሪዎችን የሥራ ውጤት ለአነስተኛና ለአዳዲስ ተቃውሞ ያጋልጣቸዋል:: የሚያቅዷቸው ሁሉ ተፈጻሚ መሆን ይሳናቸዋል:: ለምሳሌ ሂትለር በመጨረሻ ዘመኑ ቀጥታ ትዕዛዞቹ ተግባራዊ አይሆኑም ነበር:: ምክንያቱም ከእሱ በታች በተዋረዱ

የሥልጣን እርከኖች ላይ የነበሩ ሰዎች ትዕዛዙን ተግባራዊ ለማድረግ ፈቃደኛ ስላልነበሩና ሕዝቡም ስለማይታዘዛቸው ነበር።

ይህ ሲባል ግን አምባገነን መሪዎች ምንም ጥፋት ሣይሠሩና አደጋ ሳያደርሱ ባንድ ጊዜ ይወገዳሉ ማለት እንዳልሆነ መታወቅ አለበት። ለነጻነት የሚወሰድ ማንኛውም እርምጃ ችግርና ሥቃይ ሊያስከትል ይችላል። ጊዜም ይፈልጋል። ማንኛውም እርምጃ በማንኛ ውም ጊዜ አፋጣኝ ውጤት ላያስገኝ ይችላል። ሆኖም የአምባገነኖችን ደካማ ጐን ለይቶ በሰላማዊ መንገድ መታገሉ ጠንካራ በሆኑበት አቅጣጫና በኃይል ከመታገል የተሻለና ፈጣን ውጤት ሊያስገኝ ይችላል። ታዲያ ይህ ትግል እንዴት ይካሄድ? ነው ጥያቄው።



# ምዕራፍ አምስት

## አቅምን በሥራ ላይ ማዋል

ምዕራፍ አንድ ላይ እንደተመለከትነው ከአምባገነን ገገርዎች ጋር የሚደረገው ትግል በጦር መሣሪያ እንዲሆን ሲወሰን፣ አምባገነኖች ደካማ በሆኑበት ሳይሆን በመሣሪያ አቅርቦት፣ በጦር መሣሪያ ቴክኖሎጂና በመሣሰሉት እጅግ ጠንካራ በሆኑበት መንገድ መፋለም ስለሚያስከትል በአንጻራዊነት ተቃዋሚዎችን በግልፅ ይጐዳቸዋል። በመሆኑም ምንጊዜም ቢሆን አምባገነን መንግሥታት በመስኩ የተሻለ አቅም ይኖራቸዋል። አምባገነኖችን ለመመከት በውጪ ኃይሎች ላይ መተማመን ያለውን አደጋም ተመልክተናል። በምዕራፍ ሁለት ደግሞ አምባገነኖችን ለማስወገድ ድርድር ያለውን ጠቀሜታ መርምረናል።

እንዲህ ከሆነ ለተቃዋሚዎች ግልፅና እንፃራዊ ጠቀሜታ ያላቸውና የታወቁ የአምባገነኖችን ደካማ ጐኖች ሊያባብሱ የሚችሉ ምን ምን ዘዴዎች አሉን? በምዕራፍ ሦስት ውስጥ እንደተመለከተው በፖለቲካ መርህ ላይ የሚመሠረቱ ምን ምን ሥልቶችን መተግበር ይቻላል? ያለው አማራጭ ፖለቲካዊ ተቃውሞ ነው።

ፖለቲካዊ ተቃውሞ የሚከተሉት ባህርያት አሉት:-

- የትግሉ ውጤት አምባገነኖች በሚመርጡት የትግል ሥልት አይወሰንም፣
- አገዛዙ መቋቋም አይችልም፣
- የአምባገነኖችን ደካማ ጐን ባልተለመደ ሁኔታ ከማባባሱም በላይ የኃይል ምንጫቸውን ያሟጥጠዋል፣
- ተግባር ላይ ሲውል እንዳስፈላጊነቱ በማስፋት ወይም በማጥበብ በተፈለገው ዓላማ ላይ እንዲያተኩር ለማድረግ ይቻላል፣

- አምባገነኖች የትግሉን ዘዴ ተረድተው የሚወስዱት እርምጃ የባሰ ስህተት ላይ ይጥላቸዋል፣
- የጥቂቶችን አገዛዝ ፍፃሜ ለማቃረብ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ ማህበራዊ ቡድኖችንና ተቋሞችን በብቃት ለመጠቀም ያስችላል፣
- በህብረተሰቡ ውስጥ ዲሞክራሲን ለማስረፅና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ይበልጥ ለማጠናከር በሚያስችል ሁኔታ ውጤታማ የሆነ የሥልጣን ክፍፍል ለማዳረስ ይረዳል::

## 5.1. የሰላማዊ ትግል አካሄድ

እንደወታደራዊ አቅም ሁሉ ሰላማዊ የፖለቲካ ተቃውሞም ተቃዋሚው ኃይል የተለያየ እርምጃ እንዲወስድ ከመገፋፋት ጀምሮ ለግጭቶች ሰላማዊ መፍትሄ ለመፈለግ ወይም አምባገነን አገዛዝን ለማፍረክረክ ሊያገለግል ይችላል:: ይሁንና የፖለቲካ ተቃውሞ ከኃይል እርምጃ ፍጹም ልዩ በሆነ አውድ ውስጥ የሚሠራ ነው:: ሁለቱም ዘዴዎች መታገያዎች ቢሆኑም የሚጠቀሙባቸው ሥልቶችና ውጤቶችም ይለያያሉ:: የኃይል አማራጭ መንገዶቹና ውጤቶቹም በሚገባ የታወቁ ናቸው:: ቁሳዊ የጦር መሣሪያዎች የሰውን ልጅ ለማሠቃየት፣ ለመጉዳት፣ ለመግደልና ለማውደም ይውላሉ::

ሰላማዊ ትግል ከአመፅ የበለጠ ውስብስብና የተለያዩ ሥልቶችን የሚጠቀም ነው:: ሰላማዊ ትግል የህብረተሰቡንና የተቋማትን ሥነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ይካሄዳል:: እነዚህ ተቃውሞዎችም ሥራ ማቆም፣ ትብብር መንፈግ፣ ድጋፍ መንሳት፣ ማማረር እና የህዝብን ኃይል ማሳየት በሚሉ የተለያዩ ስሞች ይታወቃሉ:: ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው መንግሥታት ህዝብን ሊያስተዳድሩ የሚችሉት ህብረተሰቡና ተቋማቱ



ሲተባበሯቸው፣ ሲታዘዟቸውና ሲያከብሯቸው ብቻ ነው:: ከኃይል እርምጃ ይልቅ የፖለቲካ ተቃውሞ እነዚህን የመሳሰሉ የመንግሥት የሥልጣን ምንጮችን ለማድረቅ የተለየ ተስማሚነት አለው::

## 5.2. ሰላማዊ የትግል መሣሪያዎችና ዲሲፕሊን

ያልታሰበባቸው የፖለቲካ ተቃውሞዎች ተደጋጋሚ ስህተት የሥራ ማቆምና ሰላማዊ ሰልፍን በመሳሰሉ አንድ ወይም ሁለት ዘዴዎች ላይ ብቻ መተማመናቸው ነው:: እንደውነቱ ከሆነ የተቃውሞ አመራር ቀያሾች እንደአስፈላጊነቱ በተወሰነ ጉዳይ ላይ በማተኮር ወይም በስፋት በመለጠጥ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ በርካታ የተቃውሞ ዘዴዎች አሉ::

በአሁኑ ጊዜ ከሁለት መቶ በላይ የተለያዩ ሰላማዊ የተቃውሞ ዘዴዎች ተለይተው የሚታወቁ ሲሆን ከዚህም ይበልጥ እንደሚኖሩ ይገመታል:: እነዚህም ዘዴዎች በሦስት ዓበይት ክፍሎች ይመደባሉ:: እነሱም፣ ተቃውሞና ማግባባት፣ ትብብር መንፈግ፣ እንደዚሁም ጣልቃ መግባት ናቸው:: የተቃውሞና ማግባባት ዘዴ ሰልፍን፣ ጉዞንና ልዩ የተቃውሞ ቀንን /53 ዓይነት ዘዴዎች/ ጨምሮ ባመዛኙ ለተምሳሌትነት የሚከናወኑ ናቸው:: ትብብር መንፈግ ደግሞ በሦስት ንዑሳን ክፍሎች ይመደባል:: እነሱም፣

1. ማህበራዊ ትብብር መንፈግ /15 ዓይነት ዘዴዎች/፣
2. ግንኙነት ማቋረጥንና /26 ዓይነት ዘዴዎች/ ሥራ ማቆምን /22 ዓይነት ዘዴዎች/ ጨምሮ የኢኮኖሚ ትብብር መንፈግ፣
3. የፖለቲካ ትብብር መንፈግ /38 ዓይነት ዘዴዎች/:: ሰላማዊ በሆነ መንገድ በሥነ-ልቦናዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ በሆነ ዘዴ ጣልቃ መግባትና ፈጣንና ሰላማዊ በሆነ መንገድ አንድን ነገር በቁጥጥር ሥር ማዋል እንደዚሁም

ከመንግሥት መዋቅር በተነጻጻሪ ራስን ማደራጀት /41 ዓይነት ዘዴዎች/ የመጨረሻው ዘዴ ነው:: /195 የእነዚህ ዘዴዎች ዝርዝር በመፅሀፉ አባሪ ተደርጓል::/

በጥንቃቄ የተመረጡ፣ ያለማቋረጥ በሥፋት ሥራ ላይ የሚውሉ ለትግሉ ግብ አግባብ የሆኑ ታክቲኮች ተጣጥመው በሠለጠኑ ሲቪሎች በሥራ ከተተረጐሙ በማንኛውም ህገወጥ አገዛዝ ላይ የከፋ ችግር መፍጠራቸው አይቀርም:: ይህም ለማናቸውም አምባገነኖች ሁሉ ሊሠራ የሚችል ነው::

ከወታደራዊ የትግል ዘዴ በተለየ ሁኔታ ሰላማዊ የትግል ዘዴዎች በቀጥታ በአንገብጋቢ ችግሮች ላይ እንዲያተኩሩ ለማድረግ ይቻላል:: ለምሳሌ ያህል የአምባገነኖች ጉዳይ የፖለቲካ ጉዳይ በመሆኑ ፖለቲካዊ የሆኑ ሰላማዊ የትግል ዘዴዎች ሥራ ላይ መዋላቸው ወሳኝ ይሆናል:: ይህም የአምባገነኖችን ህጋዊነት አለመቀበልና ትብብር መንፈግንም ይጨምራል:: ትብብር መንፈግ በተመረጡ የመንግሥት ፖሊሲዎች ላይ እንዲያተኩር ማድረግም ይቻላል:: አንድን ነገር መግታትና ለተወሰነ ጊዜ ማሰናከል እንዳስፈላጊነቱ በፀጥታና እንዲያውም በምስጢር ሊፈፀም የሚችል ሲሆን፣ እንደሁኔታው ደግሞ ይፋ የሆነ እምቢተኝነትና የአደባባይ ተቃውሞ ሊደረግና እንደዚሁም ሰላማዊ ሰልፎችና የሥራ ማቆም አድማዎች በግልፅ ሊካሄዱ ይችላሉ::

በሌላ በኩል ደግሞ ሥልጣን ላይ ያለው አምባገነን መንግሥት ለኤኮኖሚያዊ ግፊቶች የሚንበረከክ ቢሆን ወይም የብዙው ህዝብ ብሶት ኤኮኖሚያዊ ቢሆን ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ከመግዛት መታቀብ ወይም ሥራ ማቆም ተመራጭነት ያላቸው የትግል ዘዴዎች ይሆናሉ:: አምባገነኑ መንግሥት ኤኮኖሚያዊ ሥርዓቱን ለግል ጥቅሙ ለማዋል የሚያደርገው ጥረት ውስን በሆኑ የሥራ ማቆም አድማዎችና ሥራን ማቀዝቀዝ እንደዚሁም የቁልፍ ሙያተኞች እምቢታና በሥራ



ገበታቸው ላይ አለመገኘት በእጅጉ ይጉዳዋል:: በማምረቻ ድርጅቶች፣ በትራንስፖርት ተቋማት፣ በጥሬ ዕቃ አቅርቦትና በምርት ማከፋፋያዎች ቁልፍ ቦታዎች የተለያዩ የሥራ ማቆም አድማዎች ሊደረጉ ይችላሉ::

በአንዳንድ የሰላማዊ የትግል ዘዴዎች የሚሳተፉ ሰዎች ኑሯቸውን ከመሠረቱበትና ከለመዱት ሥራ የተለየ ድርጊት እንዲያከናውኑ ይጠበቅባቸዋል:: ለምሳሌ ያህል በራሪ ወረቀቶችን ማሰራጨት፣ በህቡዕ በሚሠራ የህትመት ሥራ መሳተፍ፣ የረሀብ አድማ ማድረግ ወይም በመንገድ ላይ መቀመጥ ሊሆን ይችላል:: በአስገዳጅ ሁኔታ ትግሉ ካልጠየቀ በስተቀር እነዚህ የትግል ዘዴዎች ለአንዳንድ ሰዎች ሊያስቸግሯቸው ይችላሉ::

በሌሎች ሰላማዊ የትግል ዘዴዎች ግን በትግሉ የሚሳተፉ ሰዎች ከሞላ ጐደል የተለመደ ዕለታዊ ተግባራቸውን ሊያከናውኑ ይችላሉ:: ለምሳሌም ያህል በሥራ ማቆም ፋንታ በሥራ ገበታቸው ላይ ሊገኙ ይችላሉ:: ነገር ግን ሆነ ብለው ሥራቸውን ያቀዘቅዛሉ ወይም ውጤታቸው ከተለመደው ዝቅ እንዲል ያደርጋሉ:: ከዚህም በላይ ሆነ ብለው ተደጋጋሚ የሥራ ስህተቶች ይፈፅማሉ:: አንዳንድ ጊዜም ሆነ ብለው በህመም በማሳበብ ለመሥራት እንደማይችሉ ያሳውቃሉ ወይም እምቢ አልሠራም ሊሉ ይችላሉ:: ከዚህም በላይ የፖለቲካ ይዘት ባላቸው ሀይማኖታዊ በዓላት ላይ ተሳታፊ ይሆናሉ:: ህፃናትንም ከአምባገነኑ መንግሥት ፕሮፓጋንዳ አዘል ትምህርት ለመጠበቅ ሲባል በቤት ውስጥ ሊያስተምሩ ይችላሉ:: ግዴታ ባለባቸው አንዳንድ ድርጅቶች ውስጥ ላለመሣተፍ እምቢ ማለት ሌላው አማራጭ ነው:: እነዚህ የትግል ዘዴዎች ሰዎች የዕለት ኑሯቸውን ለማሸነፍ ከሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ጋር መመሳሰል ወይም ከዕለት ኑሯዋቸው ጋር የሚኖራቸው መቀራረብ ብዙ ሰዎች ከአምባገነኖች ነጻ

የማውጣቱን ትግል ለማፋጠን የሚያደርጉትን ተሳትፎ የበለጠ ቀላል ያደርገዋል::

ሰላማዊ ትግልና የኃይል አመጽ በተለያዩ መሠረታዊ መንገዶች የሚካሄዱ ስለሆነ በፖለቲካ ትግል ጊዜ የሚቀላቀል የኃይል ተቃውሞ ትግሉን አምባገነኖች ይበልጥ የበላይነት ወደ አላቸው የትጥቅ ትግል የሚቀይረው ስለሆነ አጥፊ ነው:: ሰላማዊ አመጽ ለስኬት ቁልፍ ስለሆነ የአምባገነኖችና የወኪሎቻቸው ትንኮሳና ጭካኔ ቢፈታተነውም ዲሲፕሊኑ መጠበቅ ይኖርበታል::

ዝቅ ብለን እንደምንመለከተው ከኃይል እርምጃ ይልቅ በሰላማዊ ትግል ላይ ማተኮር አራቱን የሰላማዊ ትግል አሠራር መርሆዎች ያፋጥናል:: ሰላማዊ ትግል ለፖለቲካ ጅዋጅዌ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው:: አገዛዙ በሰላማዊ ታጋዮች ላይ የሚከተለው ፍፁም የሆነ የኃይል እርምጃ በአገዛዙ ደጋፊዎችና በሶስተኛ ወገኖችም ጭምር የፖለቲካ ድጋፍ ከማስገኘቱም በላይ በባለሥልጣናት ላይ ሽብር ይለቅባቸዋል::

ይሁንና አልፎ አልፎም ቢሆን በአገዛዙ ላይ የሚሰነዘር የኃይል እርምጃ ሊያጋጥም ይችላል:: ህዝቡ በአገዛዙ ላይ ያለው ተስፋ መቁረጥና ጥላቻ ወደ ኃይል እርምጃ ሊለወጥ ይችላል ወይም ደግሞ የተወሰኑ ቡድኖች ሰላማዊ ትግል ያለውን ጠቀሜታ ቢገነዘቡም እንኳ የኃይል አማራጩን ለመተው ፈቃደኞች ላይሆኑ ይችላሉ:: በመሆኑም ሰላማዊ የፖለቲካ እምቢተኝነት ችላ ሊባል አይገባውም:: ይሁንና፣ እስከ ተቻለ ድረስ የኃይል እርምጃውን ከሰላማዊ ትግል መለየት አስፈላጊ ነው:: ይህም በመልከዓ ምድር፣ በተለያዩ የህዝብ ቡድኖች፣ በጊዜና ከአንገብጋቢ ጉዳዮች አንፃር ተገናዝቦ መታየት ይኖርበታል:: ይህ ካልሆነ ግን የኃይል አማራጭ መጠቀም ይበልጥ ውጤታማና ኃያል በሆነው የፖለቲካ እምቢተኝነት ላይ መጥፎ ውጤት ያስከትላል::



ታሪካዊ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በፖለቲካ እምቢታ ላይ ሙትና ቁስለኞች የማይታጡ ቢሆኑም በጦር መሣሪያ ትግል ከሚያጋጥመው ጉዳት እጅግ ያነሰ ነው:: ይበልጡንም ይህ ዓይነቱ ሰላማዊ ትግል ማለቂያ ለሌለው የግድያና ጭካኔ ዑደት አስተዋፅዖ አያደርግም::

ሰላማዊ ትግል የመንግሥትን ኃይልና የኃይል አገዛዝ መናቅን ወይም አለመፍራትን ይጠይቃል:: ፍርሀትን ማስወገድ ወይም መቆጣጠር አገዛዙ በህዝቡ ላይ የጫነውን ኃይል ለማጥፋት ቁልፍ ጉዳይ ነው::

## 5.3. ግልፅነት፣ ምስጢራዊነትና ፅናት

ምስጢራዊነት፣ ማሳሳትና/ማደናገር/ ድብቅ ሴራ ለሰላማዊ ትግል ብርቱ ፈተናዎች ናቸው:: የአገዛዙ ፖሊስና የደህንነት ኃይሎች የሰላማዊውን ትግል አቅጣጫዎችና ትግሎች እንዳይደርሱበት ማድረግም ቀላል አይደለም:: ከትግሉ ሂደት አንፃር ምስጢራዊነት መነሻው ፍርሀት ብቻ ሳይሆን ለፍርሀት መኖር አስተዋፅኦ ከማድረጉም በላይ የመቃወም መንፈስንም ይገድላል፣ በትግሉ የሚሳተፉ ሰዎችን ቁጥርም ውሱን ያደርጋል:: ከዚህም በላይ ማን ለጠላት መረጃ እንደሚያቀብል ወይም ማን የምስጢር ተከታታይ እንደሆነ በትግሉ ሂደት አግባብ ሳልሆነ ጥርጣሬና ለፈጠራ ወንጀል መፈብረክ አስተዋፅዖ ማድረጉ አይቀርም:: በተጨማሪም ምስጢራዊነት ሰላማዊ ትግሉ በሰላም መቀጠሉን ሊጐዳው ይችላል:: ከዚህ በተቃራኒ በትግሉ ሂደት ሊፈፀሙ የታሰቡና የታቀዱ ጉዳዮችን በሚመለከት የግልፅነት መኖር ተቃራኒ ውጤት የሚኖረው ብቻ ሳይሆን የተቃውሞ ትግሉ እጅግ ኃያል እንደሆነ ለመገመት የሚያስችል አስተዋፅዖ ይኖረዋል:: ይሁንና ጉዳዩ ከዚህ ይበልጥ ውስብስብና አንዳንድ የትግሉ ሂደቶች ምስጢራዊነት

ሊኖራቸው እንደሚገባም ያመላክታል:: በጉዳዩ ላይ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ስለ ሰላማዊ ትግል ሂደትና ስለአምባገነኖች የስለላ ዘዴ ከልዩ ልዩ ሁኔታዎች አንፃር በቂ መረጃ ኖሯቸው ግምገማ ሊያደርጉ ይገባል::

ከፍተኛ ምስጢራዊነት ሊጠበቅላቸው ከሚገባ ጉዳዮች መካከልም ህቡዕ ጽሁፎችን ማዘጋጀት፣ ማተም፣ ማሠራጨት፣ በሀገር ውስጥ የሚካሄድ የሬድዮ ሥርጭትና ስለአምባገነኑ መንግሥት አሠራር የሚሠባሰቡ መረጃዎችን የሚመለከቱ ናቸው:: በሰላማዊ ትግል በሁሉም ደረጃዎች ከፍተኛ የባህርይ ፅናት አስፈላጊ ነው:: ፍርሀትን ማስወገድና የሰላማዊ ትግል ዲሲፕሊንን መጠበቅ ዘወትር አስፈላጊ ናቸው:: አንድ ተፈላጊ ለውጥ ለማምጣትም ብዙ ሰዎች በየጊዜው ሊያስፈልጉ እንደሚችሉ መዘንጋት የለበትም:: ይሁንና እነዚህ ወገኖች በባህርይ ፅናታቸው የሚመረጡ አስተማማኝ ተሳታፊዎች መሆን አለባቸው::

## 5.4. <u>የኃይል አሰላለፍን መቀያየር</u>

የፖለቲካ እምቢተኝነት የሚካሄድበት ትግል በማያቋርጥ ሁኔታ ልዩ ልዩ ደጋፊና አደናቃፊ እንቅስቃሴዎች እንደሚኖሩ የፖለቲካ ትግል ቀያሾች መገንዘብ ይኖርባቸዋል:: ማናቸውም ነገር ቋሚ ሊሆን አይችልም:: አንፃራዊም ሆኑ ፍፁማዊ የኃይል አሰላለፎች በማያቋርጥና ፈጣን ለውጦች ውስጥ የሚያልፉ ናቸው:: ይህም የሚሆነው የማያቋርጥ ጭቆና ቢኖርም ቅሉ የትግሉ ተሳታፊዎች በሚያካሂዱት ያልተቋረጠ ሰላማዊ አመፅ ምክንያት ነው::

በዚህ ዓይነቱ የትግል ሂደት በተፋላሚዎች መካከል የሚኖረው የኃይል መዋዠቅ በኃይል ከሚደረግ አመፅ ይልቅ እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ በቅፅበት የሚካሄድ ዓይነተ ብዙና በፖለቲካ ረገድ ጉልህ ውጤቶች የሚያስገኝ ነው:: በእነዚህ የኃይል መዋዠቆች ምክንያት የሰላም ታጋዮች የሚያካሂዱት ትግል ከጊዜውና ከቦታው ርቀው



የሚሄዱ ውጤቶች ይኖሩታል:: የእነዚህ ውጤትም አንዱን ወይም ሌላውን ተፋላሚ ቡድን ሊያጠናክር ወይም ሊያዳክም ይችላል::

ከዚህም በተጨማሪ ሰላማዊው የትግል ቡድን በሚያደርጋቸው ግፊቶችና ተፅዕኖዎች በተፋላሚው ቡድን ላይ በእጅጉ አንፃራዊ የሆነ ጥንካሬ ላይ ዝቅ ወይም ከፍ የማድረግ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊፈጥር ይችላል:: ለምሳሌም ያህል ዲሲፕሊን ያለውና ቆራጥ የሆነ የሰላም ትግል በአምባገነኖች ጭካኔ አንፃር ውጥረትን፣ መረበሽን፣ ዕምነት ማጣትን፣ ብሎም በባሰ ሁኔታ በአምባገነኑ መንግሥት ሠራዊት መካከልና በህዝቡ ውስጥ አመፅ ሊቀሰቅስ ይችላል:: ይህ ተቃውሞም አምባገነኑን መንግሥት ለዓለም ህብረተሰብ ውግዘት ሊያጋልጠው ይችላል:: ከዚህም በተጨማሪ ጥንቃቄ የተሞላበት፣ በዲሲፕሊን የተመራና የማያቋርጥ የፖለቲካ ተቃውሞ በዝምታ ለአምባገነኖች ድጋፍ የሚሰጡ ወይም በትግሉ ውስጥ አቋም ያልያዙ የህብረተሰብ ክፍሎች በይበልጥ በትግሉ ዙሪያ እንዲሰባሰቡ ሊያደርግ ይችላል::

## 5.5. <u>አራቱ የለውጥ መንገዶች</u>

ሰላማዊ ትግል በአራት መንገዶች ለውጥ ያመጣል:: እነሱም:- የመቀየር/መለወጥ/፣ መቻቻል፣ ሰላማዊ አስገዳጅነትና የጠላት መፍረክረክ ናቸው:: የመጀመሪያው መንገድ ግን የሚከሰትበት አጋጣሚ ዝቅተኛ ነው:: የጨቋኙ መንግሥት አባላት ሥርዓቱ በቆራጥ ሰላማዊ ታጋዮች ላይ የሚያደርሰው ሥቃይና ጭቆና ሲቀሰቅሳቸው ወይም እነዚህ ታጋዮች የቆሙለት ዓላማ ፍትሀዊ ነው ብለው ሲያምኑ ትግሉን ሊቀላቀሉ ይችላሉ:: ይህም አቋምን የመቀየር /የመለወጥ/ መንገድ ይባላል:: እንደዚህ ዓይነቱ የመለወጥ ሁኔታ አልፎ አልፎ ቢያጋጥምም ከቁጥር የማይገባና በአብዛኞቹ ግጭቶችም ጨርሶ የማያጋጥም ወይም በሥፋት የማይታይ ነው::

ይበልጡኑ፣ ብዙ ጊዜ ሰላማዊ ትግል የግጭቱንና የህብረተሰቡን ሁኔታ በመቀየር ተቃዋሚው ወገን የፈለገውን ነገር በቀላሉ እንዳያደርግ ያስገድደዋል:: ይህ ዓይነቱ ለውጥም የሚከተሉት ሦስቱ መንገዶች እንዲፈጠሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል:: እነሱም መቻቻል፣ ሰላማዊ አስገዳጅነትና የጠላት መፍረክረክ/መበታተን/ ናቸው:: ከእነዚህ የትኞቹ እንደሚከሰቱ የሚወስነው አንፃራዊና ፍፁማዊ የኃይል ተዛምዶ ፍርርቅ ለዲሞክራቶች ሲያደላ ነው::

የሚነሱት ጉዳዮች መሠረታዊ ካልሆኑ ተቃዋሚዎች በተወሰነ ዘመቻ የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሆነው አይገመቱም:: የተፋላሚ ኃይሎች ትግል የኃይል ሚዛኑን በተወሰነ ደረጃ ከለወጠው ግጭቱ በድርድር፣ ልዩነቶቹን በማጥበብ፣ ወይም በመቻቻል ሊደመደም ይችላል:: ይህ አካሄድ የመቻቻል መንገድ ይባላል:: ለምሳሌ በብዙ የሥራ ማቆም አድማዎች የሚፋጠጡት ሁለቱም ወገኖች ሁሉንም ዓላማዎቻቸውን ባያሟሉም የተወሰኑትን በዚህ መንገድ ሊፈቱ ይችላሉ:: መንግሥትም ውጥረትን በማላላት፣ ተገቢ ሊመስሉ የሚችሉ ሁኔታዎችን እንደሚቀበል ለህብረተሰቡ ለማሳየት ወይም የመንግሥቱን ዓለማቀፍ ገፅታ ለማሻሻል ስለሚጠቅመው እንደበጐ ውጤት ይመለከተዋል:: ስለሆነም በድርድር ሊፈቱ የሚችሉ ጉዳዮችን በመምረጥ ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል:: ይህ መንገድ ያለጥርጥር አምባገነኖችን ከሥልጣን ለማውረድ ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱ አይደለም::

ሰላማዊ ትግል ከቅየራና መቻቻል የለውጥ መንገዶች ይበልጥ ኃያልና አስተማማኝ ነው:: ምልዓተ ህዝቡን ያሳተፈ ትብብር መንፈግና የፖለቲካ እምቢተኝነት ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን በተለይም የኃይል ግንኙነትና አሰላለፍን በመቀየር አምባገነኖች ያላቸውን የኤኮኖሚ፣ የማህበራዊና የፖለቲካዊ የበላይነት በማሳጣት ህብረተሰቡን



ከቁጥጥራቸው ውጪ ያደርግባቸዋል:: የአምባገነኑ መንግሥት የጦር ኃይሎችም አስተማማኝ ስለማይሆኑ ተቃማዊዎችን ለመጨፍለቅ የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ ከማይቀበሉበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ:: የአምባገነኑ መንግሥት መሪዎች በነበራቸው አስተሳሰብ ሥልጣን ላይ ቢቆዩም ሥራቸውን ለመሥራት ግን አቅም አይኖራቸውም:: ይህም ሰላማዊ የሆነ ማስገደድ ሊባል ይችላል::

በአንዳንድ ያፈነገጡ አጋጣሚዎች በሰላማዊ መንገድ የማስገደድ ሁኔታዎች ትግሉን ይበልጥ ወደፊት ሲገፉና ውጤቶቹም የላቁ ሊሆኑ ይችላሉ:: የአምባገነኑ መንግሥት አመራር አቅም ስለሚያጣ የትዕዛዝ ሰንሰለቱ ሽባ ይሆናል:: ተቃዋሚዎች በራሳቸው አመራር ትብብር የመንፈግና የመቃወም ድርጊት እየተሟላ ስለሚሄድ አምባገነኖች የይስሙላ ቁጥጥር እንኳ ያጣሉ:: መንግሥታዊ ቢሮክራሲውም ላለቆቹ መታዘዝ ያቆማል:: ሠራዊቱና ፖሊስም ያምፃሉ:: አምባገነኑን መንግሥት በመደገፍ የሚታወቁ የህብረተሰብ ክፍሎችም አመራሩን በመካድ ለመምራት መብት እንደሌለው በይፋ መናገር ይጀምራሉ:: በመሆኑም የነበረው ድጋፍና መታዘዝ ብትንትኑ ይወጣል:: ስለሆነም አራተኛው የለውጥ መንገድ ማለትም፣ የገዢው ወገን ከነሥርዓቱ ይበታተናል የሚለው መርህ ተግባራዊ ሲሆን አገዛዙ እጅ ለመስጠት እንኳ አቅም ያንሰዋል:: በመሆኑም አምባገነኑ መንግሥት ይበተናል::

ከአምባገነኖች ነጻ የሚያወጣ ትግል ሲታቀድ እነዚህ አራት የለውጥ መንገዶች በአእምሮ መያዝ አለባቸው:: አንዳንድ ጊዜ እነዚሀ የለውጥ መንገዶች የሚሰሩት በአጋጣሚ ነው:: ይሁንና ከነዚህ መንገዶች አንዱን ወይም ይበልጡን ለአንድ ግጭት መፍቻ መንገድ እንዲውሉ ሲሞከር ተጨባጭና እርስ [illegible] የሚደጋገፉ ወደ ግብ መቃረቢያ ዘዴዎችን ለመቀየስ ያስችላሉ:: ይህም ማለት አንድ መንገድ ለመምረጥ ብዙ ነገሮች ማለትም የተፋላሚ ወገኖች ፍፁማዊና አንፃራዊ

የኃይል አሰላለፍ፣ ዝንባሌያቸውና የሰላማዊ ትግሉ ዓላማ ይወስኑታል ማለት ነው::

## 5.6. <u>የፖለቲካ ተቃውሞ ውጤቶችን ዲሞክራሲያዊ ማድረግ</u>

የሰላማዊ ትግል ዘዴ ሥራ ላይ መዋል ማዕከላዊነትን ከሚያጠናክረው የኃይል አመፅ ይልቅ ማህበረሰቡን ዲሞክራሲያዊ ለማድረግ በተለያዩ መንገዶች አስተዋፅዖ ያደርጋል::

ይህ ዲሞክራሲያዊ የማድረግ ሂደት በመሪዎቹ ላይ አንድ ብቻ «አሉታዊ» ተፅእኖ ያሳድራል:: ይኸውም ከጦር መሣሪያ ትግል በተቃራኒ ይህ ዘዴ የበላይ አመራሩ ጨቋኝ ሆኖ ወደ ህብረተሰቡ በመዞር አምባገነን እንዲሆን ወይም አምባገነንነትን እንዲጠናከር ዕድል አለመስጠቱ ነው:: ይህም የፖለቲካ ተቃውሞ መሪዎች በተከታዮቻቸው ላይ የፖለቲካ ጫናና ግፊት ሊፈጥሩ ቢችሉም ተከታዮቻቸው በአስተሳሰብ ቢለዩ ወይም ሌሎች መሪዎችን ቢመርጡ ሊያስሯቸው ወይም ሊረሽኗቸው አይችሉም ማለት ነው::

ሌላው ዴሞክራሲያዊነትን የማስፈን ዘዴ አዎንታዊ ነው:: እሱም ሰላማዊ ትግሉ ህዝቡ በፖለቲካ የመቃወም ዘዴ መብቶቹንና ነፃነቱን ከሚጋፉና ሊጋፉ ከሚችሉ አምባገነኖች እንዲከላከል ማስቻሉ ነው:: አዎንታዊ የሆኑ ዲሞክራሲያዊ የማድረግ ሂደት ውጤቶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል::

- ማህበረሰቡ የሚያካብተው የሰላማዊ ትግል ልምድ ይበልጥ በራሱ እንዲተማመን ስለሚያደርገው የአምባገነኑን መንግሥት ትንኮሳና በኃይል የመጨቆን አቅም ለመቋቋም ይረዳዋል::
- ትብብር መንፈግና የፖለቲካ ተቃውሞን የመሰለ የሰላማዊ ትግል ልምድ ያለው ህብረተሰብ ማናቸውም አምባገነን የሚያደርግበትን ፀረ ዲሞክራሲያዊ አፈና ለመመከት ያስችለዋል::



- ከአምባገነኖች አፈናና ቁጥጥር በተቃራኒ ሰላማዊ ትግል እንደ የንግግር ነጻነት፣ የህትመት ነጻነት፣ በነጻ መደራጀትና የመሰብሰብ ነጻነት የመሳሰሉ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ለመተግበር ያገለግላል::
- ቀደም ሲል እንደተገለፀው ሰላማዊ ትግል በህብረተሰቡ ውስጥ ለነጻ ቡድኖችና ተቋሞች መፈጠር፣ ህልውናና መጠናከር ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ያደርጋል:: እነዚህም፣ የህብረተሰቡን አቅም በመጠቀም በአምባገነኖች ላይ ገደብ በማድረግ ለዲሞክራሲ መስፈን እጅግ የላቀ ጠቀሜታ አላቸው::
- ሰላማዊ ትግል ህብረተሰቡ የአምባገነኑን መንግሥት ፖሊስና የጦር ሠራዊት እርምጃ ለመቃወም አቅሙን ለማጠናከር ያስችላል::
- ህብረተሰቡና ተቋማቱ በሰላማዊ ትግል ዘዴዎች ዲሞክራሲን በማጠናከር የአምባገነኑን መንግሥት የኃይል ምንጭ በመገደብ ወይም በማቋረጥ ጭቆናውን ለመቀጠል ያለውን አቅም በመፈታተን ያዳክሙታል::

## 5.7. <u>የሰላማዊ ትግል ውስብስብነት</u>

በዚህ ምዕራፍ እንደተመለከትነው ሰላማዊ ትግል በርካታ ዘዴዎችን፣ መንገዶችንና የተወሰኑ ባህርያትን በማሟላትና በመጠቀም ውስብስብ የሆኑ ማህበራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል:: በተለይም አንድን አምባገነን ለማስወገድ የሚደረገው የፖለቲካ ተቃውሞ ትግል ውጤታማ እንዲሆን በጥንቃቄ መታቀድና መዘጋጀት ያስፈልገዋል:: በትግሉ ሊሳተፉ የሚችሉ ወገኖችም የሚፈለግባቸው ግልፅ ሊሆንላቸው ይገባል:: ለትግሉ የሚያስፈልጉት ግብዓቶችም መሟላት አለባቸው:: ወደ ግብ መቃረቢያውን ዕቅድ የሚነድፉትም ሰላማዊ ትግሉ ይበልጥ ውጤታማ የሚሆንበትን መንገድ ማጥናት አለባቸው:: ከዚህ በኋላ ወሳኝ ወደሆነው ስትራቴጂያዊ ዕቅድ አዘገጃጀት እንሸጋገራለን::

# ምዕራፍ ስድስት

# የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አስፈላጊነት

በአምባገነኖች ላይ የሚነጣጠር የፖለቲካ ተቃውሞ በተለያዩ መንገዶች ሊጀመር ይችላል:: በአለፉት ዘመናት የዚህ ዓይነቱ ተቃውሞ አብዛኛውን ጊዜ ያልታቀደና አጀማመሩም ግብታዊ እንደነበረ ይታወቃል:: የዚህ ዓይነቱን ተቃውሞ የሚያቀጣጥሉት ድርጊቶችም በጣም የተለያዩ ሲሆኑ ብዙውን ጊዜ የአምባገነኖች አዳዲስ የጭካኔ ተግባራት፣ የአንድ ታዋቂ ሰው መታሰር ወይም መገደል፣ የአዳዲስ ጭቋኝ ህጐች ወይም መመሪያዎች መውጣት፣ የምግብ ዕጥረት፣ የሀይማኖት መደፈር ወይም በህብረተሰቡ ውስጥ የጐላ ተቀባይነት ያለው ክብረበዓል መንቋሸሽ ሊሆን ይችላል:: አንዳንድ ጊዜም አምባገነኖች የሚወስዱት እርምጃ ህዝቡን ስለሚያስቆጣ የሚያስከትለው ወይም መጨረሻው ባይታወቅም አመፅ ሊቀሰቅስ ይችላል:: በሌላ አጋጣሚ ደግሞ ቆራጥ ዜጐች ወይም አነስተኛ ቡድኖች የሚወስዱት እርምጃ ህዝቡን ሊያነሳሳና ሊያሰባስብ ይችላል:: በህዝቡ ውስጥ ያለ አንድን ብሶት ሌሎች የህዝብ ክፍሎች ከደረሰባቸው ተመሳሳይ በደል ጋር ስለሚያያይዙት በትግሉ እንዲቀላቀሉ ሊያደርጋቸው ይችላል:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በአንድ ግለሰብ ወይም በተወሰነ ቡድን የሚደረግ የትግል ጥሪ ባልተጠበቀ ሁኔታ ከህዝቡ ሰፊ ድጋፍ ሊያገኝ ይችላል::

ግብታዊነት ጥቂት አዎንታዊ ውጤቶች ሊኖሩት ቢችሉም ብዙውን ጊዜ በጐ ያልሆነው ጐኑ ያመዝናል:: ተደጋግሞ እንደሚታየው ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች አምባገነኖች የሚያደርሱባቸውን ሥቃይ ባለመገመት ከፍተኛ ጉዳት የሚያጋጥማቸው ከመሆኑም በላይ ትግሉ ይዳከማል:: አንዳንድ ጊዜም ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ቁልፍ ውሳኔዎችን



ለአጋጣሚ በመተዋቸው ውጤቱ አስከፊ ይሆናል:: ጨቋኙ አምባገነን ሥርዓት በሚደመሰስበት ሁኔታ እንኳን ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚደረገው ሽግግር በዕቅድ ባለመመራቱ አዲስ አምባገነን እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል::

## 6.1. ትክክለኛ ዕቅድ መንደፍ

ያልታቀዱ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ወደፊት ያለጥርጥር አምባገነኖችን በማስወገድ ረገድ ሰፊ ድርሻ ይኖራቸዋል:: ይሁንና ባሁኑ ጊዜ አምባገነኖችን ለማስወገድ ውጤታማ የሆኑ ዘዴዎችን ለመቀመር የፖለቲካ ሁኔታዎችንና የህዝቡን ዝንባሌና ብስለት በመገምገም ዘመቻው እንዴት መቀነባበር እንዳለበት ለማቀድ ይቻላል:: በዚህ ሁኔታ ስለተጨባጭ ሁኔታው በጥንቃቄ ግምገማ ከተደረገና የህዝቡ አቅም ከታየ ከአምባገነኖች ለመላቀቅ የሚቻልባቸውን ውጤታማ መንገዶች ለመምረጥ ያስችላል::

ማንም ሰው አንድ ነገር ማከናወን ከፈለገ አስቀድሞ ማቀድ የተገባ ነው:: የዓላማው መሳካት ይበልጥ ወሳኝ ሲሆን ወይም የሚያስከትለው ውድቀት ሲከፋ የዕቅድን ወሳኝነት ያመለክታል:: ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ማዘጋጀት ግብአቶችን በማሰባሰብ ይበልጥ ውጤታማ በሆነ ዘዴ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያስችላል:: ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄው ውሱን ግብአት የሚጠቀምና ደጋፊዎቹ እስካፍንጫው ከታጠቀ አምባገነን ጋር የሚፋለሙ በመሆናቸው ለአደጋ ይጋለጣሉ:: ይህም ለሁሉም ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄዎች ይበልጥ እውነትነት አለው:: ከዚህ በተቃራኒው በተለምዶ አምባገነኑ መንግሥት ሰፊ ቁሳዊ ሀብቶች፣ ጠንካራ ድርጅታዊ አቅምና የማስቃየት ችሎታ ይኖረዋል::

«ወደግብ መቃረቢያ አጠቃላይ ዕቅድ» ማውጣት ማለት ትግሉ ካለበት ደረጃ ተነስቶ ወደፊት ሊፈጠር ለታሰበው ሥርዓት የሚያደርስ

መንገድ በመቀመር የተግባር መመሪያ መንደፍ ማለት ነው:: ይህም ማለት ባጭሩ ከአንድ አምባገነን አገዛዝ ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚደረገውን ሽግግር በዕቅድ መምራት ማለት ነው:: ይህን ዕቅድ በተግባር ለመተርጎምም በየደረጃው የሚከናወኑ ዘመቻዎችና የአምባገነኑን አገዛዝ ማድከምና ጭቁኑን ህዝብና ማህበረሰቡን ማጠናከርን ያጠቃልላል:: እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚገባው ዓላማው ዝም ብሎ ሥልጣን ላይ ያለውን አምባገነን ማስወገድ ብቻ ሳይሆን በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲተካ ማድረጉ ነው:: ይህ ሳይሆን ቀርቶ የአምባገነኑን አገዛዝ በማጥፋት ላይ ብቻ የሚያተኩር አጠቃላይ ዕቅድ ሌላ ጨቋኝ አገዛዝ እንዲተካ የማድረግ አደጋ ሊያስከትል ይችላል::

## 6.2. ዕቅድ የመንደፍ እንቅፋቶች

አንዳንድ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚገኙ የነጻነት ኃይሎች ነጻነት የሚገኝበትን መንገድ ለማፋጠን ያላቸውን ኃይል በቅንጅት ሥራ ላይ አያውሉም:: እነዚህ የሰላም ጠበቆች ከተግባር በፊት ጥንቃቄ የተሞላበትን ስትራቴጂያዊ ዕቅድ የመንደፍን አስፈላጊነት ብዙውን ጊዜ አያተኩሩበትም:: በመሆኑም ስትራቴጂያዊ ዕቅድን በተግባር አናገኘውም::

ለህዝባቸው የፖለቲካ ነጻነት ለማምጣት ራዕይ ያላቸው ሰዎች ወደግባቸው ለመድረስ እንዲችሉ የዚህ ዓይነቱ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ የማይኖራቸው ለምንድነው? አለመታደል ሆኖ እነዚህ ተቃውሞ የሚያካሂዱ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ብዙውን ጊዜ የስትራቴጂያዊ ዕቅድን አስፈላጊነት አይረዱትም ወይም አለመዱትም ወይም በዚያ መንገድ እንዲያስቡ አልሰለጠኑም:: ስትራቴጂያዊ ዕቅድ መንደፍ በእርግጥ አስቸጋሪ ተግባር ነው:: በአምባገነኖች በማያቋርጥ ሁኔታ እየተዋከቡና በዕለት ከለት ተግባሮቻቸው እየተዋጡ ተቃዋሚዎች ብዙውን ጊዜ



ስትራቴጂያዊ ዕቅድ የመንደፍ ችሎታቸውን ለማሻሻል የደህንነት ዋስትናም ሆነ ጊዜው የላቸውም::

ይልቁንም ለአምባገነኖች ትንኮሳ መልስ የመስጠት አካሄዳቸው የተለመደ ነው:: በመሆኑም ተቃዋሚው ወገን ብዙውን ጊዜ የተወሰኑ መብቶችን ወይም አንዳንድ ጥቅሞችን ለማግኘት እንዲያም ሲል የአምባገነኖችን ቁጥጥር ለማላላት ወይም በመንግሥት አዳዲስ የጭቆና ፖሊሲዎች ላይ አንዳንድ ገደብ በማድረግ ስለሚወሰን በማጥቃት ፋንታ ተከላካይ ይሆናል::

ጥቂት ግለሰቦችና ቡድኖች የነጻነት ትግሉ በረጅም ጊዜ ዕቅድ መመራት እንዳለበት አስፈላጊነቱ ላይታያቸው ይችላል:: ተግባራቸውን በዕቅድ ከመምራት ይልቅ ዓላማቸውን በየዋህነት፣ በትክክልና ለረጅም ጊዜ ደግፈው ስለዘለቁ አምባገነኑ ሥርዓት ይወድቃል ብለው በቅንነት ያስባሉ:: ሌሎች ደግሞ ባለው አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ችለው ከኖሩና አምባገነኖች የሚፈፅሙትን ከታዘቡ ዓላማቸውን በተግባር ለመተርጎም የቻሉትን ያደረጉ ሊመስላቸው ይችላል:: ለሰው ልጅ ሰብዓዊ ግቦችና መርሆዎች በፅናት መቆም የሚደነቅ ተግባር ቢሆንም አምባገነኖችን አስወግዶ ነጻነትን ለመቀዳጀት ግን በቂ አይደለም::

ሌሎች የዋህ የአምባገነን ተቃዋሚዎች ደግሞ ኃይል ከተጠቀሙ ነጻነት መጎናፀፍ ይቻላል ብለው በየዋህነት ሊያስቡ ይችላሉ:: ነገር ግን ቀደም ሲል እንደተገለፀው የኃይል ተቃውሞ ማካሄድ ለስኬት ዋስትና አይሆንም:: እንዲያውም በተቃራኒው በነጻነት ፈንታ ወደሽንፈትና ወደብዙሀን ሰቆቃ ወይም ወደ ሁለቱም ሊያመራ ይችላል:: በብዙ አጋጣሚዎች በኃይል ተቃውሞና በወታደራዊ ሁኔታዎች ረገድ ተቃዋሚዎች የተሻለ ሁኔታ ላይ አይገኙም::

ያሰኛቸውን ማድረግ እንደሚገባቸው የሚያምኑ ታጋዮችም አሉ:: ይሁንና የዚህ ዓይነቱ አካሄድ የራስን ሀሳብ ብቻ ማድመጥ ከመሆኑም

ባሻገር አጠቃላይ ነጻ የመውጣት ሂደቱንም በስትራቴጂያዊ ዕቅድ ለመምራት ዕድል አይሰጥም።

አንዳንድ ሰዎች በሚሰነዝሩት «ድንቅ ሀሳብ» ላይ ተግባርን መመሥረትም እንደዚሁ እንከን አያጣውም። ከዚህ ይልቅ ተከታታይ እርምጃዎችን በጥንቃቄ በማቀድ አምባገነኖችን ለማውረድ ይቻላል። የተቃውሞ መሪዎች ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ከሌላቸው ለድል የሚያበቁ ተከታታይ እርምጃዎች ምን ምን መሆን እንዳለባቸው ሊያውቁ አይችሉም። «ፈጠራና ድንቅ ሀሳቦች» ጠቃሚነታቸው ባይካድም ያለውን ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በመተግበር ወደፊት ለማራመድ እንዲችሉ በዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ተጣጥመው ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው።

ጥቂት ሰዎች ደግሞ በአምባገነኖች ላይ በተከታታይ መወሰድ ያለባቸውን ጠንካራ እርምጃዎች ቢያውቁም ከየት መጀመር እንዳለባቸው ስለሚቸገሩ «ሁሉንም ነገር ጐን ለጐን ማካሄድ» እንደሚጠቅም ያስባሉ። ይህ አካሄድ ምናልባት ሊጠቅም ቢችልም በተለይም ላልተጠናከሩ ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሰዎች የሚሞከር አይደለም። ከዚህም በላይ እንደዚያ ዓይነቱ አካሄድ ትግሉ ከየት መጀመር እንዳለበት፣ የት ቦታ መረባረብ እንደሚገባና ውሱን ግብዓቶችን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ፍንጭ አይሰጥም።

ሌሎች ሰዎች ደግሞ አንድ ዓይነት ዕቅድ የመኖሩን አስፈላጊነት ቢገነዘቡም የአጭር ጊዜ ዕቅድ ወይም በሥልት ላይ የተመሠረተ ዕቅድ ብቻ እንደሚያስፈልግ ያስባሉ። የረጅም ጊዜ ዕቅድ የመንደፍን አስፈላጊነት ወይም ጭራሹኑ መንደፍ መቻሉ አይታያቸውም። አንዳንድ ጊዜ በተደጋጋሚ በሚያጋጥሟቸው አነስተኛ ዕለታዊ ጉዳዮች ስለሚዋጡ፣ እንዲያውም በዲሞክራሲያዊው እንቅስቃሴው ዕቅድ መሠረት የተግባር ቅድሚያ ከመያዝ ይልቅ ብዙውን ጊዜ ለተቃዋሚው እርምጃ መልስ ለመስጠት ሲታክቱ ስትራቴጂያዊ በሆነ መንገድ



ለማሰብና ትንተና ለመስጠት አይችሉም። እነዚህ መሪዎች ያላቸውን በርካታ አቅም በእንደዚህ ዓይነት የአጭር ጊዜ እንቅስቃሴዎች ላይ ስለሚያውሉም ብዙውን ጊዜ ወደግባቸው የሚያቃርቧቸውን አጠቃላይ ጥረቶቻቸውን ለመምራት በርካታ አማራጮችን ለመመርመር አይችሉም።

አንዳንድ ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎች በዕለት ከዕለት ጉዳዮች ላይ በማተኮርና በሌሎችም ምክንያቶች አምባገነኑን መንግሥት ለማውረድ ትግሉን የሚመሩበት ዓብይ ስትራቴጂ ላይነድፉ ይችላሉ። በውስጣቸውም በእነሱ ጥረት ብቻ አምባገነኖችን ማጥፋት እንደሚቻል አያምኑም። በመሆኑም አምባገነኖችን ለማጥፋት ዕቅድ ማውጣት ጊዜ ማባከን ወይም ዋጋ የሌለው ድካም ተደርጐ ይገመታል። ለነጻነት የሚፋለሙ ኃይሎች ብዙውን ጊዜ ከተጠናከሩና እስከአፍንጫቸው ከታጠቁ ወታደራዊና የፖሊስ ኃይል ካላቸው ጋር ስለሚጋፈጡ አምባገነኖቹ የፈለጉትን ሊያደርጉ የሚችሉ ይመስላቸዋል። በዚህ ምክንያት እውነተኛ ተስፋ ስለማይኖር እንደዚህ ዓይነት ሰዎች አምባገነኖችን የሚቋቋሙት በውስጣቸው ባለው ሀቅና ምናልባትም ለታሪክ ይሆናል። ስህተታቸውን ባያምኑና ምናልባትም በህሊናቸውም ላያሰላስሉት ቢችሉም እንኳ ተግባራቸው ለራሳቸውም ተስፋ ቢስ እንደሆነ ይረዱታል። በመሆኑም ለእነሱ የረጅም ጊዜ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ምንም ዋጋ የለውም።

እንደዚህ ዓይነት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ማዘጋጀት አለመቻል የሚኖረው ውጤት ድንገተኛ ይሆናል። ይህም ማለት የአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ጥንካሬ ይባክናል፤ ተግባር ውጤት አያመጣም፤ አቅምም በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ይባክናል፤ አንፃራዊ ጠቀሜታ ያላቸው አጋጣሚዎችም ሥራ ላይ አይውሉም። ከዚህም በላይ መስዋዕትነት ከንቱ ይሆናል። ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ተግባራቸውን በስትራቴጂያዊ

ዕቅድ የማይመሩ ከሆነ ከግባቸው ላይደርሱ ይችላሉ:: በጥንቃቄ ያልተዘጋጀና ተያያዥነት የሌላቸው ድርጊቶች ቅልቅል የሆነ ዕቅድ ትግሉን ወደፊት አያራምደውም:: በተቃራኒው አምባገነኑ መንግሥት ቁጥጥሩን እንዲያጠብቅና ኃይሉን እንዲያጠናክር ሊያግዘው ይችላል::

ያለመታደል ሆኖ ምናልባትም ጭራሹኑ ተሞክሮ ከሆነ ትግሉን የሚመራ አጠቃላይ ዕቅድ ባለመኖሩ ምክንያት አምባገነኖች ከሚገባው በላይ የተረጋጉና ዘላቂ መስለው ይታያሉ:: በመሆኑም መኖር ከሚገባቸው በላይ ለዓመታትና እንዲያውም ለዓሥርት ዓመታት ሥልጣን ላይ ይቆያሉ::

## 6.3. በስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅት አራት ቁልፍ ቃላት

የስትራቴጂያዊ ዕቅድ ዝግጅትን አስተሳሰብ ለማዳበር እንዲረዳን የአራቱን መሠረታዊ ቃሎች ትርጉም ግልፅ ማድረግ ይኖርብናል:: እነሱም:- ዓብይ ስትራቴጂ፣ ስትራቴጂ፣ ስልትና ዘዴ ናቸው::

ዓብይ ስትራቴጂ ማለት ማናቸውንም አግባብነት ያላቸውንና ሊሰባሰቡ የሚችሉ የኤኮኖሚ፣ የሰው ኃይል፣ የሞራል፣ የፖለቲካና የድርጅት ወዘተ... ግብዓቶችን በማቀነባበርና በመጠቀም በአንድ ግጭት ውስጥ የአንድን ቡድን ዓላማ ለማሟላት የሚያገለግል ፅንሰ ሀሳብ ነው:: አብይ ስትራቴጂ በቡድኑ ዓላማና ግብዓቶች ላይ በማተኮር በትግሉ ውስጥ መደበኛ የጦር መሣሪያ ትግል ወይም ሰላማዊ ትግል የትኛው ይበልጥ ትግሉን ለማራመድ ጠቃሚ እንደሆነ በግጭት ውስጥ እጅግ ተስማሚ የሆነውን የድርጊት ቴክኒክ ይወስናል:: ዓብይ ስትራቴጂን በመንደፍ የተቃውሞ መሪዎች በተቃራኒው ወገን ላይ ግፊትና ተፅዕኖ የሚፈጥሩበትን ሁኔታ መገምገም አለባቸው:: ከዚህም በላይ ዓብይ ስትራቴጂ የተቃውሞ ዘመቻዎች የሚካሄዱበትን አመቺ ሁኔታዎችና ጊዜ ጭምር ይወስናል::



ዓብይ ስትራቴጂ ትግሉን ለማካሄድ ይበልጥ ውሱን የሆኑ ስትራቴጂዎችን ያስቀምጣል:: ከዚህም በላይ ለተወሰኑ ቡድኖች ግዳጅና አስፈላጊ ግብዓቶችን ይሰጣል::

ስትራቴጂ ደግሞ በግጭት ውስጥ በተመረጠው ዓብይ ስትራቴጂ ውስጥ አንድን ዓላማ በተሻለ መንገድ ማሳካትን የሚመለከት ፅንሰ ሀሳብ ነው:: ስትራቴጂ መቼና እንዴት መፋለም እንደሚገባ እንደዚሁም የተቻለውን ያህል የትግሉን አንድ ግብ ውጤታማ በሆነ መንገድ ማከናወንን ይመለከታል:: ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በአንድ ሰዓሊ ንድፍ ሊመሰል ሲችል ስትራቴጂ ደግሞ በሰዓሊው ፅንሰ ሀሳብ ሊመሰል ይችላል::

ከዚህም በላይ ስትራቴጂ ተቃራኒ ወገኖች ድል መሆናቸው እንደማይቀር በመረዳት በግልፅ ፍልሚያ ሳያደርጉ እጃቸውን የሚሰጡበትን ስትራቴጂያዊ ሁኔታ መፍጠርንም ሊያካትት ይችላል:: ያም ባይሆን የተሻሻለው ስትራቴጂያዊ ሁኔታ ተፋላሚዎቹ ትግላቸው ውጤታማ እንደሚሆን ያረጋግጣል:: ከዚህም በላይ በስትራቴጂው ስኬት ሲገኝ እንዴት ትግሉን ወደፊት በሚያራምድ መንገድ ጥቅም ላይ እንደሚውል ያመላክታል::

ስትራቴጂ በራሱ በትግል ሂደት ውስጥ ዘመቻ እንዴት እንደሚጀመርና የተለያዩ የስትራቴጂያዊ ዕቅድ አካላት ወደ ግብ ለመድረስ እንዴት በግጥምጥሞሽ እንደሚሠሩ የሚያመላክት መሠረታዊ ሀሳብ ነው:: ከዚህም በላይ የተወሰኑ ቡድኖች በአነስተኛ ግዳጆች ላይ እንዴት በጥንቃቄ መሠማራት እንዳለባቸው ያሳያል:: በብልሀት የተዘጋጀ ስትራቴጂ አንድ የተመረጠ የትግል ሥልት ለውጤት የሚበቃበትን መመዘኛዎች ያገናዘበ መሆን አለበት:: የተለያዩ ቴክኒኮች የተለያዩ ሁኔታዎችን ማሟላት ይጠይቃሉ:: ይሁንና የተለያዩ

ሁኔታዎች መሟላት ብቻውን ለሥኬት ዋስትና አይሆንም:: ሌሎች መሟላት ያለባቸው ጉዳዮችም ይኖሩ ይሆናል::

ስትራቴጂያዊ ዕቅዶችን በመንደፍ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ግቦችን በግልፅ ማስቀመጥና ውጤታማነትም በምን እንደሚለካ በማያሻማ ሁኔታ መግለፅ አለባቸው:: ይህ አተረጓጐምና ትንተናም ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ነዳፊው ለተመረጡ ግቦች በትክክል የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ለመለየት ያስችለዋል:: ይህ ግልፅነትና ትርጓሜ ለሥልታዊ ዕቅድ አነዳደፍ ጭምር አግባብነት ይኖረዋል::

ሥልት ማለት የተወሰነ ግብን ለማሳካት የሚውል ድርጊት ነው:: ሥልቶችና ዘዴዎች ስትራቴጂውን ለመተግበር ይጠቅማሉ:: ሥልቶች በአንድ በተወሰነ ግዳጅ በሳልና ውጤታማ የሆነ የአቅም አጠቃቀምን ይጠቁማሉ:: አንድ ስትራቴጂ ላይ ለመድረስ የሚመረጠው ታክቲክ/ብልሀት/ በየትግሉ ምዕራፎች የሚካሄደው የትግል ዓይነት ምን ያህል በስኬት ሊመራ እንደሚችል ይወስናል:: በጣም ውጤታማ ለመሆን ሥልቶችና ዘዴዎች ወደ ስትራቴጂያዊ ግቦች የሚያዳርሱ መሆናቸው የማያቋርጥ ትኩረት ማግኘት አለበት:: ስትራቴጂያዊ ግቦችን የማያጠናክር የሥልት አፈጻጸም በመጨረሻ የባከነ አቅም መሆኑ አይቀርም::

ስለሆነም ስትራቴጂ በዓብይ ስትራቴጂ ውስጥ እንደሚካተት ሁሉ ስልትም በስትራቴጂ ውስጥ የሚካተት ውስን ድርጊት ነው:: ሥልቶች ፍልሚያን ሲያመለክቱ ስትራቴጂ ደግሞ ሰፋ ያሉ የትግል ዘዴዎችን ያካትታል:: አንድ ሥልት የአንድ አጠቃላይ ፍልሚያ ወይም ዘመቻ ስትራቴጂ አካል ሆኖ ሊገለፅ ይችላል:: ሥልቶች ከስትራቴጂ ይልቅ ለአጭር ጊዜና ጠበብ ላለ አካባቢ ወይም ተቋም ወይም ደግሞ ለተወሰኑ የሰዎች ስብስብ አለበለዚያም ውስን ለሆኑ ዓላማዎች ማስፈፀሚያ ሊውሉ ይችላሉ:: በሰላማዊ ትግል ሂደት በሥልታዊ ግብና



በስትራቴጂያዊ ግብ መካከል ያለው ልዩነት የተመረጠው ግብ አነስተኛ ወይም አብይ በመሆኑ ሊሆን ይችላል::

ሥልታዊ የማጥቃት ግዳጆች ሲመረጡ ስትራቴጂያዊ ግቦችን ለማፋጠን ነው:: ሥልታዊ ግዳጆች ጠላትን በወሳኝነት ለማጥቃት የሚያስችሉ የስትራቴጂ ቀያሹ መሣሪያዎች ናቸው:: ስለሆነም፣ ትግሉን ለማቀድና ለመምራት ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች ሁኔታዎችን ለመገምገምና ተገቢ ዘዴዎችን ለመምረጥ የሚያስችላቸው ዕውቀት እንዲኖራቸው የግድ ነው:: በትግሉ የሚሳተፉ ወገኖችም የተመረጠውን ቴክኒክና የተወሰኑ ዘዴዎችን ለመጠቀም እንዲችሉ ሥልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል::

ዘዴ የተወሰኑ ብልሀቶችን ወይም የተግባር አማራጮችን የሚያመለክት ነው:: በሰላማዊ ትግል ቴክኒክ ውስጥ በምዕራፍ አምስት የተመለከትናቸውን የተለያዩ ዓይነት የሥራ ማቆም አድማዎችን፣ በአንድ ድርጊት ከመሳተፍ መቆጠብን፣ የፖለቲካ ትብብር መንፈግና የመሳሰሉትም የትግል ቅርፆች ያካትታል::

ለአንድ ሰላማዊ ትግል ሚዛናዊና ውጤታማ የሆነ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ መቅረፅ አብይ ስትራቴጂዎች፣ ሥልቶችና ዘዴዎች፣ በጥንቃቄ በመቀመራቸውና በመመረጣቸው ላይ ይወሰናል::

የዚህ ምዕራፍ ዋናው ትምህርት ከአንድ አምባገነን ነጻ ለመውጣት ጥንቃቄ የተመላበት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በመንደፍ ረገድ የአንድን ግለሰብ ወይም ቡድን ችሎታ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን ነው::

የአንድን ግለሰብ ወይም ቡድን ምሁራዊ አቅም ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም የስትራቴጂያዊ ግቡን ሂደት በሚገባ በማሳየት ህብረተሰቡን ወደ ነጻነትና ዲሞክራሲ ለመምራት ያሉትን ግብዓቶች በብልሀት ለመጠቀም የሚያስችለውን ያህል ብልህነት የተመላበት ዕቅድ ለመንደፍ አለመቻል ደግሞ ለውድቀት ይዳርጋል::

# ምዕራፍ ሰባት
## ስትራቴጂያዊ ዕቅድ መንደፍ

ስኬታማነትን አስተማማኝ ለማድረግ የተቃውሞ መሪዎች የሚሰቃየውን ህዝብ የሚያጠናክር፣ አምባገነኖችን አዳክሞ የሚያጠፋና ዘላቂ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሚያስችል አጠቃላይ ዕቅድ መንደፍ ይኖርባቸዋል:: እንደዚህ ዓይነት የድርጊት መርሀ ግብር ለመንደፍም ተጨባጭ ሁኔታውን በጥንቃቄ መመርመርና ለውጤታማ ተግባር የሚያበቁ አማራጮችን መለየት ያስፈልጋል:: ከዚህ ዓይነቱ ጥንቃቄ የተሞላበት ትንተና በመነሳትም ዓብይ ስትራቴጂም ሆነ ነጻነትን ለመጎናጸፍ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የዘመቻ ስትራቴጂዎች ሊነደፉ ይችላሉ:: ምንም እንኳን ተዛማጅነት ያላቸው ቢሆኑም ዓብይ ስትራቴጂና የዘመቻ ስትራቴጂዎች ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው:: ልዩ የዘመቻ ስትራቴጂዎች ዳብረው ሊዘጋጁ የሚችሉት አብይ ስትራቴጂ ከተነደፈ በኋላ ብቻ ነው:: የዘመቻ ስትራቴጂዎች ሲዘጋጁ ዓብይ ስትራቴጂውን ለማጠናከርና ከግብ ለማድረስ በሚያስችል መልኩ መሆን ይኖርባቸዋል::

የተቃውሞ ስትራቴጂ ቀረፃ ብዙ ጥያቄዎችንና ግዳጆችን ያገናዘበ መሆን አለበት:: እዚህ ላይ በዓብይ ስትራቴጂም ሆነ በዘመቻ ስትራቴጂ ደረጃ አንዳንድ ጠቃሚ ጉዳዮችን ማየት ይኖርብናል:: ይሁን እንጂ ማናቸውንም ስትራቴጂያዊ ዕቅዶች የሚነድፉ ሁሉ አካላዊ፣ ታሪካዊ፣ መንግሥታዊ፣ ወታደራዊ፣ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ ኤኮኖሚያዊና ዓለማቀፋዊ ጉዳዮችን በትኩረት በማየት አጠቃላይ ትግሉ ስለሚካሄድበት ሁኔታ መሠረታዊ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል:: ስትራቴጂዎች ሊነደፉ የሚችሉት በአንድ የትግል ዘርፍና መነሻውን ባገናዘበ መልኩ ብቻ ይሆናል::



ዲሞክራሲያዊ መሪዎችና የስትራቴጂ ቀያሾች የትግሉን ጠቀሜታና ግቦች መገምገማቸው ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው:: ግቦቹ ወሳኝ ትግል ሊደረግላቸው ይገባል? ለምን? በመሆኑም የትግሉን ተጨባጭ ግብ ማስቀመጥ ወሳኝ ነው:: ከላይ እንደተመለከትነው የአምባገነኖች መወገድ ወይም ሥልጣን ላይ ያሉት አምባገነኖች መባረር ብቻውን በቂ አይደለም:: የዚህ ትግል ዋና ዓላማ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚመራ ነጻ ህብረተሰብና መንግሥት መመሥረት ነው:: በዚህ ነጥብ ላይ ያለው ግልፅነት አብይ ስትራቴጂና ዝርዝር ስትራቴጂዎች ለመንደፍ ያስችላል::

የትግሉ ስትራቴጂ ቀያሾች የሚከተሉትን የመሳሰሉ በርካታ መሠረታዊ ጥያቄዎችን መመለስ ይጠበቅባቸዋል::

- ነጻነትን ለመቀዳጀት ዓብይ የሆኑት እንቅፋቶች ምንድናቸው?
- ነጻነትን የመጎናፀፍ ሂደት የሚያፋጥኑ ጉዳዮች ምንድናቸው?
- የአምባገነኑን መንግሥት ዋና ዋና ጠንካራ ጎኖች ምንድን ናቸው?
- የአምባገነኑ መንግሥት የተለያዩ ደካማ ጎኖች ምንድን ናቸው?
- የአምባገነኑ መንግሥት የሥልጣን ምንጮች ለጥቃት የተጋለጡት እስከ ምን ድረስ ነው?
- የዲሞክራሲያዊ ኃይሎችና የአጠቃላዩ ህዝብ ጠንካራ ጎኖች ምንድን ናቸው?
- የዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ደካማ ጎኖችና የሚጠናከሩበት መንገዶች ምንድን ናቸው?
- በግጭቱ ውስጥ በቀጥታ የማይሳተፉ፣ ምናልባትም አምባገነኑን መንግሥት ወይም ዲሞክራሲያዊውን ንቅናቄ የሚረዱ ወይም ሊረዱ የሚችሉ የሦስተኛ ወገኖች አቋም ምን ይመስላል?
- በምንስ ዓይነት መንገድ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎችን ሊረዱ ወይም ሊተባበሩ ይችላሉ?

### 7.1. የትግል ዘዴ አመራረጥ

ዕቅድ ቀያሾች በዓብይ ስትራቴጂ ደረጃ ወደፊት በሚያጋጥመው ግጭት ሥራ ላይ የሚውለውን የትግል ዘዴ መምረጥ አለባቸው:: የተለያዩ የትግል ሥልቶች ማለትም፣ እንደ መደበኛ የጦር መሣሪያ ውጊያ፣ የደፈጣ ውጊያ፣ የፖለቲካ ተቃውሞና ሌሎችም የትግል ዘዴዎች ያላቸው ጠቀሜታና ውስንነት መመዘን ይኖርበታል::

ይህን ምርጫ በማካሄድም የትግሉን ስትራቴጂ የሚቀይሱት ሰዎች ከዚህ የሚከተሉትን የመሣሠሉ ጥያቄዎችን ማጤን ይኖርባቸዋል::

- የተመረጠው የትግል ዓይነት የዲሞክራቶችን አቅም ይመጥናል? የተመረጠው የትግል ቴክኒክ የጭቁኑን ህዝብ ጥንካሬ ይጠቀማል? የተመረጠው ቴክኒክ የአምባገነኖችን ድክመት ዒላማ ያደርጋል? ወይስ ደግሞ በጠንካራ ጐናቸው ላይ ያነጣጠረ ነው? የተመረጠው የትግል ዘዴ ዲሞክራቶች ይበልጥ በራሳቸው እንዲተማመኑ ያደርጋል? ወይስ ደግሞ በሶስተኛ ወገኖች ላይ ወይም በውጪ ኃይሎች ላይ ጥገኛ ያደርጋቸዋል? የተመረጠው የትግል ዘዴ አምባገነኖችን በማስወገድ ረገድ ያለው ታሪክ ምን ይመስላል? የተመረጠው የትግል ዘዴ በትግሉ የሚደርሰውን ጉዳትና ጥፋት ይጨምረዋል? ወይስ ይገድበዋል? የተመረጠው የትግል ዘዴ ውጤታማ ሆኖ አምባገነኖችን እንደሚያስወግድ በማመን ከትግሉ በሚወለደው የመንግሥት ዓይነት ላይ ምን ተፅዕኖ ያሳድራል? በዚህ ሂደት ውጤታማ አለመሆኑ የተረጋገጠው የትግል ዘዴ ከዓብይ ስትራቴጂው ውስጥ መሠረዝ ይኖርበታል::

ቀደም ባሉት ምዕራፎች ውስጥ የፖለቲካ ተቃውሞ ከሌሎች የትግል ዘዴዎች ይልቅ አንፃራዊ ጠቀሜታ እንዳለው ተገንዝበናል::



የትግሉ ስትራቴጂ ቀያሾች የግጭቱን ሁኔታ በጥልቀት በመመርመር የፖለቲካ ተቃውሞ ከላይ ለተቀመጡት ጥያቄዎች አዎንታዊ ምላሽ ይሰጥ እንደሆነ መወሰን ይኖርባቸዋል::

### 7.2. ዲሞክራሲን ስለማቀድ

የዓብይ ስትራቴጂው ዓላማ አምባገነኖችን ከሥልጣን ማውረድ ብቻ ሳይሆን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በመመሥረት አዲስ አምባገነን እንዳይፈጠር መከላከል መሆኑ ሊዘነጋ አይገባውም:: እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚመረጠው የትግል ሥልትም በህብረተሰቡ ውስጥ የተሻለ የሥልጣን ክፍፍል እንዲፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል:: በአምባገነኑ አገዛዝ ህብረተሰቡና ሲቪል ተቋማቱ እጅግ ደካማ ሲሆኑ በተቃራኒው መንግሥት ደግሞ እጅግ ጠንካራ ነው:: ይህ የኃይል ሚዛን መዛባት ሳይስተካከል አዲስ የሚፈጠሩ መሪዎች ከፈለጉ እንደቀድሞዎቹ አምባገነን ከመሆን የሚያግዳቸው ነገር የለም:: የቤተመንግሥት አብዮት ወይም መፈንቅለ መንግሥትም ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም::

በምዕራፍ አምስት እንደተመለከተው የፖለቲካ ትግል ህብረተሰቡን በማንቀሳቀስ በህብረተሰቡ ውስጥ ተመጣጣኝ የሆነ የሥልጣን ድልድል ለመፍጠር አስተዋፅዖ ያደርጋል:: ይህም ሂደት በብዙ መንገዶች ሊከሰት ይችላል:: የሰላማዊ ትግል አቅም መጐልበት ማለት የአምባገነኑ መንግሥት የኃይል ጭቆና ህብረተሰቡን በቀላሉ የማዋከብና ታዛዥ የማድረግ አቅሙን ያጣል ማለት ነው:: ህብረተሰቡም የአምባገነኑን መንግሥት የጭቆና እርምጃ ለመቋቋምና አንዳንድ ጊዜም ለመገደብ የሚያስችለው የራሱ ሀይል ይኖረዋል ማለት ነው:: ከዚህም በላይ በፖለቲካ ተቃውሞ መልክ የህብረተሰቡን ኃይል ማንቀሳቀስ መቻሉ የህብረተሰቡን ነጻ ተቋማት ያጠናክራቸዋል::

እንደዚህ ያለው ህዝባዊ ኃይል የሚያስገኘው የፖለቲካ ልምድም በቀላሉ አይረሳም:: በትግሉ ውስጥ የሚገኘው ዕውቀትና ልምድም ህብረተሰቡ ለሚመጡ አምባገነኖች በቀላሉ እንዳይንበረከክ ያደርገዋል:: ይህ በኃይል አሰላለፍ ረገድ የሚደረግ ለውጥ በመጨረሻው ዘላቂ ዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር ያለውን ዕድል አስተማማኝ ያደርገዋል::

### 7.3. <u>የውጪ ድጋፍ</u>

ዓብይ ስትራቴጂ በሚዘጋጅበት ጊዜ አምባገነኖችን ለማንበርከክ የሚደረገው የውስጥ ትግልና የውጪ ግፊት የሚኖራቸውን ተዛማጅ ሚና መገምገም አስፈላጊ ነው:: በዚህ ረገድ ዋናው ትግል ሀገር ውስጥ እንደሚሆን እምነት አለ:: ይህም ማለት ዓለማቀፍ ድጋፍ ጨርሶ ባይገኝም እንኳን የውስጡ ትግል መጠናከር የውጪ ግፊት ሊያነቃቃ እንደሚችል ይገመታል::

ለማሚያ ያህል፣ ዓለማቀፉ ህብረተሰብ በሰብአዊ ጉዳዮች፣ በሞራልና በሀይማኖት ረገድ በአምባገነኖች ላይ ግፊት እንዲያደርግ ማንቀሳቀስ ይቻላል:: ከዚህም በላይ የውጪ ሀገር መንግሥታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በአምባገነኑ መንግሥት ላይ ዲፕሎማሲያዊ፣ ፖለቲካዊና የኢኮኖሚ ጫናና ማዕቀብ እንዲጥሉ ጥረት ሊደረግ ይችላል:: እነዚህ እርምጃዎችም የኢኮኖሚና የጦር መሣሪያ ዕገዳ መጣል፣ የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ዝቅ ማድረግ ወይም ጨርሶ ማቋረጥ፣ የኢኮኖሚ ዕርዳታና የኢንቨስትመንት ፍሰትን ማገድ፣ አምባገነኑን መንግሥት ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ከተባበሩት መንግሥታት አካላት ጭምር ማባረርን የመሳሰሉ ሊሆኑ ይችላሉ:: ከዚህም በላይ የገንዘብ ዕርዳታና የመገናኛ ድጋፍ የመሳሰሉት ዓለምአቀፍ ዕርዳታዎች በቀጥታ ለዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ሊሰጡ ይችላሉ::



### 7.4. <u>ዓብይ ስትራቴጂ መቅረፅ</u>

ሁኔታውን በብቃት በመገምገም የትግሉን ዘዴ መምረጥና የውጪ ድጋፍ የሚኖረውን ሚና መወሰን የትግሉ ቀያሾች ትግሉ እንዴት ውጤታማ በሆነ መንገድ እንደሚካሄድ ማሰብ ይኖርባቸዋል:: የሚዘጋጀውም ዕቅድ ትግሉ ካለበት ደረጃ እስከ ነጻነትና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እስከ መመስረት ያለውን ሂደት የሚያጠቃልል መሆን አለበት:: ይህን ዓብይ ስትራቴጂ ለመቅረፅ የትግሉ ቀያሾች ራሳቸውን በርካታና የተለያዩ ጥያቄዎች መጠየቅ ይኖርባቸዋል:: የሚከተሉት ጥያቄዎች /ቀደም ሲል ካየነው ይልቅ ይበልጥ ዝርዝር በሆነ መልክ/ ለፖለቲካ ተቃውሞ ትግል ዓብይ ስትራቴጂ በማዘጋጀት መካተት ያለባቸውን ጉዳዮች ያመላክታሉ::

የረጅም ጊዜ ትግል እንዴት ቢጀምር ይመረጣል? ጭቁኑ ህዝብ ለመነሻ ያህል በተወሰነ መንገድም ቢሆን አምባገነኑን መንግሥት ለመቋቋም በራስ መተማመንና በቂ የሆነ ጥንካሬ እንዴት ሊያገኝ ይችላል? ህዝቡ ትብብር በመንፈግና በእምቢተኝነት ለመታገል ያለውን አቅም በሂደት እንዴት ሊያሳድገው ይችላል? በህብረተሰቡ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ቁጥጥር ለማድረግና የአምባገነኑን መንግሥት እንቅስቃሴ ለመገደብ የሚደረጉት የተወሰኑ ዘመቻዎች ዓላማቸው ምን ሊሆን ይችላል?

አምባገነኑን መንግሥት ተቋቁመው የዘለቁና ነጻነትን ለማምጣት ሊታገሉ የሚችሉ ነጻ ተቋሞች አሉ? አምባገነኑ መንግሥት ሥልጣን ላይ እያለ ከእጁ ፈልቅቆ ለማውጣት የሚቻሉ ወይም አዲስ ሊደራጁ የሚችሉና ዴሞክራሲያዊ ሁኔታዎችን ሊያጠናክሩ የሚችሉ ምን ዓይነት ተቋሞች ይኖራሉ?

በትግሉ ውስጥ ድርጅታዊ ጥንካሬ እንዴት ሊፈጠር ይችላል? ተሳታፊዎችስ እንዴት ሊሰለጥኑ ይችላሉ? በትግሉ ሂደት ምን ዓይነት

ግብዓቶች /የገንዘብ፣ የማቴሪያል ወዘተ.../ ያስፈልጋሉ? ህዝቡን ለማንቀሳቀስ ምን ዓይነት ውጤታማ ሊሆን የሚችል በአርኣያነት ሊታይ የሚችል ተግባር ያስፈልጋል?

የአምባገነኖች ኃይል ምንጭ ቀስ በቀስ እየተዳከመ ሊሟጠጥ የሚችለው በምን ዓይነት እርምጃና በምን በምን ደረጃዎች ነው? ተቃውሞ የሚያካሂደው ህዝብ ተቃውሞውንና የሰላማዊ ትግሉን ዲሲፕሊን በመጠበቅ እንዴት ትግሉን ጐን ለጐን ሊያስኬድ ይችላል? ማህበረሰቡ በትግሉ ሂደት መሠረታዊ ፍላጐቶቹን እንዴት ሊያሟላ ይችላል? በትግሉ ውስጥ ህግና ሥርዓት እንዴት ሊጠበቅ ይችላል? ድሉ እየተቃረበ ሲመጣ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች አምባገነኑ መንግሥት ከወደቀ በኋላ ለሚገነባው ሥርዓት ሽግግሩን እንዴት የተስተካከለ ሊያደርጉት ይችላሉ?

በአምባገነኖች ላይ ለሚካሄድ ለእያንዳንዱ የነጻነት ትግል ሊያገለግል የሚችል የተቀመረ ወይም ሊቀመር የሚችል የትግል ዘዴ እንደሌለ መዘንጋት የለበትም:: አምባገነኖችን ለማስወገድና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሚደረገው እያንዳንዱ ትግል አንዱ ከሌላው የተለየ ይሆናል:: ሁለት ፍፁም የተመሳሰሉ ነባራዊ ሁኔታዎች ያለመኖራቸውን ያህል እያንዳንዱ አምባገነንም የተለያዩ የራሱ ባህርያት ይኖሩታል፤ ነጻ ለመውጣት የሚታገለው ህዝብ አቅምም እንደዚሁ ይለያያል:: በመሆኑም ዓብይ የፖለቲካ ትግል ስትራቴጂ ቀያሾች ያለውን ተጨባጭ የግጭቱን ነባራዊ ሁኔታ በጥልቀት መረዳት ብቻ ሳይሆን በሚመርጡትም ትግል ዘዴ ላይ ጥልቅ ዕውቀት ሊኖራቸው ይገባል::

በጥንቃቄ የተዘጋጀ ዓብይ የትግል ስትራቴጂ በህዝቡ በስፋት እንዲታወቅ የማድረግ አስፈላጊነትም በቂ ምክንያቶች አሉት:: ከእነዚህም በትግሉ ውስጥ የሚሳተፉ በርካታ ሰዎች አጠቃላይ ፅንሰ ሀሳቦችንና ዝርዝር መመሪያዎችን ቢረዱ ለመሳተፍ ፈቃደኛና ብቁ ሊሆኑ



መቻላቸው ይገኝበታል:: በጉዳዩ ላይ የሚኖራቸው ዕውቀት ሞራላቸውን ከፍ ሊያደርገው፣ ፈቃደኝነታቸውን ሊያጐለብተውና በአግባቡ ተግባር ላይ እንዲያውሉት ሊያግዛቸው ይችላል:: የትግሉ ዓብይ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በአምባገነኖች ቢታወቅም የሚያስከትልባቸውን የፖለቲካ ተቃውሞ በመረዳት የሚፈፅሙትን ጭካኔና ጭቆና እንዲያላሉ ያደርጋቸዋል:: የዓብይ ስትራቴጂው ልዩ ልዩ ባህርያት በገዥው መደብ ሠፈር መታወቁ በመካከሉ ተቃውሞ ለመቀስቀስና አንዳንድ አባላቱ እንዲያፈነግጡ ዕድል ይሰጣል::

አምባገነኖችን ለማስወገድና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመስረት የሚካሄደውን ትግል የሚመራ ዓብይ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ከተነደፈ በኋላ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ ይገባቸዋል:: ከተቀረፀው ስትራቴጂ ለመውጣት የሚቻለው አስገዳጅ ሁኔታዎችና ልዩ አጋጣሚዎች ሲፈጠሩ ብቻ ይሆናል:: የተመረጠው ዓብይ ስትራቴጂ በአግባቡ ግንዛቤ ያልተያዘበት መሆኑ በቂ መረጃ ሲኖር ወይም ትግሉ የሚካሄድበት ተጨባጭ ሁኔታ መሠረታዊ ለውጥ ማድረጉ ሲረጋገጥ ዓብይ ስትራቴጂው ለውጥ ሊደረግበት ይችላል:: እዚህ ደረጃ ላይ ከተደረሰ በኋላ እንኳን ዕቅዱ ሊሻሻል የሚችለው መሠረታዊ ግምገማ ከተካሄደና አዲስ የተሟላ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ተነድፎ ከፀደቀ በኋላ መሆን ይኖርበታል::

## 7.5. <u>የዘመቻ ስትራቴጂዎች መንደፍ</u>

አምባገነን አገዛዝን ለመጣልና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመመሥረት የሚነደፈው ዓብይ ስትራቴጂ ምንም ያህል በሳልና ተስፋ የሚጣልበት ቢሆንም ወደ ግብ መቃረቢያ እንጂ ራሱ ግብ ስላልሆነ ውጤት እንዲገኝ በሥራ መተርጐም ይኖርበታል:: የአምባገነኑን ኃይል በማፍረክረክ ላይ የሚያልሙና በመመሪያነት የሚያገለግሉ ልዩ

ስትራቴጂዎች መነደፍ ይኖርባቸዋል:: እነዚህ ስትራቴጂዎች በተራቸው በአምባገነኖች ላይ ወሳኝ ምት የሚያሳርፉ ሥልታዊ ግዳጆችን ያካትታሉ:: ተግባሩን የሚመሩት ሥልቶቹና ዘዴዎቹ ለእያንዳንዱ ስትራቴጂያዊ ግብ ተፈጻሚነት አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ በጥንቃቄ መመረጥ አለባቸው:: እዚህ ላይ የምናካሂደው ውይይት በስትራቴጂ ደረጃ ብቻ የተወሰነ ይሆናል::

የዘመቻ ስትራቴጂዎችን የሚያቅዱ ሰዎች ዓብይ ስትራቴጂውን እንደሚነድፉት ሰዎች ሁሉ የተግባሩን ባህርይና ዘዴ በጥልቀት መገንዘብ ይኖርባቸዋል:: የጦር ስትራቴጂ የሚነድፉ መኮንኖች የሚያዙትን ሠራዊት አወቃቀር፣ ሥልት፣ ሎጅስቲክስ፣ ጦር መሣሪያ፣ የመልክአ ምድር ተፅዕኖና የመሳሰሉትን በጥልቀት መረዳት እንደሚገባቸው ሁሉ፣ የፖለቲካ ተቃውሞ ዕቅድ የሚነድፉ ሰዎችም የሰላማዊ ትግሉን ባህርይና ስትራቴጂያዊ መርሆዎች በጥልቀት መረዳት አለባቸው:: ይሁንና፣ ያም ሆኖ ግን የሰላማዊ ትግል ዕውቀት፣ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ለቀረቡ ሀሳቦች የሚሰጥ ትኩረት እንደዚሁም እዚህ የተነሱ ጥያቄዎች ብቻቸውን ስትራቴጂዎችን ሊያመነጩ አይችሉም:: ለትግሉ ስትራቴጂዎችን ለመንደፍ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ፈጠራ አስፈላጊ ነው::

ለተወሰኑና የተመረጡ የተቃውሞ ዘመቻዎችና ለነጻነት ትግሉ የረጅም ጊዜ ትግል የሚያገለግሉ መመሪያዎች ለመንደፍ የፖለቲካ ተቃውሞ ስትራቴጂ ነዳፊዎች በርካታ ጉዳዮችንና ችግሮችን ማገናዘብ ይኖርባቸዋል:: ከእነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል::

- የተመረጡት የዘመቻ ግቦች ለዓብይ ስትራቴጂው መተግበር የሚያደርጉትን አስተዋፅዖ መወሰን፣
- ለተመረጡት ስትራቴጂዎች የሚስማሙ ዘዴዎች ወይም የሚጣጣሙ የፖለቲካ መሣሪያዎችን ማገናዘብ፣ በእያንዳንዱ ልዩ የዘመቻ ዕቅድ ውስጥ ምን ዓይነት አነስተኛና ሥልታዊ ዘዴዎች



ተግባር ላይ እንደሚውሉና የአምባገነኑን ሥልጣን በመገደብ ግፊት እንደሚፈጥሩ መወሰን ያስፈልጋል:: የዓብይ ግቦች ተግባራዊነት የአነስተኛ እርምጃዎች በጥንቃቄ መመረጥና መተግበር ውጤት መሆኑም ሊዘነጋ አይገባም::

- ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች ባጠቃላይ የፖለቲካ ትግል ውስጥ እንዴት ይዛመዱ እንደሆነ መወሰን ያስፈልጋል:: የኢኮኖሚ ጥያቄዎች በትግሉ ወስጥ ጉልህ ቦታ እንዲይዙ ከተፈለገ አምባገነኑ አገዛዝ ከተወገደ በኋላ ብሶቶቹ መፍትሄ እንደሚያገኙ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: ይህ ካልሆነ ግን በሽግግሩ ጊዜ ፈጣን መፍትሄዎች ካልተሰጡ ብዥታና እምነት ማጣት ሊከሰት ይችላል:: የዚህ ዓይነቱ ብዥታ መፈጠርም ለኢኮኖሚ ብሶቶች መፈታት ተስፋ እንሰጣለን በሚል ሽፋን አምባገነኖች እንደገና ሊፈጠሩ ይችላሉ::
- ትግሉን ለመጀመር ምን ዓይነት የአመራር መዋቅርና የመገናኛ ሥርዓት ሊኖር እንደሚገባ በቅድሚያ መወሰን ያስፈልጋል:: ከዚህም በላይ ለተቃዋሚዎችና በአጠቃላይ ለህዝቡ፣ በትግሉ ሂደት ምን ዓይነት ተከታታይ ውሳኔ አሰጣጥና የግንኙነት ዘዴ እንደሚያስፈልግ መወሰን ይኖርበታል::
- በአጠቃላይ ለህዝቡ፣ ለአምባገነኑ የጦር ሠራዊትና የፖሊስ ኃይሎች እንደዚሁም ለዓለም አቀፍ የብዙሀን መገናኛዎች ትግሉ የደረሰበትን ደረጃ ማሳወቅ ያስፈልጋል:: በዚህም ሂደት የሚሰጠው መረጃ ምን ጊዜም ቢሆን በእውነታ ላይ የተመሠረተ መሆን ይገባዋል:: በዚህ ረገድ የሚፈጠር ማጋነንና መሠረት የሌለው የድል ብሥራት ትግሉን ተአማኒነት ያሳጣዋል::
- በቀጣዩ የትግል ሂደት የህዝቡን ፍላጐት ለማሟላት በራስ መተማመን የተመላበት የማህበራዊ፣ የትምህርት፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማድረግ እንዲቻል አስቀድሞ ማቀድ

ያስፈልጋል:: እንደዚህ ዓይነት ኘሮጀክቶች በትግሉ ወስጥ በቀጥታ በማይሳተፉ ሰዎች ሊካሄዱ ይችላሉ::

- የሚካሄደውን ልዩ ዘመቻ ወይም አጠቃላይ ትግል ለመደገፍ እንዲቻል ምን ዓይነት የውጭ ዕርዳታ መቀበል እንደሚገባ መወሰን ያስፈልጋል:: በሀገር ውስጥ የሚካሄደው ትግል አስተማማኝነት በማይኖረው በውጪ ድጋፍ ላይ ጥገኛ ሳይሆን እንዴት ሥራ ላይ ሊውል ይችላል? የትኞቹ የውጪ ቡድኖች ትግሉን ለማገዝ ይበልጥ እንደሚጠቅሙ መወሰን ያስፈልጋል:: ለምሳሌ ያህል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች /ማህበራዊ ድርጅቶች፣ የሀይማኖት ተቋማት፣ የፖለቲካ ቡድኖች፣ የሠራተኛ ማህበራት ወዘተ.../ መንግሥታትና ወይም የተባበሩት መንግሥታት እንደዚሁም የተባበሩት መንግሥታት ልዩ ልዩ አካላት ሊሆኑ ይችላሉ::

ከዚህም በላይ በአምባገነኖች ላይ ሰፊ መሠረት ያለው የህዝብ መነሳሳት በሚፈጠርበት ጊዜ ህግና ሥርዓት ለማስከበርና ማህበራዊ ፍላጐቶችን ለማሟላት ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው:: ይህም ሲሆን ከአምባገነኑ መንግሥት ቁጥጥር ነጻ የሆኑ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት ለመፍጠርና ሀቀኛ የህዝብ ፍላጎቶችን ለማሟላት ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ህግና ሥርዓት በሚጣስበት ጊዜ ህግና ሥርዓት ለማስከበር የኃይል ጭቆና ያስፈልጋል የሚባለውን አስተሳሰብ ዋጋ ለማሳጣት ይጠቅማል::

## 7.6. ትብብር የመንፈግን ፅንሰ ሀሳብ ማሰራጨት

ለተሳካ ፀረ አምባገነን የፖለቲካ ተቃውሞ ህዝቡ ትብብር የመንፈግን ፅንሰ ሀሳብ እንዲገነዘብ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: በምዕራፍ ሶስት «በዝንጀሮዎች ጌታ» ተምሳሌትነት እንደቀረበው ሀሳቡ ቀላል ነው:: የከፋ ጭቆና ቢኖርም ሥርዓቱን የተሸከሙት ብዙ ሰዎች ለረጅም ጊዜ



ለሥርዓቱ ትብብር ከነፈጉት ጨቋኙ ሥርዓት ተዳክሞ በመጨረሻም መውደቁ አይቀርም::

በአምባገነኖች ሥር የሚኖሩ ሰዎች ከተለያየ አቅጣጫ ለዚህ ፅንሰ ሀሳብ አዲስ ላይሆኑ ይችላሉ:: ያም ቢሆን እንኳን ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ትብብር የመንፈግን ፅንሰ ሀሳብ በበቂ ሁኔታ በህዝቡ ውስጥ ማሰራጨት አለባቸው:: የዝንጀሮዎች ጌታን ዓይነት ወይም ተመሣሣይ ታሪኮች በህብረተሰቡ ውስጥ በሥፋት ሊሰራጩ ይችላሉ:: ሰዎች እንደዚህ ያለውን ታሪክ በቀላሉ ከመረዳታቸውም በላይ አይረሱትም:: ትብብር የመንፈግ ፅንሰ ሀሳብ ሥር ከሰደደ በኋላ ህዝቡ ከአምባገነኖች ጋር ለሚደረገው ፍልሚያ ጥሪ ሲደረግለት እንግዳ አይሆንበትም:: ከዚህም በላይ ህዝቡ እንደሁኔታውና እንደአስፈላጊነቱ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ተጨባጭ የሆኑ በርካታ ትብብር የመንፈግ የትግል ዓይነቶችን ሊቀይስ ይችላል::

ምንም እንኳን በአምባገነኖች ሥር አስቸጋሪ ቢሆንና አደጋ ባይለየውም ሀሳብ ለመለዋወጥ፣ መረጃ ለመስጠትና ትዕዛዝ ለማስተላለፍ እንደሚቻል በተደጋጋሚ ተረጋግጧል:: በጀርመን ናዚዎችና በኮሚኒስቶች አገዛዝ ዘመን እንኳን ግለሰቦች ከግለሰብ ጋር ብቻ ሳይሆን ብዙ ህዝብ በተገኘበት መድረክ ላይ በህቡዕ በሚታተሙ ጋዜጦች፣ በበራሪ ወረቀቶች፣ በመፃህፍት እንደዚሁም በኋለኞቹ ዓመታት ደግሞ በድምፅና በቪዲዮ ካሴቶች ጭምር ሀሳብ መለዋወጥ ተችሎ ነበር::

በቅድሚያ በሚቀረፅ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ አማካይነት አጠቃላይ የትግሉ መርሆዎች ተዘጋጅተው ሊሰራጩ ይችላሉ:: እነዚህም ህብረተሰቡ መቃወም ያለበትንና ትብብር መንፈግ ያለበትን ጉዳዮች እንዴት ሊተገብራቸው እንደሚችልም የአፈጻጸም ሁኔታዎችን ያሳዩታል:: ከዴሞክራሲያዊ አመራሩም ግንኙነት ቢቋረጥና የተወሰኑ ትዕዛዞች ባይዘጋጁ ወይም ባይላኩ እንኳ በአንዳንድ ጠቃሚ ጉዳዮች ላይ

ህብረተሰቡ ምን ማድረግ እንዳለበት ይገነዘባል:: እንደዚህ ዓይነት መመሪያዎች የአምባገነኑ መንግሥት ፖሊስ ትንኮሳ ለማካሄድና ትግሉን ዋጋ ለማሳጣት ከሚያዘጋጃቸው የማሳሳቻ መመሪያዎች እውነተኞቹን ለመለየት ያስችላሉ::

## 7.7. ጭቆናና የአፀፋ እርምጃዎች

ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ነዳፊዎች አምባገነኑ መንግሥት በትግሉ ሂደት ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ለሚወስዱት እርምጃ የሚሰጠውን አፀፋና በተለይም የኃይል እርምጃ ለመውሰድ የሚችልበትን ሁኔታ በሚገባ መገምገም አለባቸው:: ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ለአምባገነኑ ጭቆና ሳይንበረከኩ እንዴት መቋቋም፣ አፀፋ እርምጃ መውሰድ ወይም የከፋ ጭቆና ውስጥ እንዳይገቡ የሚያመልጡበትን መንገድ መወሰን አለባቸው:: በሥልት ረገድ በተወሰኑ አጋጣሚዎች ላይ ህዝቡና በትግሉ ተሳታፊ የሆኑ ሰዎች ሊያጋጥማቸው ስለሚችል አፈና በቅድሚያ እንዲያውቁ ማድረግ በተሳትፎ ላይ ሊያጋጥማቸው የሚችለውን አደጋ እንዲገምቱ ይጠቅማቸዋል:: የሚያጋጥመው የኃይል እርምጃ ጠንካራ ከሆነ ለሚቆስሉ ተሳታፊዎች ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል::

እንደዚህ ዓይነቱ የኃይል እርምጃ ሊያጋጥም እንደሚችል አስቀድሞ ሲገመትም ስትራቴጂ ቀያሾቹ ወደተመረጠው ግብ የሚያደርስ ሥልትና ዘዴ ብቻ ሳይሆን እንደዚህ ያለው ግልጽ የኃይል እርምጃ እንዳይከሰት ሊያደርጉ ይችላሉ:: ለምሳሌም ያህል የለየላቸውን አምባገነኖች ለመቃወም በመንገድ ላይ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰልፎች አስደናቂ ሊሆኑ ቢችሉም በሺህ የሚቆጠሩ ሙታን ሊያጋጥሙ ይችላሉ:: ይሁንና ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ የሚከፈለው መስዋዕትነትና የሚገኘው ውጤት ሁሉም ሰው በቤቱ በመቅረት፣ ሥራ በማቆም ወይም ሰፊ



መሠረት ያለው ትብብር የመንፈግ ድርጊት ወይም በመንግሥት ሠራተኞች የሚፈፀም ሰፊ ትብብር የመንፈግ ተግባር በአምባገነኖች ላይ ከሚፈጥረው ግፊት ያነሰ ነው::

ዓላማው ትንኮሳ የሆነ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትል የሚችል የተቃውሞ እርምጃ ስትራቴጂያዊ ለሆነ ዓላማ የሚፈለግ ቢሆንም የሚገኘውን ጥቅምና የሚደርሰውን ጉዳት በጥንቃቄ ማመዛዘን ያስፈልጋል:: በዚህ ዓይነቱ የትግል ጊዜ ተቃዋሚዎችና ህዝቡ ሰላማዊ በሆነና ዲሲፕሊን በጠበቀ መንገድ መታገል ይችላሉ? ከአምባገነኑ መንግሥት በኩል የኃይል እርምጃ እንዲወስዱ የሚደርስባቸውን ትንኮሳስ መቋቋም ይችላሉ? የትግሉ ቀያሾች የከፋ የኃይል እርምጃ ቢደርስባቸውም የሰላማዊ ትግል ዲሲኘሊን ተጠብቆ ትግሉ እንዲቀጥል ምን እርምጃዎች መወሰድ እንዳለባቸው ማሰላሰል ይጠበቅባቸዋል:: እንደ ቃል መግባት፣ የፖሊሲ መግለጫ መስጠት፣ የዲሲኘሊን በራሪ ወረቀቶች መበተን፣ የሰላማዊ ሰልፍ መሪዎች መኖር፣ አመፅን የሚደግፉ ቡድኖችን ትብብር መንፈግ የሚሳኩና ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ? በመጨረሻም የትግሉ መሪዎች ሰላማዊ ትግሉን የኃይል አቅጣጫ እንዲይዝ ተልዕኮ ካላቸው ምንደኞችና ተንኳሾች ተጠንቅቀው መጠበቅ አለባቸው::

## 7.8. በስትራቴጂያዊ ዕቅዱ መተማመን

የተሟላ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ከፀደቀ በኋላ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ከዓብይ ስትራቴጂውና ከአንድ የዘመቻ ስትራቴጂ እንዲወጡና ጠቃሚ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩሩ ከአምባገነኑ መንግሥት በኩል የሚደረግባቸውን ግፊት መቋቋም አለባቸው:: ከዚህም ሌላ ምናልባትም ከአንድ የአምባገነኑ መንግሥት የኃይል እርምጃ ጋር በተያያዘ የሚፈጠር ስሜታዊነት ትግሉን ከዓብይ ስትራቴጂውም ሆነ ከዘመቻ ስትራቴጂው

አቅጣጫ እንዳያስለውጠው መጠንቀቅ ይገባል:: በአምባገነኑ መንግሥት በኩል የኃይል እርምጃ በመውሰድ ተቃዋሚ ኃይሎች መሠረት የጣሉበትን ሰላማዊ የትግል አቅጣጫ እንዲተውና እንዲያውም የኃይል እርምጃ እንዲወስዱ በመተንኮስ በቀላሉ እንዲሸነፉ የተወጠነ ሴራ ሊኖር ይችላል::

ትግሉ የሚመራበት ስትራቴጂ ትክክለኛ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ተግባር ደረጃ በደረጃ ወደፊት መግፋት መሆን አለበት:: ያም ሆኖ ግን በሥልትና በመዳረሻ ግቦች ረገድ ለውጥ መኖሩ ባይቀርም በሳል መሪዎች ምንጊዜም አዳዲስ ዕድሎችን ከመጠቀም ወደኋላ አይሉም:: እነዚህ ማስተካከያዎችም ከዓብዩ ስትራቴጂ ግቦች ወይም ከአንድ የዘመቻ ግብ ጋር መምታታት የለባቸውም:: የተመረጠው ዓብይ ስትራቴጂና የልዩ ልዩ ዘመቻ ስትራቴጂዎች በጥንቃቄ በሥራ መተርጐምም ለስኬት ታላቅ አስተዋፅዖ ያደርጋል::



# ምዕራፍ ስምንት

## ፖለቲካዊ ተቃውሞ /መተግበር/

አቅመቢስነትና ፍርሃት ያደረበት ህዝብ ያለባቸው ተቋማት፣ ፖለቲካዊ ተቃውሞ በማካሄድ ረገድ በራስ የመተማመን ችሎታቸውን ለማሳደግ በቅድሚያ አነስተኛ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ተግባራትን ማከናወን ይገባቸዋል:: ተግባራቱም፣ ልብስን ባልተለመደ ሁኔታ መልበስ፣ /ለምሳሌ ሁሉም ሰው ጥቁር የሀዘን ልብስ ለተወሰኑ ቀናት ቢለብስ/፣ የተቃውሞ ሀሳብ በማቅረብ ህዝቡ ያንን እንዲከተል ማመቻቸት ሊሆን ይችላል:: በሌላ በኩልም ለምሳሌ ህዝቡ ውኃ እንዲያጠራቅም፣ /ማገዶ እንዲያከማች፣ ቀለብ እንዲሸምት/ መገፋፋት ለቡድናዊ ተግባራዊ ተሳትፎ ይረዳል፣ ያነሳሳል:: የሚዘረጉት ስትራቴጂዎችና የሚወስዱት እርምጃዎች ሁሉ በህዝቡ ተቀባይነት እንዲያገኙ የተመረጡና የሚታመንባቸው መሆን አለባቸው:: እንዲህ ዓይቶቹን ውስን ዘመቻዎች በተሳካ ሁኔታ ማካሄድ ከተቻለ የተወሰኑ ቅሬታዎችን ከማጥራቱና ከማስተካከሉም በላይ ህዝቡ እርግጥ ኃይል ያለው መሆኑን እንዲረዳ ያደርገዋል::

በረጅሙ የትግል ጉዞ ውስጥ የሚነደፈው ስትራቴጂ ዓላማ የአምባገነኖች መውደቅ፣ መወገድ በአጭር ጊዜ ይፈፀም ዘንድ የሚሰናዳ ሳይሆን፣ በምትኩ የተወሰኑ ግቦችን በማሳካት ላይ ሊሆን ይገባል:: ወይም ሁሉም ዓይነት የተቃውሞ ዘመቻዎች ጠቅላላ የህዝቡን ተሳትፎ ሁሌም የሚጠይቁ መሆን አይገባቸውም::

ታላቁን ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ውስን ስትራቴጂዎችን በማውጠንጠን የተቃውሞ ብልሃቶች ነዳፊዎች ዘመቻው በመጀመሪያው፣ በመካከሉና በፍጻሜው ላይ ያሉ ልዩ ልዩ እርምጃዎች

ተመሣሣይ እንዳልሆኑ ማስተዋል ይገባቸዋል:: አንዱ ደረጃ ከሚቀጥለው የተለየ ሥፋትና ጥልቀት ይኖረዋልና::

## 8.1. ተቃውሞን መምረጥ/መርጦ መቋቋም/

በትግሉ የመጀመሪያ ወቅት ልዩ ልዩና የተወሰነ ዓላማ ያላቸውን ሰላማዊ የተቃውሞ ዘመቻዎች ማድረግ እጅግ ጠቃሚ ነው:: እንዲህ ዓይነቶች የተመረጡ የተቃውሞ ዘመቻዎች በተከታታይ ሊደረጉ ይችላሉ:: አንዳንድ ጊዜ ሁለት ወይም ሦስቱ ሊደራረቡ ይችላሉ::

ምርጥ የተቃውሞ እርምጃ ለመውሰድ ሲታቀድ የአምባገነኑን ጨቋኝነት ሊያሳዩ የሚችሉ ውስንና ምርጥ ቅሬታዎችንና ጉዳዮችን ነጥሎ ማውጣት ይገባል:: እንዲህ ዓይነቶቹ ጉዳዮች ምናልባትም ወደዋናው ስትራቴጂ የሚያደርሱ መካከለኛ ግቦች ሊያስገኙ ይችላሉ::

እነዚህ የመካከለኛ ስትራቴጂዎች ዓላማዎች በዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ወቅታዊ አቅምና ችሎታ መመሥረት አለባቸው:: ይህን ማድረግም በሞራል ግንባታ ረገድ መልካም ዕድል የሚያጐናጽፉ ተከታታይ ድሎች ያስገኛሉ፤ እንዲሁም ለረጅሙና ለዘለቄታው ትግል በኃይል ሚዛኑ በኩልም ተጨማሪ ግፊትና አቅም እንዲኖር ያደርጋሉ::

በዋናነት የተመረጡ ተቃውሞዎች ሊያተኩሩባቸው የሚገቡ የተወሱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ ጉዳዮች መሆን ይገባቸዋል:: ይህም የሚጠቅመው የተወሰነውን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሥርዓት ከአምባገነኑ ቁጥጥር ለመነጠል፣ በአምባገነኑ የተያዙትን የተወሰኑ ክፍሎች መልሶ ለመያዝ ወይም የአምባገነኑን የተለየ ዓላማ ለመቃወምና፣ ላለመቀበል ሊሆን ይችላል:: የተመረጡ የተቃውሞ ዘመቻዎች የሚደረጉት፣ ከተቻለ ቀደም ሲል በተዘረዘሩት የአምባገነኑ ሥርዓት ድክመቶች በአንዱ ወይም በበርካታዎች ላይ ሊሆን ይችላል::



በዚህም ዲሞክራሲያዊ ኃይሉ፣ ባለው አቅምና ኃይል ውጤታማ ተግባር ሊያከናውን ይችላል::

ገና ከመነሻው ዕቅድ አውጪዎች ለመጀመሪያው የተቃውሞ ዘመቻ የሚሆን ስትራቶጂ መንደፍ ይገባቸዋል:: የተወሰኑ ዓላማዎች ምን ሊሆኑ ይገባል? ለተመረጠው ዋና ስትራቴጂ ምን ድጋፍ ይሰጣሉ? የሚሉና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ:: ከተቻለም የሁለተኛና የሦስተኛው ደረጃ ስትራቴጂዎች አጠቃላይ ንድፍ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል:: እነዚህ ሁሉ ስትራቴጂዎች አጠቃላዩንና ዋናውን ስትራቴጂ ከሚያሳኩ መርሆዎች ጋር ተጣጥመው መሰናዳት ይጠበቅባቸዋል::

## 8.2. ተምሳሌታዊ ግፍጫ

አምባገነናዊ አገዛዙን ለማንኳሰስ የሚያስችል አዲስ ሰላማዊ ዘመቻ ሲታቀድ መደረግ ያለበት የመጀመሪያው ተግባር በተወሰነ ደረጃ የሚከናወን ፖለቲካዊ እርምጃ መሆን አለበት:: የህብረተሰቡን አስተሳሰብና መንፈሳዊ ይዞታ በሚፈትን፣ በሚጐተጉትና በሚያነቃቃ መልኩ መቀየስ አለበት:: እንዲሁም ትግሉን በቀጣይነት ለማካሄድ ትብብርን ለሚነፍግ ፖለቲካዊ ተቃውሞ የሚያሰናዳ መሆን ይጠበቅበታል::

የመጀመሪያው ተግባር ተምሳሌታዊነት ያለባቸው ውስን የተቃውሞ እርምጃዎች ምናልባትም ውስንና ጊዜያዊ ትብብርን የመንፈግ እንቅስቃሴዎች ሊሆኑ ይችላሉ:: በመነሻው ላይ የሚሳተፉ ሰዎች ቁጥር አናሳ ከሆነ፣ ተምሳሌታዊነት ባላቸው ቦታዎችና አካባቢዎች ላይ አበባ በማስቀመጥ ሊጀመር ይችላል:: በሌላ በኩል ደግሞ የተሳታፊዎቹ ቁጥር በርካታ ከሆነ ለተወሰኑ ደቂቃዎች እንቅስቃሴዎችን መገደብ /5 ደቂቃ/ ወይም ባሉበት ሁኔታና ቦታ ለብዙ ደቂቃዎች ፀጥ ማለት ሊሆን ይችላል:: በሌላ ሁኔታም አንዳንድ ግለሰቦች የርሃብ አድማ ሊያደርጉ

ይችላሉ፣ ተምሳሌታዊነት ባላቸው ቦታዎችም በመሰብሰብ ሊፀልዩ፣ ሊጠብቁ ይችላሉ፣ ተማሪዎች ትምህርት ሊያቆሙ ወይም ጠቀሜታ ባላቸው ቢሮዎችና ተቋማት አካባቢ ለተወሰነ ጊዜ ቁጭ ሊሉ ይችላሉ:: እንደዚህ ዓይነቶቹ እርምጃዎች ግን ከአምባገነናዊ አገዛዙ እጅጉን ጭካኔ የተሞላበት ምላሽ ሊያስከትሉ እንደሚችሉ መገመት ይገባል::

በአምባገነናዊው አገዛዝ ቤተመንግስት አካባቢና በፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ አካባቢ የሚደረጉ ተምሳሌታዊ እርምጃዎችና ዘመቻዎች ብዙውን ጊዜ ከፍተኛ ጉዳት ስለሚያስከትሉ እንዲደረጉ አይመከርም::

በበርማ በ1988 እንደተደረገው ያለ ህዝባዊ የጐዳና ላይ ሰልፍ፣ በ1989 በቤጂንግ ታይናንሜን አደባባይ እንደተደረገው የተማሪዎች አድማ ያሉ ተምሳሌታዊነት ያላቸው ተቃውሞዎች ትልቅ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ትኩረትና ድጋፍ ሊያስገኙ ይችላሉ:: በነዚህ ቦታዎች የደረሱት ከፍተኛ የህይወት ጥፋቶች እንዲህ ዓይነት የተቃውሞ ዘመቻ ለማድረግ ለሚያቅዱ ስትራቴጂ ነዳፊዎች ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የሰጡት ትምህርት አለ::

እንደዚህ ዓይነቶቹ እርምጃዎች ምንም እንኳ ሞራላዊና ሥነ-ልቦናዊ ተፅዕኖ ቢኖራቸውም/ቢያስገኙም በራሳቸው አምባገነናዊ አገዛዙን ሊያስወግዱ አልበቁም:: ይልቁንም በተምሳሌትነት ከመጠቀስ በላይ የአምባገነኑን የሥልጣን አቋም ለመተካት/ለመለወጥ አላስቻሉም::

በትግሉ መጀመሪያ ላይ የአምባገነኑን አገዛዝ የሥልጣንና የኃይል ምንጭ ማንጠፍ አይቻልም:: አገዛዙን ለመቃወምና በጠንካራ ተቃውሞ እምቢ ለማለት ቀደም ሲል ባመዛኙ አሜንና እሺ ብለው ይገዙ የነበሩትን፣ የህዝቡንና የማህበራዊ ተቋማቱን ከፍተኛ ጥረትና ትብብር ይጠይቃል:: ያ ካልሆነ ከግብ ለመድረስ እጅግ በጣም አስቸጋሪ ነው:: ስለዚህ፣ አብዛኛውን ጊዜ ሙሉ በሙሉ ያለመተግበር ሥልት መቀየስ



ተግባራዊ የማይሆንና ከወቅቱ ጋር የማይጣጣም ፀረአምባገነናዊ ዘመቻ ይሆናል::

## 8.3. ኃላፊነትን ማከፋፈል

የተመረጡ የተቃውሞ ዘመቻዎች በተወሰኑ ወይም በበርካታ የህብረተሰቡ ክፍሎች ላይ የማይፈለግ ውጤት ሊያመጡ ይችላሉ:: ይሁንና ልዩ ልዩ ዓላማዎች ያሏቸው ተከታታይ ዘመቻዎችና ቀጣይ ዘመቻዎች ሊወሰዱ ይችላሉ:: በዚህን ጊዜ በትግሉ ምክንያት የሚደርሰው ጫና ወደሌሎች ሊዞር ይችላል:: ለምሳሌ ተማሪዎች በትምህርት ጉዳይ ላይ ሰላማዊ ሰልፍ ሊያደርጉ፣ የሃይማኖት መሪዎች የሃይማኖት ነጻነትን ሊያነሱ፣ የትራንስፖርት /የባቡርና የአውቶቡስ ጣቢያ ሠራተኞች/ በመንገዣ ጥገናና አቅርቦት ላይ ጥያቄ ሊያነሱና ሥራቸውን ሊያጓትቱ፣ ጋዜጠኞች በሳንሱር ምክንያት እንዳይታተሙ በተደረጉ ገጾችና አምዶች ላይ በጥቁር የተሸፈነ ባዶ ገጽ ሊያትሙ፣ ፖሊሶች ዲሞክራሲያዊ የተቃውሞ ኃይላትን እያደኑ ማሰር ሁሉ ሊሳናቸው ይችላል:: የተቃውሞ ዘመቻውን በእንዲህ ዓይነቱ በየጉዳዩ በተከፋፈለ ደረጃ ማካሄድ ህዝቡን በየወገኑ ፋታ ሊያስገኙለት ይችላል::

የተመረጠ የተቃውሞ እርምጃ ጠቃሚ የሚሆነው፣ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ ከአምባገነኑ አገዛዝ ነጻ የወጡ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተቋማትን በተለይ በመከላከልና በመጠበቅ ነው:: እነዚህ ነጻ ማዕከላት በአምባገነኑ አገዛዝ ላይ ተፅዕኖ ለማሳደርም ሆነ ጭቆናውን ለመቋቋም የሚያስችሉ ተቋማዊ ኃይል ያስገኛሉ:: በትግሉ ሂደት ውስጥም የአምባገነን አገዛዙ የመጀመሪያ ዒላማ ውስጥ ከሚገቡት ተቋማት ውስጥ የሚመደቡ መሆናቸውም ሊዘነጋ አይገባውም::

### 8.4. በአምባገነኑ ሥልጣን ላይ ማለም

የረጅም ጊዜ ትግሉ ከመነሻ ስትራቴጂው ይበልጥ እየጐለበተ በሄደ መጠን የትግሉ መሪዎች የአምባገነኑ አገዛዝ ኃይል ምንጭ ይበልጥ ውስንና ደካማ እየሆነ የሚሄድበትን ሥልት መቀየስ/ማሰላሰል ይገባቸዋል:: ዓላማውም ዲሞክራሲያዊ ኃይሎቹ ይበልጥ የሚያመቻቸውን አዲስ ኃይል ለመፍጠር የሚያስችል ህዝባዊ ያለመተባበርን/ትብብር ነፈጋን በመጠቀም ላይ ሊያነጣጥር ይችላል::

የዲሞክራሲያዊ ተቃውሞው ኃይሎች እየጠነከሩ በሄዱ መጠን፣ የትግሉ ስትራቴጂ ቀያሾች ከፍ ያለ ውጤት በሚያስገኝ እንቅስቃሴ ላይ ሊያተኩሩ ይገባቸዋል:: የተገኙትን ድሎች እየጠበቁ የአምባገነኑን የኃይል ምንጭ እያደከሙና፣ ፖለቲካዊ ሽባነት እንዲፈጠርበት እያደረጉ በመጨረሻም አምባገነናዊ አገዛዙ እንዲፍረከረክ በሚያስችል ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች ላይ ማነጣጠር ይጠበቅባቸዋል::

ህዝቡና አንዳንድ ቡድኖች ለአምባገነናዊ አገዛዙ ቀደም ሲል ይሰጡት የነበሩትን ድጋፎች በማዳከም ረገድ በጥንቃቄ አልሞ መነሳት ተገቢ ነው:: የእነዚህ ተባባሪ አካላት ድጋፍ የሚዳከመው/የሚቀነሰው የአገዛዙን ጭካኔና አረመኔያዊ ድርጊት በማጋለጥ ነው? የአምባገነኑ አገዛዝ ፖሊሲ ያደረሰውን ኤኮኖሚያዊ ጥፋት በማጋለጥ ነው? ወይስ በሌላ የማስረጃ ዘዴ ለአምባገነናዊ አገዛዙ የሚደረገውን ድጋፍ ማዳከም ይቻላል? ብሎ ማለም ይገባል:: የአምባገነኑ ደጋፊዎች ቢያንስ ገለልተኛ አቋም እንዲይዙ፣ ከፍ ሲልም የዲሞክራሲያዊ ኃይሉ እንቅስቃሴ ደጋፊዎች እንዲሆኑ መጣጣር ያስፈልጋል::

ወታደራዊ ኃይሉ፣ ከተራ ወታደር እስከመኮንኖቹ ድረስ ያሉት፣ ለአምባገነናዊ አገዛዙ ያላቸው ታማኝነት እስከምን ድረስ እንደሆነ መጠናት አለበት፤ በዲሞክራሲያዊ ኃይሉ ተፅዕኖ ሊደረግበት ይቻል እንደሆን በሚገባ ተገምግሞ ሊጤን ይገባል:: ምናልባት በርካታ



ወታደሮች ምልመላውን ሊፈሩ ይችሉ ይሆን? ምናልባትስ አብዛኞቹ ወታደሮችና መኮንኖች በግል፣ በቤተሰብ፣ ወይም በፖለቲካ ምክንያት የተገለሉ ይሆኑ? ወታደሮቹንና መኮንኖቹን ለዲሞክራሲያዊ አካሄድ ምቹ እንዲሆኑ የማያሰናዳቸው ሌላ ምን ምክንያት ይኖር ይሆን? ተብሎ በጥንቃቄ መጠናት አለበት::

ከአምባገነናዊ አገዛዝ ነጻ ለመውጣት በሚደረገው ትግል ከመጀመሪያ ደረጃ ጀምሮ በወታደራዊ ዕዝና አገልግሎቱ ላይ ልዩ ትኩረት የሚያደርግ ስትራቴጂ መንደፍ ያስፈልጋል:: በልዩ ልዩ ዘዴ ማለትም በመፈክር፣ በምልክት፣ በተግባራዊ እንቅስቃሴዎችና እርምጃዎች አማካይነት የነጻነት ትግሉ ተጠናክሮ እንደሚደገፍ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎቹ ለወታደሮቹና ለተቋማቱ ማስገንዘብና ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል:: ወታደሮቹ ትግሉ አምባገነናዊ አገዛዙን የማስወገድ እንጂ የእነሱን ግላዊ ህይወት የሚነካና የሚጐዳ አንዳችም ዓላማ እንደሌለው ሊያውቁና ሊረዱ ይገባቸዋል፤ ይህ ዓይነቱ ጥረት የአምባገነናዊ አገዛዙን ወታደሮች ሞራል በማላሸቅ ድጋፋቸውን ወደ ዲሞክራሲያዊ ኃይሉ እንዲያዞሩና ትብብራቸውን እንዲያሳዩ ሊያደርግ ይችላል:: በፖለቲካዊና ሲቪል ሠራተኞችም ላይ ተመሳሳይ ተግባራት መከናወን አለባቸው::

ደጋፊ የማበርከቱና የአምባገኑን አገዛዝ ኃይል የማዳከሙ ተግባር ተጠናክሮ በዘላቂነት መቀጠል ያለበት ነው:: ወታደራዊ ኃይሉም የአምባገነናዊ አገዛዙን ዕድሜ በወታደራዊ እርምጃ በአጭር እንዲቀጨውም መሥራት ይጠበቃል:: እንዲህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ /ትልም/ ምናልባት ላያዋጣ ይችላል:: ቀደም ሲል እንደጠቀሰው ምናልባት ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት በህዝቡና በአገዛዙ መካከል የኃይል ሚዛኑን በማዛባት ረገድ ያለው ድርሻ አነስተኛ ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ የዲሞክራሲያዊ ኃይሉን በመደገፍ ረገድ ቀና አመለካከት

ያላቸውን ወታደራዊ መኮንኖች በማዘጋጀት በምን ዓይነት መልኩ አምባገነናዊ አገዛዙን ለማስወገድ ይረዳሉ ተብሎ ሊጠና የሚገባው ጉዳይ ነው:: እዚህ ላይ ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥትም ሆነ ህዝባዊ አመፃ እንዲደረግ ሲወሰን ደም መፍሰስ በፍጹም እንዳይከሰት ተግቶ መሥራት ይጠይቃል፤ ማሳመንና ማስገንዘብም ይገባል::

ለዲሞክራሲያዊ ኃይሉ ድጋፍና ርህራሄ ያላቸው ወታደራዊ መኮንኖችና በወታደራዊ ኃይሉ ውስጥ ቅሬታዎችን በማሰራጨትና ትብብርን በመንፈግ፣ ሥራን ሆን ብሎ በማጓተትና ትዕዛዝን ባለመቀበል፣ እንዲሁም ጭቆናንና የኃይል እመቃን በመቃወም ለዲሞክራሲያዊ ትግሉ ጠቃሚ ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ:: ወታደራዊ መሪዎች ለዲሞክራሲያዊ ኃይሉ የእምቢተኛነት ተቃውሞ ልዩ ልዩ አዎንታዊ ድጋፍ ሊያበረክቱ ይችላሉ፤ ማለትም ነጻ መንቀሳቀሻ አካባቢ፤ መረጃ፣ ምግብ፣ መድኃኒትና የመሳሰሉትን ዕርዳታና ድጋፎች ሊያስገኙ ይችላሉ::

ለአምባገነናዊ አገዛዙ ወታደራዊ ኃይሉ እምቢተኛውን ህዝብ ለመቅጣት ወታደራዊ ዕዝንና መሣሪያውን ለመጠቀም የሚያስችለው የኃይል ምንጭ በመሆኑ፣ እጅጉን ጠቃሚው ነው:: በዚህም የተነሳ የተቃውሞ ስትራቴጂ ነዳፊዎች ሊጠነቀቁበት የሚገባው ጉዳይ፣ ወታደራዊ ኃይሉ፣ ፖሊሱ፣ ቢሮክራሲያዊ መዘውሩ ሁሉ ለአምባገነናዊ አገዛዙ ሙሉ ድጋፋቸውን በሚሰጡበት አኳኋን የሚደረጉ የእምቢታ ተቃውሞዎች ውጤት ሊያስገኙ አለመቻላቸውን ነው:: ስለዚህ ከሁሉ አስቀድሞ የአምባገነናዊ አገዛዙን ደጋፊዎች በማስከዳት ተግባር ላይ በቅድሚያ ማለምና ብልሀት ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል::

በወታደራዊና በፖሊስ ሥርዓት ውስጥ አለመታዘዝና ማመጽ በአባላቱ/ግለሰቦቹ ላይ/ከፍተኛና አሰቃቂ ቅጣት የሚያስከትሉ መሆናቸውን ዲሞክራሲያዊ ኃይሎቹ መገንዘብ ይኖርባቸዋል:: ወታደሮችም ሆኑ ፖሊሶች ምንም ዓይነት የእምቢተኝነት



መንፈስ/ድርጊት/ ቢያሳዩ በክህደት ተወንጅለው ሊገደሉ ይችላሉ:: ስለዚህ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎቹ ወታደሮቹም ሆኑ መኮንኖቹን ፈጣን የሆነ ምላሽ ሊጠይቋቸው አይገባም:: ይልቁንም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም፣ ከአደጋ ነጻ የሆኑ ድብቅ የተቃውሞ/ የእምቢተኛነት እርምጃዎች በመውሰድ እንዲጀምሩ ማነሳሳት ይቻላል:: ለምሳሌ ፖሊሶችና ወታደሮች የዕመቃ እርምጃ እንዲወስዱ ሲታዘዙ በአግባቡ አለመፈፀም፣ ተፈላጊ ሰው እንዲይዙ ሲታዘዙ ፈልጎ አለመያዝ፣ ተቃዋሚዎችን ሊታሰሩ፣ ሊታፈኑ ወይም ሊሰደዱ እንደሚችሉ መረጃ በማቀበል ማስጠንቀቅ፣ የደረሱበትን ጠቃሚ መረጃም ለበላዮቻቸው በቅድሚያ ያለማሳወቅ እርምጃዎችን በመውሰድ ዲሞክራሲያዊ ኃይሉን ሊተባበሩ ይችላሉ:: ቅሬታ የገባቸው የበላይ ኃላፊዎችና መኮንኖች የጭቆናና የዕመቃ ትዕዛዛዊ ሰንሰለቶችን ወደታች ሳያሳልፉ ይችላሉ:: ወታደሮችም በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ወደሰማይ በመተኮስ ሊተባበሩ ይችላሉ፤ በተመሳሳይ ሁኔታም ሲቪል ሠራተኞች በበኩላቸው፣ ትዕዛዞችንና እንቅስቃሴዎችን በማጓተት ሥራን ሊያዳክሙ ይችላሉ፤ በ«ህመም» ምክንያትም እስከሚሻላቸው ድረስ ከቤታቸው ሊቀመጡ ይችላሉ::

## 8.5. <u>ስትራቴጂ መለወጥ</u>

የፖለቲካ ተቃውሞ ስትራቴጂ አውጭዎች ዋናው የትግል ስትራቴጂና ውስን የትግል ዘመቻዎች እንዴት እየተከናወኑ እንደሆነ ዘወትር መገምገምና መመዘን ይገባቸዋል:: ለምሳሌ ትግሉ እንደሚጠበቀውና እንደታሰበው ሳይከናወን /ሳይፈፀም/ ይችላል:: በዚህም ጊዜ በተነደፈው ስትራቴጂ ላይ ሊደረጉ የሚገቡ ለውጦችን ማሰብ ያስፈልጋል:: እንቅስቃሴውን አጠናክሮ ለመቀጠልና እርምጃውን ለማፋጠን ምን መደረግ ይኖርበታል? በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ

የትግሉን ችግር መርምሮ መረዳት፣ የተነደፈውን ስትራቴጂ እንደገና መመርመር፣ ትግሉን እንዲያከናውኑ ኃላፊነት የተሰጣቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች መሰወጥ፣ ተጨማሪ የኃይል ምንጭ ማንቀሳቀስና ተሰዋጭ የትግል ሥልት መቀየስ ሁሉ እጅጉን አስፈላጊዎች ናቸው:: ይህ ሁሉ ከተከናወነ በኋላ፣ በዚህ መሠረት የተሠናዳው አዲሱ ዕቅድ በፍጥነት ወደተግባር መሰወጥ አለበት::

ትግሉ በዚህ ዓይነት ከተቀጣጠሰና ከተጠበቀውም ጊዜ በፊት ውጤታማ እየሆነ ሄዶ አምባገነዊ አገዛዙ ፈጥኖ ከተፈረካከሰ፣ ዲሞክራሲያዊ ኃይሉ የተገኘውን ያልተጠበቀ ድል ይዞ እንዴት ወደፊት ሊገፋበት ይችላል የሚሰው የሚያነጋግር ነው:: ይህንኑ ጉዳይ በሚቀጥሰው ምዕራፍ እንዳስሰዋለን::



# ምዕራፍ ዘጠኝ

## እምባገነናዊነትን ማናጋትና ማፈራረስ

በሚገባ የተከናወነ የፖለቲካዊ ተቃውሞ ዘመቻ ጥቅል ውጤት የህብረተሰቡን ትግል ሲያጠናክርና ሲያስፋፋ፣ የአምባገነን ገዢዎችን የቁጥጥር አቅም ደግሞ ይገድባል:: እንዲሁም የተቃውሞ ዘመቻው፣ ከአምባገነኖች ጋር የሚኖር ትብብርን እንዴት መመከት እንደሚቻልና ፖለቲካዊ ተቃውሞ እንዴት ማካሄድ እንደሚቻል ልምድ ይሰጣል፣ ያስገኛል:: ይህም ልምድ ሁሉን አቀፍ/ብዙኃን አቀፍ የሆነ ትብብር ነፈጋንና ተቃውሞን ለማጧጧፍ እጅግ ጠቃሚ ድጋፍ ይሰጣል::

በምዕራፍ ሦስት ውስጥ እንደተብራራው ለጨቋኙ አካል እሺ ባይነት፣ ተባባሪነትና አጉራጠናኝ ማለት አምባገነኖች የሥልጣን ኃይል እንዲያገኙ ማገዝ ማለት ነው:: አምባ ገነኖች፣ የሥልጣን ምንጭ ወደሆነው ህዝብ መድረስ ካልቻሉ ኃይላቸው ይደክማል፣ በመጨረሻም ይበተናሉ፣ ይሟሟሉም:: ስለዚህ ድጋፍን መንፈግ ማለት አምባገነንነትን ለመበታተንና ለማንበርከክ ተገቢ እርምጃ እንደሆነ መታወቅ አለበት:: ዲሞክራሲያዊ ኃይሉ የሥልጣንና የኃይል ምንጭ የሆነውን ህዝብ እንዴት የፖለቲካዊ ተቃውሞ ተጽዕኖ ሊያደርግበት እንደሚችል መቃኘትና መገምገም አለበት::

ተምሳሌታዊነት ያለው እምቢባይነት ወይም ተቃውሞ የአገዛዙን ሞራላዊና ፖለቲካዊ ሥልጣን በማራከስ፣ በማዋረድና የህጋዊነት መሠረቱን በማሳጣት ረገድ ሊወሰዱ ከሚገባቸው እርምጃዎች ውስጥ አንዱ ነው:: የአገዛዙ የሥልጣን የበላይነት ከፍ ባለ መጠን እሺባይነትንና ተባባሪነትን እያገኘ መሄዱ አይቀርም:: ስለዚህ የአምባገነናዊነትን አቋምና ሞራል ለማናጋትና ለማፈራረስ ሰላማዊ እምቢተኛነት በተግባር መታየትና መገለጽ አለበት:: ተባባሪነትንና እሺ

ባይነትን መንፈግ የአገዛዙን የሥልጣን ኃይል ምንጮችን ማዳከምና ማሳነስም ጭምር ነው።

ለአገዛዙ ሥልጣን ሌላው ደጋፊ የሰው ኃይል ምንጩ ነው። የሚታዘዙ፣ የሚተባበሩና የሚረዱ በርካታ ሰዎች መኖር ለገዢዎች ድጋፍ ነው። በህዝቡ ውስጥ አብዛኛው አምባገነኖችን የማይተባበራቸው ከሆነ አገዛዙ በከፋ ችግር ውስጥ ይወድቃል። ለምሳሌ ሲቪል ሠራተኞች ሥራቸውን በተለመደው ትጋትና ቅልጥፍና የማይሰሩ ቢሆን ወይም በቤታቸው ቢቀሩ አስተዳደራዊ መዋቅሩ ቅጣንባሩ ይጠፋል።

በተመሣሣይ ሁኔታም፣ የማይተባበሩት ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ቀደም ሲል ለአገዛዙ በሰለጠኑበት ክህሎትና ዕውቀት ሲያገለግሉ የነበሩትን ወገኖች በተቃውሞው ካካተቱ አምባገነኖች ፍላጐታቸውን የማስፈፀም አቅማቸው ጨርሶ ይዳከማል። በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ ለማሳለፍም ሆነ ውጤታማ ፖሊሲ ለማውጣት ያላቸው ችሎታ ከፉኛ ይጐዳል።

ህዝቡን ወደ ተገዢነትና ታዛዥነት ወይም ወደ ደጋፊነት የሚገፉፉት፣ የሚመሩት ረቂቅ ህሊናዊ ጉዳዮች፣ የሚባሉት የሥነ-ልቦናዊና የርዕዮተዓለማዊ መሠረቶች ከተሸረሸሩና ከተስተካከሉ፣ ወይም በተፃራሪው እንዲሰሩ ከተደረጉ ገዢዎች ይበልጥ ይዳከማሉ። ይልቁንም ህዝቡ አልታዘዝም፣ አልገዛም፣ አልተባበርም ወደማለቱ እያደላና እምቢተኛነቱ እያደገ ይሄዳል።

አምባገነኖች ለሀብት ምንጭ ያላቸው ዕድል የሥልጣናቸው ዋነኛ ኃይል ነው። ስለዚህም፣ የገንዘብ ተቋማትን፣ የኢኮኖሚ መዋቅርን፣ ንብረትን፣ የተፈጥሮ ሀብትን፣ የመጓጓዣና የመገናኛ ዘዴዎችን በአገዛዝ ሥርዓቱ ተቃዋሚዎች ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ከተደረገ አምባገነናዊ ሥርዓቱ ክፉኛ መጐዳቱ ወይም መወገዱ አይቀርም። እንዲሁም ሰላማዊ ሰልፎች፣ አድማዎች፣ ቀጣይነት ያላቸው ኢኮኖሚውንና መገናኛ



ውን ነጻ የማውጣት ተግባራት ያገዛዝ ሥርዓቱን ከመሠረቱ ለማናጋት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉ።

ቀደም ሲል እንደተብራራው፣ የአምባገነኖች አቅም የሚገለፀው ሥርዓቱን ፋታ በሚነሱና ትብብር በሚነፍጉ ሰላማዊ አመፀኞች ላይ ሲሆን ይኸውም በማስፈራራት፣ በአገታ ወይም በቅጣት ሊሆን ይችላል። ይህም የአምባገነን ሥልጣን ዋና መገለጫ ነው። ይህን የሥልጣን ኃይል ተግባር በሁለት መንገድ ማዳከም ይቻላል። አንዱ፣ ህዝቡ ራሱ ራሱን በጦርነት ውስጥ እንዳለ አድርጐ ከቆጠረና በሚያደርገው ተቃውሞ ምክንያት የሚፈፀምበትን ማናቸውንም ዓይነት በደሎች ለመቋቋም ከተዘጋጀ ሊደርስበት የነበረው ጉዳት ሊቀንስ ወይም ሊወገድ ይችላል። አምባገነኖችም እርምጃቸው ውጤት አልባ ይሆንባቸዋል። የፈለጉትንም አያገኙም። ሁለተኛው፣ የፖሊሱና የወታደሩ ኃይል በግልም ሆነ በትብብር በዚህ ሰላማዊ ህዝባዊ አመጽ ከተነሳሳ ገዢዎች የሚያዙትን ተቃዋሚዎችን የማሰር፣ የመደብደብና የመግደል ትዕዛዝ አልቀበልም፣ እምቢ ሊል የመቻሉ ጉዳይ ነው። አምባገነኖች በፖሊስና በወታደር አማካይነት የጭቆና ሥርዓታቸውን ለማካሄድ ካልቻሉ አምባገነንነታቸው ክፉኛ ይጠቃል። ይፍረከረካል።

ለማጠቃለል ያህል፣ የአምባገነኖችን ምሽግ ለማስወገድ በአንጻሩ የሚቆም ትብብርን የመንፈግና የመቃወም ትግል ያስፈልጋል። አምባገነናዊነት የራሱን የሥልጣን ኃይል በዘላቂነት ማስቀጠል ስለሚያዳግተውም ይዳከማል፣ በመጨረሻም ይበታተናል። ከዚህ አኳያ በአምባገነናዊነት አንጻር/ተቃራኒ የሚነደፍ ብልሃትና ዘዴ፣ የታሰበበት፣ የታቀደና በወጉ የተሰናዳ ፖለቲካዊ ተቃውሞ ሊኖር ይገባዋል። ይህ ፖለቲካዊ ተቃዋሚ ዋነኛ ዓላማው አድርጐ መነሳት ያለበት ያገዛዙን የሥልጣንና የኃይል ምንጭ ነው።

## 9.1. ነፃነትን ማጉልበት፣ ማስፋፋት

በተመረጡ የትግል ደረጃዎች ከፖለቲካው ተቃውሞ ጋር አብሮ መከናወን ያለበት ነጻ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ተቋማትን ማሳደግ ነው። ይህም በበኩሉ የህዝቡን «ዲሞክራሲያዊ ይዞታ» ሲያስፋፋ፣ የአምባገነኖችን የቁጥጥር አቅም ያከስምናል። ከአምባገነኖቹ አንጻር የህዝቡ ተቋማት እየጠነከሩ በሄዱ ቁጥር አምባገነኖቹ ወደዱትም ጠሉት ህዝቡ ከእነሱ ውጭ የነጻነቱን ህንፃ እየገነባና እያሳደገ ይሄዳል። አምባገነኑ ይህን «የነፃነት ግንባታ» እገታለሁ፣ እከላከላለሁ ብሎ ሲነሳ የተገኘውን አዲስ የነጻነትና የዲሞክራሲ ይዞታ ለመከላከል፣ ሰላማዊ ህዝባዊ እምቢተኝነት በተግባር ማዋል/ማፋፋም/ ይገባል። በዚህም ጊዜ አምባገነናዊነት ሌላ የተቃውሞና የትግል ግንባር ይገጥመዋል ማለት ነው።

በሂደትም፣ በተቃውሞ የመመከቱና የነጻነቱ ተቋም መጠናከር የማይቀረው እውነተኛ ነጻነት፣ የአምባገነኖችን መፈረካከስና፣ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እውን ይሆናሉ። ምክንያቱም በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው የኃይል/ሥልጣን ግንኙነት ተለውጧልና ነው።

በ1970ዎቹና በ1980ዎቹ በፖላንድ የተደረጉት የተቃውሞ እርምጃዎች የህብረተሰቡን ያገልግሎት ተቋማት መልሶ ለመያዝ ያስቻሉ ዓይነተኛና ግልጽ ምሳሌዎች ናቸው። የካቶሊክ ቤ/ክርስቲያን በአገዛዙ ስትሰቃይ ብትቆይም ሙሉ በሙሉ በኮሚኒስቱ ሥርዓት ቁጥጥር ውስጥ ሊያደርጉት አልቻሉም። በ1976 የተወሰኑ ምሁራንና ሠራተኞች የፖለቲካ አመለካከታቸውን ማራመድ የሚያስችላቸውን ኮሚቴ /የሠራተኞች መከላከያ ኮሚቴ ዓይነት/ በአነስተኛ ቡድኖች አማካይነት መሠረቱ። የሠራተኞች አንድነት ማህበር ድርጅት ውጤታማና ተግባራዊ ሰላማዊ ተቃውሞ/አድማ በማድረግ በ1980 ህጋዊነቱን



ተቀዳጀ። ገበሬዎች፣ ተማሪዎች፣ ሌሎች በርካታ ቡድኖችም የራሳቸውን ነጻ ድርጅቶች አቋቋሙ። እነዚህ ቡድኖች የሥልጣኑን አቋም እንደለወጡት በተረዱ ጊዜ ኮሚኒስቶቹ የአንድነት ማህበሩን ዘጉት፤ ኮሚንስታዊ ወታደራዊ አገዛዝ ሰፈነ።

የህብረተሰቡ ነጻ ተቋማት በወታደራዊ አገዛዝ ህግ በርካታ እሥሮችና መንገላታቶች ቢደርስባቸውና፣ አሰቃቂና ኢ-ሰብአዊ እርምጃዎች ቢወሰድባቸውም፣ የተቃውሞ ተግባራቸውን ግን አላቋረጡም ነበር። ለምሳሌም፣ በርካታ ጋዜጦችና መጽሔቶች በህቡዕ እየታተሙ ይሠራጩ ነበር። በህቡዕ የተቋቋሙ ማተሚያ ቤቶች በዓመት በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ መጻሕፍትን ሲያሳትሙ፣ በጣም ታዋቂና ምስጉን ደራሲዎችና ፀሐፊዎች በኮሚኒስቱና በመንግሥት ማተሚያ ቤቶች ላይ አደሙ፣ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችም ተመሣሣይ እርምጃዎች መውሰዳቸውን ቀጠሉ።

በአንድ ወቅትም በያሩስልስኪ ወታደራዊ አገዛዝ፣ የወታደራዊው ኮሚኒስት መንግሥት በህብረተሰቡ አናት ላይ ተቀምጦ የሚያናጥር ተቋም ተደርጐ መገለጽ ተጀመረ። ባለሥልጣኖች የመንግሥትን ቢሮዎችና ህንፃዎች እንደያዙ ቀጠሉ። አገዛዙ በህብረተሰቡ ውስጥ የጭቆና ክንዱን መጫኑን ተያያዘው፤ የመቅጣት፣ የማሰር፣ የማጋዝ፣ ማተሚያ ቤቶችን የመውረስና የመሳሰሉትን እርምጃዎች የመውሰድ ተግባሩንም ገፋበት። ይሁንና አምባገነናዊነት ማህበረሰቡን ሙሉ በሙሉ ሊቆጣጠረው አልቻለም። ይህ ሁሉ ሲሆን ህብረተሰቡ ያገዛዝ መዋቅሩን ጨርሶ ለማስወገድ የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነበር የሚጠብቀው።

አምባገነናዊ አገዛዙ የመንግሥትን ሥልጣን በያዘበት አኳኋንም እንኳ ቢሆን ትይዩ/አቻ ዲሞክራሲያዊ መንግሥትን መመሥረት የሚቻል ጉዳይ ነው። ይህም እንደተቃዋሚ መንግስት፣ ተፎካካሪ ተቋም ጠንክሮ የሚንቀሳቀስ፣ ከህዝቡም አመኔታን፣ ተባባሪነትን፣ ደጋፊነትን

እያገኘ የሚቀጥል ይሆናል:: አምባገነናዊ አገዛዝም በአኳያው ተለጣጣቂነትና ተከታታይነት ባለው አኳኋን የመንግሥትነት ባህርይውን እያጣ ይሄዳል:: አሲያም የተቋቋመው ትይዩ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት በሽግግር መንግሥት ሥርዓት ሥልጣኑን ሊረከብ ይችላል:: በሂደትም በሽግግሩ ወቅት ህገ-መንግሥት ሊሰናዳና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሊከናወን ይችላል::

## 9.2. አምባገነናዊነትን ማፈራረስ

የህብረተሰቡ ተቋማዊ ለውጥ እየተካሄደ ባለበት ወቅት፣ ተቃውሞና ትብብርን የመንፈግ እንቅስቃሴዎች እየጨመሩና እየጐለበቱ መሄድ አለባቸው:: የዴሞክራሲያዊ ትግል መርህ ነዳፊዎች ማሰብ ያለባቸው በአገዛዙ ላይ ከሚደረጉ ውሱን የተመረጡ የተቃውሞ እርምጃዎች የዘለለና ጠንከር ያለ ሀገር አቀፍ ተቃውሞ ለማድረግ መዘጋጀትንም ነው:: አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ ዓይነቱን ሀገር አቀፍ ህዝባዊ ተቃውሞ ለማዘጋጀትና፣ ለማቋቋም፣ የተቃዋሚ ኃይላትንም ብቃት ለመገንባት በቂ ጊዜ ይጠይቃል:: ምናልባትም ዓመታት ሊፈጅ ይችላል:: በዚህ የዝግጅት ጊዜ ግን የተመረጡ ተቃውሞዎች ከአመርቂ የፖለቲካ ዓላማ ጋር በተከታታይ መካሄድ አለባቸው፤ በየደረጃው የሚገኘው የህብረተሰብ ክፍልም ጠንክሮ መሳተፍ አለበት:: ቆራጥነትና ሥርዓታዊነት የተሞላባቸው ፖለቲካዊ የተቃውሞ እርምጃዎች እየጐለበቱ ሲሄዱ የአምባገነናዊ አገዛዙ ውስጣዊ ድክመት እየጐላ መምጣቱ እያደር ገሀድ ይወጣል::

የጠንካራ ፖለቲካዊ ተቃውሞና የነጻ ድርጅቶች ምሥረታ ተባብሮና ተደጋግፎ መከናወንም በጊዜው ለዴሞክራሲያዊ ኃይሉ ደጋፊ የሆነ ሰፊ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ያስገኝለታል:: እንዲሁም በአምባገነናዊ አገዛዙ ላይ ዓለምአቀፍ ዲፕሎማሲያዊ ውግዘትን፣



ማዕቀቦችንና ተቃውሞዎችን ሊያስከትል ይችላል/በፖላንድ እንደተደረገው/:: ይህም ዲሞክራሲያዊ ኃይሉን በመደገፍ ረገድ ጠቀሜታው የላቀ ነው::

የትግል መርሁ ነዳፊዎች /ስትራቴጂስቶች/ በ1989 በምሥራቅ ጀርመን እንደሆነው ሁሉ፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች አምባገነናዊ አገዛዞች በቶሎ ሊፍረከረኩ እንደሚችሉ ማሰላሰል አለባቸው:: ይህ ሊሆን የሚችለው የሥልጣን ምንጭ የሆነው ኃይል በምሉዕነት ህዝባዊ ንቅናቄውን ለማገዝ ሲንቀሳቀስ ነው:: ይህ ጉዳይ ሁሌም የሚያጋጥም ባይሆንም፣ ለአጭር ጊዜውም መዘጋጅቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለረጅም ጊዜ ትግል አቅዶ መሠናዳቱ የተሻለ ነው::

በነጻነት ትግል ሂደት ውስጥ የተገኙ ድሎች አነስተኛና ውስን ቢሆኑም እንኳ፣ መከበርና መዘከር አለባቸው:: ድሉን ያገኙና ያስገኙ መመስገንና ተገቢውን ክብር ማግኘት ይገባቸዋል:: በቆራጥነት የታጀበ የድል ክብር ወደፊት ለሚደረገው ያላሰለሰ ትግል አስፈላጊውን የሞራል ብርታት እንደሚያጐናጽፍ ይታወቃል::

## 9.3. ስኬትንና ድልን በወጉ መያዝ

የትግል መርሁ ነዳፊዎች ትግሉ ስኬታማ እንዲሆን የሚያስችለውንና የሚያመቸውን ዘዴ ሁሉ ማሰላሰል ይገባቸዋል፤ እንዲሁም አዳዲስ አምባገነኖች እንዳይፈጠሩ እየተንቀሳቀሱ ዘላቂነት ያለው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲመሠረት አበክረው መትጋት ይኖርባቸዋል::

ዲሞክራቶች በትግሉ መጨረሻ ከአምባገነን ወደ ጊዜያዊ መንግሥት የሚደረገውን ሽግግር ዓይነትና መልክ ማሰላትና ማቀድ አለባቸው:: መንግስታዊ መዋቅሩ በአስቸኳይ ሥራውን እንዲቀጥል ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ዳሩ ግን በአዳዲስ ሠራተኞች አሮጌው ሥርዓት

መቀጠል የለበትም:: የትኛው የአሮጌው መንግሥታዊ መዋቅር /ፖለቲካዊ ፣ ፖሊስ/ ለአዲሱ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አደናቃፊ እንደሆነና መፍረስ እንዳለበት፣ የትኛው ደግሞ ደጋፊ እንደሆነና ሊቀጥል እንደሚገባው በውል መጤን አለበት:: አሮጌውን መንግሥታዊ መዋቅር እንዳለ ዋጋቢስ ማድረግ፣ ለረብሻና ለሽብር ምናልባትም ለአዲስ አምባገነናዊ መንግሥት ወደሥልጣን መምጣት መንገድ ሊያመቻች ስለሚችል ጥንቃቄ መደረግ አለበት::

አምባገነናዊ መንግሥቱ ሲወገድ የከፍተኛ ባለሥልጣናቱ ዕጣፈንታ በቅድሚያ መታየትና መወሰን የሚገባው ጉዳይ ነው:: ለምሳሌ፣ አምባገነናዊ ገዢዎቹ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ? ለዘለቄታውስ ከሀገር እንዲሰደዱ ይደረጋሉ? ከድሉ ቀጥሎ ከፖለቲካዊ ተቃውሞው ጋር ተጣጥመው የሚሄዱ ሀገርን መልሶ ለመገንባትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን ለማጠናከር ምን ሌሎች አማራጮች ይኖሩ ይሆን? ያም ሆነ ይህ ለወደፊቱ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አደገኛ ፈተናና አስጊ የሆነ የደም መፍሰስ ግን ፈፅሞ መካሄድ የለበትም:: ተቀባይነትም አይኖረውም::

አምባገነናዊ ሥርዓቱ ሲዳከም ወይም ሲፈረካከስ ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚያሸጋግሩ ዝርዝር ተግባራት አስቀድሞ መታለም አለባቸው:: እንዲህ ዓይነቶቹ ዕቅዶች፣ በመንግሥት ግልበጣ መንገድ ወደሥልጣን ለመምጣት የሚፈልጉ ሌሎች ቡድኖችን ለመከላከል ይረዳሉ:: ዕቅዶች ለህገ-መንግሥታዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት መሠረት የሚሆኑ፣ ሙሉ ፖለቲካዊና ግላዊ ነጻነትን የሚያጐናጽፉ ሊሆኑ ይገባል:: ታላላቅ ዋጋዎች የተከፈሉበት የትግል ውጤት በተገቢ የአፈፃፀም ዕቅድ አለመዘጋጀት ሊታጣ አይገባውም:: ሊሰናከልም ከቶ አይቻልም::

ለነጻነታቸው ቆርጠው የተነሱና ለመብታቸው የሚታገሉ ህዝቦች ኃይል እየጨመረና ነጻ ዲሞክራሲያዊ ቡድኖችና ተቋማት እየበረከቱና



እያደጉ በመጡ ቁጥር አምባገነኖች አጠቃላይ ፍጥርጥራቸው፣ ምስጢራቸውና ተንኮላቸው እየተጋለጠባቸውና እየተቃወሰባቸው እንደሚመጣ እያወቁት ይሄዳሉ:: አጠቃላይ የማህበረሰቡ እንቅስቃሴዎች መዘጋት፣ አጠቃላይ አድማዎች፣ አጠቃላይ በቤት መከተት፣ የተቃውሞ ጉዞዎችና ሌሎች ብዙሀን አቀፍ እርምጃዎች የአምባገነኖችን ድርጅታዊ መዋቅሮችና ተጓዳኝ ተቋሞች ያራክሷቸዋል፤ ያጣጥሏቸዋል:: እንዲህ ዓይነቶቹ ተቃውሞዎችና ትብብርን የመንፈግ ሂደቶች /አለመተባበሮች/ በብዙሀኑ ተሳትፎ ታጅበው በሥነ-ሥርዓትና በብልሀት ለረጅም ጊዜ ከተካሄዱ አምባገነኖች ኃይልና ሥልጣን አልባ ይሆናሉ:: ዲሞክራሲያዊ ታጋዮችም አለምንም አመጽ/የኃይል ተቃውሞ/ ያሸንፋሉ፤ ድልም ይቀዳጃሉ::

ነገር ግን ሁሉም እንዲህ ዓይነቶቱ ጥረቶች አይሳኩም፤ በተለይም በቀላሉና በፍጥነት አይሆኑም:: ብዙ ወታደራዊ ጦርነቶችና ሽንፈቶች እንደ ድል እንደሚቆጠሩ ሊታወስ ይገባዋል:: ይሁንና ፖለቲካዊ ተቃውሞ ለእውነተኛ ድል የሚያበቃ ነው:: ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ብልህነት የተሞላበት ታላቅ የትግል መርህ ማድረግና መስፋፋት፣ ጥንቃቄ የተሞላበት ዕቅድ፣ ጠንካራ ሥራና ሥነ-ሥርዓታዊ አበረታች ትግል ለድል የማብቃቱ ዕድል የሰፋ ነው::

# ምዕራፍ አሥር

## ለዘላቂ ዲሞክራሲ የመሠረት ድንጋይ መጣል

የአምባገነን ሥርዓት መፈረካከስ በእርግጥ መከበር የሚገባው ነው። ለረጅም ጊዜ በጭቆና የማቀቁና ታላቅ ትግል ያደረጉ ሁሉ የደስታ፣ የመዝናናትና የመዘከር /የመታሰብ/ ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል። የፖለቲካ ነጻነትን በማስገኘት ሂደት አብረዋቸው ለታገሉና ለራሳቸውም ኩራት ሊሰማቸው ይገባል። ነገር ግን ያችን የነጻነት ቀን ለማየት ሁሉም አይታደሉም። ያገራቸውን ነጻነት ለመቅረፅና ለማስተከል የተሳተፉ ሁሉ፣ የተሰውትም ሆኑ ያሉት ተገቢው ክብርና መታሰቢያ ሊደረግላቸው ያስፈልጋል።

ይህ ጊዜ ብርታትን የሚያላሉበት ወቅት አይደለም። የተዋጣለት፣ የተሳካ የአምባገነኑ ሥርዓት መወገድ ቢፈጠርም በውዥንብሩና በትርምሱ ውስጥ ሌላ አፋኝና ጨቋኝ ሥርዓት እንዳያቆጠቁጥና ወደ ሥልጣን እንዳይመጣ በእጅጉ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፤ የአፍቃሪ ዲሞክራሲው መሪዎች ትክክለኛ የሽግግር ሂደት እንዲኖር በቅድሚያ በቂ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የአምባገነኑ ሥርዓት መዋቅሮች ሊወገዱ ይገባል። ህገ-መንግሥታዊና ፍትሃዊ መሠረቶችና የዘላቂ ዲሞክራሲ ባህርያት በወግና በሥነ-ሥርዓት መገንባት አለባቸው።

አምባገነናዊ ሥርዓት እንደተፈረካከሰ ወዲያውኑ አልጋ በአልጋ የሆነ ማኅበራዊ ሥርዓት ይገኛል ብሎ ማንም ሊጠብቅ አይገባውም። የአምባገነኑ ሥርዓት መፈረካከስ የሚሰጠው ጥቅም፣ በተሟላ ነጻነት ውስጥ ሆኖ በበቂ ሁኔታ የህብረተሰቡን ሕይወት ለማሻሻልና የሰውን ልጅ ፍላጎት ለማሟላት የረጅም ጊዜ ጥረት ለማድረግ ዕድል መስጠቱ ነው። ብርቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች ለዓመታት



ይቀጥላሉ። ለመፍትሄያቸውም የሕብረተሰቡን የተሟላ ትብብር የሚሹ ይሆናሉ። የወደፊቱን ችግር በማስወገድ ረገድ ገንቢ ሥራዎችን ለማካሄድና ተገቢ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ለመቅረፅ እንዲቻል፣ አዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት ልዩ ልዩ አመለካከትና እምነት ላላቸው ወገኖች ተሳትፎ አመቺ ዕድል መፍጠር አለበት።

### 10.1. የአዲስ አምባገነናዊነት ሥጋት

ከረጅም ዓመታት በፊት አርስጣጣሊስ «...ጨቋኝ ጨቋኝን ሊተካው ይችላል» ብሎ ነበር። ለዚህም በቂ አብነቶችን መጥቀስ ይቻላል። ከፈረንሳይ ጃኮቢንስና ናፖሊዮን፣ ከሩሲያ ቦልሸቪኮች፣ ከኢራን አያቶላህ፣ ከበርማም እንዲሁ፣ ሊጠቀሱ ይችላሉ። በእነዚህና በሌሎችም፣ በርካታ ሀገሮች አንዱ ጨቋኝ ሥርዓት ሲወገድ ጥቂት ሰዎች ወይም ቡድኖች ወደ ሥልጣን እንዲወጡ ዕድል ሊያመቻችላቸው ይችላል። ዓላማቸው ቢለያይ እንኳ ዞሮ ዞሮ የመጨረሻ መድረሻቸው ተመሳሳይ ነው። እንዲያውም አዲሱ አምባገነን ካለፈው የባሰ ጨካኝና ጨቋኝ ሊሆን ይችላል።

እንዲያውም አምባገነናዊ ሥርዓቱ ከመፈረካከሱ በፊት፣ የአሮጌው ሥርዓት አባላት የሕዝቡን የተቃውሞ ፍላጎት በማሟላት ሥም ኩዴታ /መፈንቅለ መንግሥት/ ሊያካሂዱ ይችላሉ። ምናልባትም አምባገነንነትን በማስወገድ ሰበብ ግን የአሮጌውን ሥርዓት ምትክ በአዲስ መልክ አጋጊጠውና አሸብርቀው ሊያቀርቡ ይችላሉ።

### 10.2. መፈንቅለ መንግሥትን መዝጋት

አዲስ ነጻ በወጡ ሕብረተሰቦች [illegible] ለ ዲረግ የሚችለውን መፈንቅለ ሥልጣን የመቋቋሚያ መንገዶች አሉ። አደጋን የመቋቋሚያ

ዘዴን በቅድሚያ ማወቅ ሙከራዎችን በጅምሩ ለማክሸፍ ይበጃል:: ቅድሚያ ጥንቃቄ ከአደጋ ይታደጋል::

በመፈንቅለ መንግሥት ሥልጣን የነጠቁ ሰዎች በቅድሚያ የሚሹት ሕጋዊነትን ነው:: ምክንያቱም ለመግዛት የሚያስችላቸውን ሥነ-ምግባራዊና ፖለቲካዊ ተቀባይነት ማግኘት አለባቸውና ነው:: ስለዚህ የመጀመሪያው መሠረታዊ የመከላከል መርሆ ይህንን የሕጋዊነት ጥያቄ ለነጣቂዎች መንፈግ ነው::

ሥልጣን ቀማኞች በተጠቃው ማህበረሰብ ላይ ሥልጣናቸውን ለመጫንና ቁጥጥራቸውን ለማጥበቅ ሕዝባዊ መሪዎችና ሕዝቡ እንዲደግፋቸው፣ ወይም እንዲወናበድ፣ አለበለዚያም ምንቸገረኝ እንዲል ይፈልጋሉ:: የሥልጣን ቀማኞች የባለሙያዎችን፣ የአማካሪዎችን፣ የቢሮክራሲውን፣ የማሕበራዊ አገልግሎት ሠራተኛውን፣ የአስተዳዳሪዎችንና የዳኞችን ሁሉ ድጋፍና ትብብር ይሻሉ::

እንዲሁም እነዚህ የሥልጣን ጥመኞች በፖለቲካ ሥርዓቱ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ፣ በህብረተሰቡ ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ፣ በኢኮኖሚው፣ በፖሊሱና በወታደሩ ኃይል ውስጥ ያሉ ልዩ ልዩ የህብረተሰቡ አባላት እነሱ እንደሚመቻቸው እያስተካከሉ የሚያወርዱትን ትዕዛዝና ፖሊሲ በእሽታ እንዲያስፈፅሙ ይፈልጋሉ::

የሥልጣን ነጣቂዎችን የመቃወሚያ ሁለተኛው መሠረታዊ መርህ፣ ትብብርን መንፈግና ቀጥታ መቃወም ነው:: ተፈላጊው ትብብርና ድጋፍ መነፈግ አለበት:: ያለፈውን አምባገነን ሥርዓት ለማስወገድ የተወሰዱ እርምጃዎች ሁሉ በአዲሱም ላይ ሊሠሩ ይገባል:: ግን በጣም በፍጥነት መሆን አለበት:: ህጋዊነትና ትብብር ሁሉ ከተነፈጋቸው፣ የሥልጣን ነጣቂዎች በፖለቲካ ሥልጣን እጦት፣ ጥማትና ርሃብ በራሳቸው ሊወገዱ ይችላሉ፣ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታው ዕድልም ሊለመልም ይችላል::



## 10.3. ህገ-መንግሥት ማርቀቅ

አዲሱ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ተፈላጊውን ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለመመሥረት የሚያስችለው ህገመንግሥት ያስፈልገዋል:: ህገመንግሥቱ የመንግሥትን ዓላማ መንደፍ፣ የሥልጣን ገደቡን መወሰን፣ የህግ አውጭውና የህግ አስፈፃሚው አካላት የሚመረጡበትን ጊዜና ሁኔታ፣ የህዝቡን መሠረታዊ መብት፣ የብሔራዊ መንግሥቱንና በተዋረድ ያሉትን ክልላዊ መንግሥታት ግንኙነት ሁሉ በግልጽ እንዲያሳይ ሆኖ መቀረጽ አለበት::

ማዕከላዊ መንግሥቱ ዲሞክራሲያዊነትን ጠብቆ እንዲዘልቅ ከተፈለገ በህግ አውጭው፣ በህግ ተርጓሚውና በህግ አስፈፃሚው መካከል ግልጽ የሥልጣን ክፍፍል መኖር አለበት:: የፖሊስ፣ የደህንነት ክፍሉና የወታደራዊ ተቋማት በህጋዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ጣልቃ እንዳይገቡ ጠንካራ ክልከላ/እቀባ/ ሊጣልባቸው ይገባል::

ዲሞክራሲያዊ ሥርዓቱን ለመጠበቅና አምባገነናዊ አዝማሚያዎችንና እርምጃዎችን ለመከላከል ህገመንግሥቱ ለብሔራዊ፣ ለክልላዊና፣ ለአካባቢ መንግሥታት ተገቢ ሥልጣንና ኃላፊነት በግልጽ ወስኖ መስጠት አለበት:: በአንዳንድ ሁኔታዎች የስዊዘርላንድ ክልላዊ አስተዳደር ማለትም በአጠቃለይ ሀገራዊ ማዕቀፍ ውስጥ የአነስተኛው ሥልጣን ተቀባይነት የሚያገኝበት ሁኔታ ሊያገለግል ይችላል::

ከአምባገነናዊ ሥርዓት ነጻ በወጣው ሀገር ውስጥ ከላይ የተጠቀሱትን መሠረታዊ ነገሮች የሚያሟላ ሕገ መንግሥት ካለም ለአዲሱ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በሚስማማ መልኩ አንዳንድ ይዘቶቹን በማሻሻል፣ በመለወጥና በማስተካከል ሥራ ላይ ማዋል ይቻላል:: ተስማሚ ህገ-መንግሥት ካልተገኘም የሽግግር ወቅት መተዳደሪያ ህገ-መንግሥት ማሰናዳት ያስፈልጋል:: አለዚለዚያም አዲስ ህገ-መንግሥት ማዘጋጀት ግድ ይሆናል:: አዲስ ህገ-መንግሥት ለማዘጋጀት በቂ ጊዜና

ማስሳሰልን፣ የሚበጅ ሀሳብን ማውጣት ማውረድን ይጠይቃል:: በዚህ ሂደት ውስጥ አዳዲስ ይዘቶችን ለመጨመር፣ ለማሻሻልና ለማጥራት የህዝብ ተሳትፎ እጅጉን አስፈላጊ ነው:: በህገመንግሥቱ የሚወጡ ህጋዊ ይዘቶች በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስቸግሩ እንዳይሆኑና ወይም እጅግ የተማከሉ ሆነው ለሌላ አዲስ አምባገነናዊ ሥርዓት እንዳይዳርጉ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል::

የህገ-መንግሥቱ አንቀጾች የሚጻፉበት ቋንቋ /የቃላት አጠቃቀም፣ የሀሣብ አገላለጽ/ አብዛኛው ሰው በሚረዳው መልኩ በቀላሉ መቀናበር አለበት:: ይህም ማለት ህገመንግሥት ለህግ ባለሙያዎችና ለአንዳንድ የተማሩ ሰዎች በሚያመች ሁኔታ ውስብስብና አሻሚነት ባለው መልክ መዘጋጀት የለበትም ማለት ነው::

## 10.4. <u>ዲሞክራሲያዊ የመከላከያ ፖሊሲ</u>

ነጻ የሆነ ሀገር አንዳንድ የውጭ ወረራ ሥጋት ሊያጋጥመው ስለሚችል ራሱን የመከላከል ብቃት ሊኖረው ይገባል:: ሀገሩ ምናልባትም በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና በወታደራዊ ተፅእኖ ረገድ ሥጋት ሊያጋጥመው ይችላል::

የውስጣዊውን ዲሞክራሲ ዘላቂነት ለማስጠበቅ እንዲችል መሠረታዊ የፖለቲካዊ ተቃውሞዎች መርሆዎች በወጉና በምር እየታዩ ለሀገር መከላከሉም ተግባር ሊውሉ ይችላሉ:: ሀገር የመከላከሉንና የመቋቋሙን ችሎታና አቅም ለሕዝቡ በመስጠትና በማንቃት ብዙ ሀብትና ድርጅት የሚፈጅና ራሱም ለዲሞክራሲ ሥርዓት አስጊ የሆነ ወታደራዊ ተቋም ከመገንባት መዳን ይቻላል::

አንዳንድ ቡድኖች የራሳቸውን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችላቸው አምባገነናዊ ሥርዓት ለመመሥረት ሲሉ በህገ መንግሥቱ ውስጥ ያሉትን ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ከቁብም የማይቆጥሩ መሆናቸውን ማንም



ሊዘነጋው አይገባም:: ስለዚህ ዲሞክራሲያዊ መዋቅርን፣ መብትንና ሥርዓትን ለመጠበቅ የህዝቡ ሚና ወሳኝ ነው:: አዳዲስ አምባገነኖችን ለመከላከል ሕዝቡ ፖለቲካዊ ተቃውሞውንና እምቢተኝነቱን በቋሚነት መጠቀም አለበት::

## 10.5. <u>ከበሬታ የሚያጐናጽፍ ኃላፊነት</u>

ሰላማዊ እምቢተኝነት አምባገነኖችን ለማዳከምና ለማስወገድ ብቻ ሳይሆን ጭቁኖችን ለሥልጣን ለማብቃትም ያገለግላል:: ይህ ዓይነቱ ሥልት ራሳቸውን ደካማና ታዛዥ፣ እንዲሁም አቅመቢስ አድርገው ይቆጥሩ የነበሩትን በራሳቸው ጥረት ለታላቅ ነጻነትና ፍትህ ሊበቁ እንደሚችሉ ያሳያቸዋል፤ ያነቃቃቸዋልም:: የሰላማዊ ትግል ልምድ ቀደም ሲል ራሳቸውን አቅመቢስ አድርገው ይቆጥሩ የነበሩ ሰዎችን ሥነ-ልቦናዊ ልዕልና ይሠጣል፤ ውስጣዊ አመኔታንና በራስ የመተማመን መንፈስንና ብርታትን በማጎልበት ረገድ እጅግ ከፍተኛ ጠቀሜታም አለው::

በሰላማዊ እምቢተኝነት ዲሞክራሲያዊ መንግሥትን የመመሥረት ትግል አንዱና ዋነኛው ዘላቂ ጥቅሙ ህብረተሰቡ ወደፊት ሊያጋጥሙት የሚችሉትን ተከታታይ ችግሮች ለመጋፈጥ እንዲችል ልምድ ማስገኘቱ ነው:: ይህም የወደፊቱን መንግሥታዊ ጥቃትንና ሙስና፣ ቡድናዊ ውንብድና፣ ኢኮኖሚያዊ አሻጥርንና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓቱን ድክመት ሁሉ ለማሻሻልና ለማስወገድ ያስችላል:: በፖለቲካዊ ተቃውሞ ረገድ ህዝቡ በቂ ልምድ ስለሚኖረው ለወደፊቱ የአምባገነናዊ ሥርዓት መከሰት ሥጋት ሊቀንስለት ይችላል::

ከነጻነት በኋላ፣ የሰላማዊ እምቢተኝነት ትግል ልምድ፣ ዲሞክራሲን፣ ህዝባዊ ነጻነትንና የአናሳዎችን መብት በመጠበቅ የአካባቢን፣ የክልልና የማዕከላዊ መንግሥትን ሥልጣንና ኃላፊነት በመወሰንና የሲቪል ህብረተሰብ ተቋማትን በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ

ዘዴና ሥልት ያመለክታል። እንዲሁም አንዳንድ ተቃውሞ በሚያስነሱ ጉዳዮች ላይ ሰላማዊ ውይይት ማካሄድንና ወደ ሽብርተኝነትና ሽምቅ ተዋጊነት ሊዘልቁ በሚፈልጉ ተቀዋሚ ወገኖች ላይ በግልጽ ለመነጋገር ዕድል ይሰጣል፤ ግልጽ ተቃውሞ ለማቅረብም ያመቻል።

የፖለቲካ ተቃውሞ ወይም የሰላማዊ እምቢተኝነት ትግል ምርምር ዓላማ ግለሰቦችንና ቡድኖችን አምባገነናዊ ጭቆናን ከህዝባቸው ላይ ለማስወገድ እንዲችሉ ይረዳል። እንዲሁም ሰብአዊ መብትንና ህብረተሰቡን በማሻሻል ረገድ የሚያግዝ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማቋቋም ያስችላል።

እዚህ ለቀረበው ሀሳብ የሚበጁ ሦስት ዋና ዋና የማጠቃለያ ነጥቦች አሉ።

1. ከአምባገነናዊነት ነጻ መውጣት ይቻላል፣
2. በጣም ጥንቃቄ የተሞላበት አስተሳሰብና የአሠራር ሥልት መቀየስ ግን የግድ ነው፣
3. ቆራጥነት፣ ጠንካራ ሠራተኛነትና ሥነ-ስርዓታዊ ትግል፣ አልፎ አልፎም ታላቅ መስዋእትነት ተፈላጊዎች ናቸው።

አንዳንድ ጊዜ «ነጻነት ነጻ አይደለም» እየተባለ የሚጠቀሰው ትክክል ነው። ለተጨቆኑ ሰዎች የሚፈልጉትን ነጻነት መጥቶ ሊሰጣቸው የሚችል ምንም ዓይነት ውጫዊ ኃይል የለም። ህዝቦች የራሳቸውን ነጻነት እንዴት እንደሚያገኙት መማርና ማወቅ አለባቸው። በቀላሉም እንደማይሆን ሊያውቁ ይገባል።

ህዝቦች ለራሳቸው ነጻነት የሚያስፈልጋቸውን አቅም ከያዙ ወደ ነፃነታቸው የሚያደርሳቸው ብዙ ውጣ ውረድና ችግር ያለበት እርምጃ ሊወስዱና ትግላቸውን ሊያጧጡፉ ይችላሉ። በመሆኑም አዲስ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመሥረትና ለመጠበቅም ይዘጋጃሉ። በዚህ ዓይነት የተገኘ ነጻነት ዘላቂነት ይኖረዋል፤ ጥብቅና ጥንቁቅ በሆኑ ሰዎችም ሊጠበቅ፣ ሊስፋፋና ሊያድግ ይችላል።



# አ ባ ሪ

## የሠላማዊ እምቢተኝነት እርምጃ ዘዴዎች/ሥልቶች፦

## የሠላማዊ ተቃውሞና ቅስቀሳ ዘዴዎች፦

### መደበኛ መግለጫዎች፦

1. ህዝባዊ ውይይት/ዲስኩር
2. የተቃውሞ/ድጋፍ ደብዳቤዎች/መግለጫዎች
3. የድርጅቶችና የተቋሞች መግለጫዎች/መመሪያዎች/አዋጆች/
4. የተፈረመበት የህዝብ አስተያየት /በፊርማ የተደገፈ የህዝብ አስተያየት/
5. የክስና ውግዘት መግለጫ
6. የቡድን ወይም የብዙኃን የመማፀኛ ፊርማ

### ከብዙኃን አድማጮች ጋር የሚደረግ ግንኙነት /ተግባቦት/

7. መፈክሮች፣ አስቂኝ የካርቱን ሥዕሉችና ምልክቶች
8. ባንዲራ፣ ማስታወቂያ ወረቀት፣ ትዕይንት
9. በራሪ ወረቀቶች፣ መጻሕፍት
10. ጋዜጦች መጽሔቶች
11. ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን፣ የተቀረጹ ቁሳቁሶች /መዝሙር፣ ፊልም.../
12. በአየርና በምድር ላይ የሚፃፉ መፈክሮች፣ በህንጻዎች አናት፣ በስልክ እንጨትና በግድግዳዎች ላይ የሚሰቀሉ መፈክሮች

### የቡድን ውክልና

13. ውክልና፣
14. የፌዝ፣ /ሹፈት/ሽልማት /አሉታዊ/
15. የቡድን ቅስቀሳ፣ ውትወታ፣ ጉትጎታ፣
16. የአካባቢ ጥበቃ፣ ዘበኝነት
17. የፌዝ፣ የቀልድ ምርጫ

### ተምሳሌታዊ የህዝብ እርምጃዎች

18. ባንዲራንና ወካይነት ያላቸውን ቀለሞች ማሳየት
19. ዓርማዎችን፣ ምልክቶችን መልበስ፣
20. ፀሎትና ምህላ ማድረግ/መያዝ/

21. ተምሳሌታዊ ቁሳቁሶች ማሳየት
22. እርቃን ተቃውሞ/ ራቁት ገላን ማሳየት/
23. የግል ንብረትን ማውደም/ማጥፋት/
24. ተምሳሌታዊ ችቦ /ማብራት/
25. ምስሎችን/ሥዕሎችን ለዕይታ ማቅረብ
26. ሥዕልን/ምስልን/ እንደመቃወሚያ መጠቀም
27. አዳዲስ ስያሜዎችና ምልክቶች
28. ወካይ /ተምሳሌታዊ ድምፆች
29. መረበሽ /ማስፈራራት

**በግለሰቦች ላይ መቀስቀስ**

30. ባለሥልጣኖችን ማበሳጨት/ማሳዘን/መጥፎ ተግባራቸውን ማጋለጥ/
31. ባለሥልጣኖችን ማንጓጠጥ/ማሽሟጠጥ
32. ከሚጠሉት ጋርም ወዳጅነት መመሥረት
33. መንቀፍ፣ መዝለፍ

**ተውኔትና ሙዚቃ**

34. ዋዛ ፈዛዛ/ቀልድና ቧልት
35. የተውኔት የሙዚቃ ክዋኔ/ሙዚቃዊ ድራማ/
36. መዘመር፣ ዘፈን

**ሰልፍ**

37. ጉዞ
38. ሰልፍ
39. ሃይማኖታዊ ሰልፍ/ጉዞ
40. ሃይማኖታዊ ጉዞ
41. የመኪና አጀባ

**ሙታንን ማሰብ**

42. ፖለቲካዊ ሀዘን
43. ውሎ፣ ሽንጉ/የማስመሰል ቀብር/ የአጉበር ቀብር/
44. የተቃውሞ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ማሳየት
45. መካነመቃብር ማክበር፣ የክብር መታሰቢያ ማስቀመጥ



**ህዝባዊ ስብሰባ**

46. የድጋፍ /ተቃውሞ ሸንጐ
47. የተቃውሞ ስብሰባ/ግንኙነት/
48. የማስመሰል፣ የማደናገር የተቃውሞ ስብሰባ
49. የመማማሪያ ስብሰባ፣ ውይይት፣ የስብከት ጉባኤ

**ማፈግፈግን ማውገዝ**

50. ረግጦ/ለቅቆ መውጣት
51. ዝምታ/ፀጥታ
52. ክብርን መንጠቅ፣ መግፈፍ፣ ማቃለል
53. ፊት ማዞር፣ ጀርባ መስጠት፣ ፊት መንሳት

**ማህበራዊ ያለመተባበር ዘዴዎች**

**- ግለሰቦችን ማግለል፣ ማውገዝ፣ መነጠል፣ ማኩረፍ**

54. ማህበራዊ እድማ
55. በተመረጡ ቦታዎች ማህበራዊ እድማ/ኩርፊያ
56. ኩርፊያ/አለማናገር-መዝጋት/
57. ክልከላ/መንፈግ

**ከማህበራዊ ክንውኖች ዝግጅቶችና ተቋሞች ጋር አለመተባበር**

58. ማህበራዊና ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን ማቆም/ማቋረጥ
59. በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ማደም
60. የተማሪ እድማ /ሰልፍ
61. ማህበራዊ አመፃ/አለመታዘዝ
62. ከማህበራዊ ተቋማት አባልነት መውጣት

**ከማህበራዊ ሥርዓቱ መውጣት/ማፈግፈግ**

63. ቤት ውስጥ መቀመጥ /መዋል/
64. አጠቃላይ ግላዊ ትብብርን መንፈግ
65. ከሥራ መቅረት/ማፈግፈግ፣ መሸሽ፣ እየጠፉ መሄድ
66. መደበቅ፣ መሸሸግ፣ መሠወር
67. በቡድን መደበቅ፣ መጥፋት፣ መሠወር
68. የተቃውሞ ጉዞ

**ኢኮኖሚያዊ ትብብርን መንፈግ ዘዴዎች**

**(1) ኢኮኖሚያዊ አድማ- የተጠቃሚዎች እርምጃዎች**

69. የደምበኞች አድማ
70. አድማ የሚደረግባቸውን ዕቃዎች አለመጠቀም
71. የችግር፣ የመከራና የመከፋት ፖሊሲ
72. ኪራይ አለመክፈል
73. አለመከራየት/ለመከራየት መቃወም/
74. ብሔራዊ የተጠቃሚዎች/የገበያተኞች/አድማ
75. ዓለምአቀፋዊ የተጠቃሚዎች /የገበያተኞች አድማ

**የሠራተኞች /ያምራቾች/ እርምጃዎች**

76. የሠራተኞች አድማ
77. ያምራቾች አድማ

**የአቀባዮች እርምጃ**

78. የአቅራቢዎችና አቀባባዮች አድማ

**የባለቤቶችና ሥራ መሪዎች እርምጃ**

79. የነጋዴዎች፣ ባለሀብቶች አድማ
80. ለመስጠትም ሆነ ለመቀበል አለመፈለግ፣ መቃወም
81. ድርጅትን መዝጋት፣ መቆለፍ
82. ኢንዱስትሪያዊ ድጋፍን መቃወም
83. አጠቃላይ የነጋዴዎች /ሸማች፣ ቸርቻሪዎች፣ አቀባባዮች/ አድማ

**የገንዘብ ምንጮች እርምጃ**

84. የገንዘብ ተቀማጭን ከባንክ ማውጣት
85. ግብርን፣ ቀረጥን፣ ዕዳን፣ አለመክፈል፣ ድጋፍን መንፈግ/መቃወም
86. ዕዳ፣ ወለድ አለመክፈል፣ መቃወም
87. ተጨማሪ ክፍያን ገንዘብን አለመስጠት/መቃወም
88. የገቢ ግብርን መቃወም
89. የመንግሥትን ገንዘብ አለመቀበል፣ መቃወም፣ ማጣጣል



**የመንግሥት እርምጃዎች**

90. የሀገር ውስጥ ዕቀባ/ማዕቀብ
91. ነጋዴዎችን ማስጠንቀቅ፣ ማስፈራራት፣ መመዝገብ
92. ዓለማቀፋዊ የሻጮች ማዕቀብ
93. ዓለማቀፋዊ የገዢዎች ማዕቀብ
94. ዓለማቀፋዊ የንግድ ማዕቀብ

**ኢኮኖሚያዊ ትብብር መንፈግ ዘዴዎች**

**(1) አድማ - ተምሳሌታዊ አድማ**

95. የተቃውሞ አድማ
96. ፈጣን እርምጃ፣ የመብራት ማቋረጥ

**የግብርና ተቃውሞ**

97. የገበሬ አድማ
98. የገበሬዎችና ሠራተኞች አድማ

**ልዩ የቡድን አድማ**

99. የተፅዕኖ ሥራን መቃወም፣ እምቢ ማለት
100. የእስረኞች አድማ
101. የዕደጥበበኞች/እናጢዎች/ተቃውሞ
102. የባለሙያዎች ተቃውሞ

**መደበኛ የኢንዱስትሪ አድማ**

103. የግንባታ ሠራተኞች ተቃውሞ/አድማ
104. የኢንዱስትሪ አድማ/ተቃውሞ
105. የድጋፍ/አጋር ተቃውሞ/አድማ

**ውስን ተቃውሞ**

106. ዝርዝር ተቃውሞ/አድማ
107. መንገድ መዝጋት፣ /ፍሬን በመያዝ/ በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ላይ/
108. የማጓተት፣ የማዘግየት አድማ
109. በሥራ ላይ ያሉ ህጎችን መቃወም

110. ታሞ መቅረት፣
111. ሥራ የመተው፣ የመልቀቅ ተቃውሞ
112. ውስን፣ ንጥል/ነጠላ/ ተቃውሞ/አድማ/
113. እየመረጡ መቃወም::

## የኢንዱስትሪዎች የጋራ ተቃውሞ/አድማ

114. የአጠቃላይ አድማ
115. ጠቅላላ አድማ

## አድማዎችንና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ዝግነት ማቀናጀት

116. ኢኮኖሚያዊ ተግባርን መዘጋት/ማቆም

## የፖለቲካዊ ትብብርን መንፈጊያ ዘዴዎች

## - ባለሥልጣንን/ሥልጣን/ አለመቀበል፣ ማጣጣል

117. ድጋፍን መከልከል/ተቃውሞ ማቅረብ
118. የህዝብ ድጋፍ መንፈግ
119. የተቃውሞ ንግግሮች ሥነ-ጽሁፋዊ መግለጫዎችን ማሰራጨት

## የዜጐች ለመንግሥት ትብብር መንፈግ

120. በህግ አካላት ላይ ማደም
121. ምርጫን መቃወም/ማደም
122. የመንግሥት ሥራ ቅጥርንና ሹመትን አለመቀበል
123. የመንግሥትን ተቋማት መተው፣ ድርጅቶችንና ሌሎች አካላቱን አለመጠቀም
124. ከመንግሥታዊ የትምህርት ተቋሞች መውጣት
125. በመንግሥት የሚደገፉ ተቋማትን መተው፣ አለመጠቀም
126. የመንግሥት ድርጅቶችን ለሚደግፉ ተቃውሞ ማቅረብ
127. የግል ምልክትን፣ መለያንና መገናኛ ቦታን ማስወገድ
128. ተሿሚዎችን መቃወም፣ አለመቀበል
129. በሥራ ላይ ያሉ ተቋማትን ለማፈራረስ፣ ለማዳከም መሥራት፣ እንዳይጠናከሩ ማድረግ/መቃወም



## የዜጐችን የታዛዥነት አማራጮች

130. መለጐም ፣ ዝምተኛ መሆን
131. ቁጥጥር በሌለበት ጊዜ ሁሉ አለመታዘዝ/ማልመጥ
132. ህዝባዊ የተቃውሞ አመፃ/አለመታዘዝ/እምቢተኛነት
133. በሥውር አለመተባበር/እምቢ ማለት
134. የሸንጐ ስብሰባዎችን መበተን
135. ቁጭታ/መቀመጥ
136. ጥሪን አለመቀበል፣ መቃወም፣ አገር አቀፍ ጥሪን መቃወም
137. መደበቅ፣ ማድፈጥ፣ ማምለጥና ራስን መሠወር፣
138. ህጋዊነት ለሌላቸው ህጐች አለመገዛት፣ ማመጽ

## የመንግሥት ሠራተኞች እርምጃዎች

139. የመንግሥት ድጋፍና ርዳታ እየመረጡ መቃወም
140. የዕዝ ሰንሰለትን መበጠስ፣ የመረጃ ፍሰትን ማወክ
141. ማውገዝና ማደናቀፍ/ማገድ
142. አጠቃላይ አስተዳደራዊ ትብብር መንፈግ
143. ፍትሃዊ/ህጋዊ/ ትብብርን መንፈግ
144. በአስተባባሪዎች አማካይነት ሥራን መበደል፣ ማጓተት፣
145. ማፈንገጥ፣ አለመታዘዝ፣ ማልመጥ

## አካባቢያዊ መንግሥታዊ እርምጃዎች

146. በህግ ከለላ እየተጠቀሙ ማዘግየት፣ ማዳከም
147. ከክልላዊ መንግሥታዊ አካላት ጋር አለመተባበር

## ዓለማቀፋዊ መንግሥታዊ እርምጃዎች

148. በዲፕሎማሲና በሌሎች የውክልና ሥራዎች ለውጥ ማካሄድ
149. ዲፕሎማሲያዊ ተግባራትን/ክንዋኔዎችን/ማዘግየት
150. ዲፕሎማሲያዊ ዕውቅናን መንፈግ
151. ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትን መግታት፣ ማጓተት
152. ከዓለም አቀፍ ተቋማት መውጣት፣ መገለል

153. የዓለም አቀፍ ተቋማት አባልነትን መቃወም
154. ማባረር፣ ማስወገድ/ከሥልጣን፣ ከኃላፊነት፣ ከተሣትፎ/

**የሰላማዊ እምቢታ ጣልቃ መግቢያ ዘዴዎች**
**ሥነ-ልቦናዊ ጣልቃ የመግቢያ ዘዴዎች**

155. ራስን ማጋለጥ፣ መፀፀት
156. ፆም፣ ምህላ
ሀ. የሞራል ግፊት ለመፍጠር መፆም
ለ. የረሀብ አድማ
157. ፍርድን መሻር፣
158. በሰላማዊ እምቢታ ማስፈራራት

**አካላዊ ጣልቃ መግቢያ ዘዴዎች**

159. መቀመጥ
160. መገተር፣/ መቆም
161. ትርምስ፣ ግርግር መፍጠር
162. መጋፋት፣ መጋጨት
163. መሰባበር፣ ማድቀቅ
164. ሰ-ባኤ መግባት/መያዝ/
165. በሰላማዊ እምቢታ ግርግርና ትርምስ
166. የሰላማዊ እምቢታ ያየር ላይ ግርግር
167. ሰላማዊ እምቢታ ወረራ
168. በሰላማዊ እምቢታ ማወክ፣ ማደናቀፍ
169. በሰላማዊ እምቢታ መረበሽ ማገድ፣ መገደብ
170. በሰላማዊ እምቢታ ቦታን መያዝ፣ መሙላት፣

**ማህበራዊ ጣልቃ የመግቢያ ዘዴዎች**

171. አዳዲስ ማህበራዊ ግንኙነቶችን መመሥረት
172. የአገልግሎት ተቋማትን ማጨናነቅ
173. ማዘግየት፣ ማጓተት/አገልግሎትን/ ዘገምተኛነት
174. ንግግርን ማደናቀፍ፣ ጣልቃ እየገቡ መረበሽ
175. ሽምቃዊ ትያትር/ተውኔት



176. አማራጭ ማህበራዊ ተቋማትን ማቋቋም /ለአገልግሎት/
177. አማራጭ የመግባቢያ መንገዶችን መዘርጋት

**የኢኮኖሚ ጣልቃ የመግቢያ ዘዴዎች**

178. አመፃን መለወጥ፣ መገልበጥ
179. በአድማ ላይ መሰንበት፣ መቆየት
180. በሰላማዊ አመፃ ቦታን/መሬትን/መያዝ
181. ዕገዳን መቃወም፣ አለመታዘዝ
182. ፖለቲካዊ የተቃውም አፀፋ/ፍጥጫ
183. ግዢን ማደናቀፍ/ማቋረጥ
184. ሀብትን መያዝ/ማቀብ/መውሰድ
185. መክመር፣ መቆለል፣ ማራገፍ
186. መርጦ መደገፍ/ማበረታታት
187. አማራጭ ገበያ መፈለግ/ማቋቋም
188. አማራጭ የመጓጓዣ ሥርዓት መፍጠር
189. አማራጭ የኢኮኖሚ ተቋማት መመሥረት

**ጣልቃ የመግቢያ ዘዴዎች**

190. አስተዳደራዊ ሥርዓቱን ማጨናነቅ፣ ማጣበብ
191. የምስጢር ሥራ ወኪሎችን ማጋለጥ/ሰላዮችን፣ ወሬ አቀባዮችን.../
192. ለእሥር የሚያበቁ ንግግሮችን ማድረግ/የሚያሳስሩ አፍ አላፊ/ ለመታሠር ተሽቀዳድሞ መሄድ/ታዋቂ ሰዎች/
193. «ገለልተኛ» ለሚባሉ ህጐች ህዝባዊ እምቢታ መቀስቀስ
194. ትብብርን እየነፈጉ ሥራን መሥራት
195. መንታ ስብዕና /ልዕልና/ እና ትይዩ መንግሥት መፍጠር/ማካሄድ

## About the Author

Gene Sharp, D. Phil (Oxon.), is Senior Scholar at the Albert Einstein Institution in Boston, Massachusetts. He holds a B.A. and an M.A. from Ohio State University and a D, Phil. in political theory from Oxford University. He has also been awarded honorary degrees of Doctor of Laws from Manhattan College and Doctor of Humanitarian Service from River College. Professor Emeritus of Political Science at the University of Massachusetts Dartmouth, he has also taught at the University of Oslo, the University of Massachusetts at Boston and for nearly thirty years held a research appointment at Harvard University's Center for International Affairs. His books in English include *The Politics of Nonviolent Action* (1973), *Gandhi as a Political Strategist* (1979), Social Power and Political Freedom (1980), *Making Europe Unconquerable* (1985), and *Civilian-Based Defense: A Post-Military Weapons System* (1990). A new major book is now in preparation (2003) *Waging Nonviolent Struggle: Twentieth Century Practice and Twenty-First Century Potential.* His writings have appeared in more than thirty languages.